# ታጠቅ

አለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር
የቲዎሪ መፅሄት
አውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የተዘጋጀ

## የኢትዮጵያ ጊዜያዊ ሁኔታና ተግባራችን

የመፅሄት አዘጋጅ ቦርድ
P.O.BOX 3198
103 64 STOCKHOLM 3
SWEDEN

ማውጫ ::

ምእራፍ 1 — ከየካቲት አንቀስቃሴ የቀደሙ ትግሎች ገጽ 1
1. 1. የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ሁኔታ 1
1. 2. 1953—1960 የኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል መራራም 7
1. 3. 1961 — 62 የፋሺስታዊ አመፅ ዓመታት 11
1. 4. 1962 — 65 የጭቆናና የችጋር ዓመታት 18

ምእራፍ 2 — የየካቲት አንቀስቃሴ ጥያቄዎችና ውጤቶች 23
2. 1. ዋና ዋና ድርጊቶች 26
2. 2. በየካቲት አንቀስቃሴ የመደቦች አሰላለፍ 32
2. 3. የቀረቡት ጥያቄዎች ይዘትና የንቅስቃሴው ዋና መልክ 57
2. 4. የመንግሥት ሥልጣን ጉዳይ 61

ምእራፍ 3 — ተግባራችን 66

ተጨማሪ — የ1905 የሩሲያ ዲሞክራሲያዊ ሬቮሉሽን 70

## <u>መቅድም::</u>

በየካቲት 1966 በገሬችን የፈነዳው የኢትዮጵያ ሕዝቦች ሰፊ ረቮሉሺናዊ አንቀስቃሴ አሁንም አላበቃም::ስለዚህም፣ በዛሬው እለት የዚህን አንቀስቃሴ ይዘት፣ ድርጊቶችና ውጤቶችን ለመደርደር መነሳት ትንሽ ችኩልነት ቢሆንብን አይቀርም::አንቅስቃሴው ስላላከተመ፣ በሚቀጥሉት ገጾች ውስጥ የምናቀርባቸው አስተያየቶች ጊዜያዊ እንጂ የመጨረሻ አይደሉም::እነዚህ አስተያየቶች የመጨረሻ የማይሆኑበት ሌላ ምክንያት አለ:— ይኸውም ከቦታው ርቀን በመገኘታችን ብዙ የማናውቃቸው ሁኔታዎች በመኖራቸው ነው::ሆኖም፣ ጉድለቶች ቢኖሩትም የዚህ ዓይነቱን ጽሁፍ በሁኑ ጊዜ ማቅረብ አስፈላጊ ስለመሰለን፣ እነሆ ጽሁፉን ለአንባቢ አስተያየትና ትችት እናቀርባለን::

ጽሁፉ በሶስት ምእራፎች የተከፈለ ነው:— የካቲትን ስለቀደሙ ትግሎች፣ ስለየካቲት ትግሎችና ውጤቶች፣ በመጨረሻም ስለተግባራችን::የመጀመሪያውን ምእራፍ በሚመለከተው በኩል፣ በአውሮፓው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር መጽሄቶች፣ <u>በትግላችን</u> በተለይ፣ በሰፊው ተጠቅመናል::በነዚህ ባለፉት ሰበት ስምንት ዓመታት የሕዝብ ድምጽ በመሆን የነጻ ጋዜጣን ቦታ በመውሰድ የኢትዮጵያን ሥርዓት የተቿቿሙት የዚህ ማህበራችን መጽሄቶችና ያሚሪካው መጽሄት <u>ቻሌንጅ</u> ናቸው::ስለዚህም አሁን ጠቃሚ ሆነው መገኘታቸው የሚያስደንቅ አይደለም:
ስለዚህ ስለመጀመሪያው ምእራፍ በጠቅላላ የምናስበው፣ በተለይ ካልተመለከተ በስተቀር የቀን አቆጣጠር በገሬችን አቆጣጠር መሆኑን ነው::

ሁለተኛውን ምእራፍ በሚመለከተው በኩል የተጠቀምንባቸውን ምንጮች በቦታው ጠቅሰናል::ሶስተኛው ክፍል ምንም የተለየ ምንጭ እንደማያስፈልገው ግልጽ ነው::ይህንን ምእራፍ በሰፊው ባለመጻፋችን አያዘነን አንባቢ እንደሚያሟላው ተስፋ እናደርጋለን::

አንዱ የመጨረሻ ነገር:— ጽሁፉ የሚመለከተው እስከሀምሌ 6 ቀን 1966 በገሬችን የነበረውን ሁኔታ ነው::ጽሁፉ ዛሬ ለአትማት በሚሄድበት ቀን — ሀምሌ 15 ቀን — እንዳልካቸው መኮንን ከሥልጣን መውረዱ ተነገረ::ይህ ዜና የቀረበውን ትንተና ምንም ያህል አይለውጠውም::በተረፈ እንዲህ ያነባቢን አስተያየት እንጠብቃለን::

ከፈለቀ አውነቀ

ከአውሮፓ የኢት. ተማ. ማ. ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ጋር
በመተባበር የተዘጋጀ

ሀምሌ 15 ፣ 1966

## ምእራፍ 1::ከየካቲት አንቀስቃሴ የቀደሙ ትግሎች

> የኤርትራ፣ የባሌ፣ ... ሕዝብ ትግሎች ታሪክ፣ የተማሪዎች አንቀስቃሴ ታሪክ በጨርጨር ታትሞ በሚቀርብበት ጊዜ፣ ቀኑ እንዴት ተቃውሞን እንደወለደ፣ ተቃውሞና ቀኑ እንዴት ተያይዘው እንዳደጉ፣ከጊዜም በኋላ እንዴት ተቃውሞ ሕዝባዊ አመጽን እስከ ትሉ የአቀቲነትን ቦታ እንደያዘ በጉልህ እንደምናይ አንጠራጠርም
>
> <u>ትግላችን</u>፣ ሰኔ 1963

### 1.1. የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ሁኔታ::

ያንድን ሕብረተሰብ የውስጥ ትግሎችና ከነዚህም ትግሎች የሚፈልቀውን የወደፊት ገምጋቢ የሚወስነው ሀይል ሕብረተሰቡ የቆመበት የኢኮኖሚ ሥርዓት ነው::በኢትዮጵያ የናው ኢኮኖሚ ኋላታዊ — ባላባታዊ — ስለሆነ፣ የትግሉቹም እንብርት በገበሬውና በባለመሬት መካከል ያለው ተቃርኖ ነው::በምእራብ አገሮች የናው ኢኮኖሚ የከበርቴ — ካፒታሊስት — ስለሆነ፣ የመደቦች ትግል እንብርት በባለገንዘቡና በወዛደሩ መካከል ያለው ነው::በሶሻሊስት አገሮች የናው ኢኮኖሚ ሶሻሊስት — ማለት የሕብረተሰቡ — ስለሆነ፣ የናው ትግል ሥልጣኑን የያዘው ወዛደር በከበርቴው ተመልሶ እንዳይቀማ ለመከላከልና አዲስ ሕብረተሰብን ለመፍጠር የሚያደርገው ትግል ነው::በምእራብ አውሮፓ የናው ትግል በገበሬ መደብና በባለመሬት መደብ መካከል ሊሆን እንደማይችል ሁሉ፣ በኢትዮጵያም በሁኑ ጊዜ የናው ትግል በወዛደሩና በከበርቴው መካከል ሊሆን አይችልም::ይህ ስለተባለ ግን ይህኛው ትግል የለም፣ ወይንም ከዚያኛው ከየናው ትግል ጋር ግንኙነት የለውም ማለት አይደለም::በኢትዮጵያ ያለው የና የሕብረተሰብ ተቃርኖ በጭሰኛውና በኋለኛው — በባላባታዊው — መደቦች መካከል ቢሆንም፣ ለምሳሌ በከበርቴውና በወዛደሩ፣ በገዥና በተገዥ ብሄረሰቦች መካከልም ያሉት ቅራኔዎች ከዚህ ከየናው ቅራኔ ጋር በጥብቅ የተሳሰሩ፣ ሊነጣጠሉ የማይችሉ ናቸው::

የኢትዮጵያን የሕብረተሰብ ሥርዓት ዓይነተኛ የኋለኛ ሥርዓት የሚያደርጉት ባሕርዮች እነማን ናቸው ? የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ሁኔታ እንዴት ነው? እዝማሚያውስ ወዴት ነው ? ከዚህ በታች እነዚህን ጥያቄዎች በጭር በጭሩ ለመመለስ እንሞክራለን::

1ኛ::በጉልታዊ ሥርዓት ውስጥ በሰዎች መካከል ያለው ግንኙነት ሁሉ የሚወሰነው በመሬት ዙሪያ ነው::በዚህ ሥርዓት ውስጥ መሬት ዋናው የሕብረተሰቡ የሀብት ማፍሪያ ነው፤ እርሻም ዋናው የሕብረተሰቡ ሥራ ነው::ስለዚህም ሰዎች እርስ በርሳቸው የሚፈጥሩት ግንኙነት ሁሉ በመሬት ባለቤትነትና በእርሻ ሥራ አካባቢ መሆኑ የማያስደንቅ ግልጽ ነገር ነው::

2ኛ::ከዚህ በላይ ከተጠቀሰው ጋር ተያይዞ፤ ጉልታዊ ሥርዓትን ዓይነተኛ የሚያደርገው የጭሰኛና የባለመሬት መኖር ነው::ጭሰኛው በመሬት ላይ ሰፍሮ የመሥራት፤ የማምረትና የመኖር መብት አለው፤ ነገርግን የመሬቱ ባለቤትነት የጉልተኞች ነው::የፊተኞቹ የሕብረተሰቡ ዋና ክፍል ቢሆኑ፤ እነዚህኞቹ ግን በጣም ጥቂቶች ናቸው::በኢትዮጵያ የጉልተኛው መደብ ዋና አባሎች ነገሥታዊ ቤተሰብ፤ መሳፍንት፤ መኳንንት፤ ጥቂት የገጠር ባላባቶች፤ ሊቃነትና ታላላቅ ካህናት ናቸው::

ጭሰኛው ዋናው የሀብት ፈጣሪ ቢሆን፤ በግድ በተሰጠ መሬት ላይ ለመኖርና ለመሥራት ይችለው ዘንድ ከሚያመርተው ሁሉ የተወሰነ መጠን ለባለመሬቱ እንዲሰጥ ይገደዳል:: ባለመሬቱም በዚህ ትርፍ የሥልጣኑን ማስከበሪያ መሣሪያ — ወታደር፤ አሽከር፤ ወዘተ — ያዳብርበታል::

3ኛ::በጉልታዊ ሥርዓት የመንግሥት ሥልጣን የነገሥታዊ ቤተሰብ፤ የመሳፍንትና የመኳንንት ሆኖ፤ በነርሱ መካከልና ከነርሱም ወዲያ ያለው የሥልጣን አከፋፈል በሰው ለሰው በግል ለግል ግንኙነት ላይ፤ ማለት በዝምድና፤ በወገን፤ በውለታ፤ በትውውቅ፤ በምልጃ ወዘተ. ላይ የተመሠረተ ነው::ስለዚህም፤ የሥርዓቱ ቁንጮ የሆነው ንጉሥ የመሳፍንትንና የመኳንንትን ታማኝነትና ታዛዥነት ሹመት ሽልማት፤ ጉልትና ግዛት ሲሰጥ፤ እነዚህ ደግሞ የተባሉትን ነገሮች ለማግኘት በተቻላቸው መንገድ ሁሉ ንጉሡን ለማስደሰት ይፍጨረጨራሉ::

በተረፈም በሕብረተሰቡ ውስጥ ያለው ወግ፤ ሥርዓት፤ ' ያባቶች ቁርስ '፤ ደንብ፤ እምነት ሁሉ ይህንን የሥልጣን አከፋፈል የሚያጸድቅና ዘላቂነት እንዲኖረው ለማድረግ የሚያግዝ ነው::የጉልተኛው መደብ ፍልስፍና የበላይና የበታች፤ ጉልተኛና ጭሰኛ፤ ጌታና ሎሌ፤ ሀብታምና ደሀ በግዜር የተፈጠረ ስለሆነ አይለወጥም፤ ለመለወጥ መሞከርም የግዜርን ሥራ ለማፍረስ እንደመሞከር ነው ይላል::ይህ ፍልስፍና በዘመን [illegible] ዋና የሚገለገለው በሃይማኖት፤ በ'ግብረገብነት ትምህርት' ቢሆን፤ ዋና ግቡ [illegible] በበለመሬት ላይ እንዲያዘነብል ማድረግ ነው::

እንግዲህ፤ የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ በጠቅላላ እንነጋገር ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን ባሕርዮች ያሟላል::በተለይ እስከምኒልክ ዘመን ድረስ በተለይም በሀበሻው አገር እነዚህን ባሕርዮች በሙላት ይዞ ነበረ::ደቡቡን አገር ባለፈው ክፍለዘመን መጨረሻ ላይ [illegible] ከያዘ በኋላ፤ ምኒልክ ይህንን ሥርዓት በገበረው ሕዝብ ላይ አስፈረ::በዚህም



መሠረት፤ ከኤርትራ በስተቀር፤ የዛሬይቱ ኢትዮጵያ በሙሉ ጋደል በግድ ዓይነት የጉልተኛ የኢኮኖሚ ሥርዓት ሥር ሆነች::ይህ ሥርዓት በተለይ በገበረው ሕዝብ ላይ እስከዛሬ በገሃ መልኩ ይታያል::

ይሁንናም፤ ምኒልክ በግድ በኃይል ደቡቡን አገር ይዞ የሀበሻን፤ በተለይም በ18 እና በ19ኛው ክፍለዘመኖች ተረቅቆ የነበረውን የሸዋን የጉልተኛ ሥርዓት ሲያሰፍርበት፤ በሌላ በኩል ደግሞ፤ ለንጉሠነገሥቱ መንግሥት መፈጠር አንድ አንቀሳቃሽ ምክንያትና ደጋፊ የሆነውን የምእራብን 'ሥልጣኔ' ወዳገሪቱ ማስገባት ጀመረ::የምእራብ ሥልጣኔ ማለትም የምእራባውያን የኢንዱስትሪ እቃ፤ ሸቀጣሸቀጥ፤ የምእራብን የገንዘብ ኢኮኖሚ፤ የምእራብን ያስተዳደር ዘዴና በመጨረሻም አስተሳሰቡን ማለት እንጂ ሌላ ትርጉም የለውም::ይህ ሥልጣኔ ወደኢትዮጵያ እንደገባ፤ ከላይ የጠቀስነውን፤ ለብዙ መቶ ዓመታት በተለይ በሀበሻው አገር የኖረውን የጉልተኛ ሥርዓት ቀስበቀስ እንደምስጥ ይበላው ጀመረ::ያኔ ቀስ በቀስ ነበር፤ ዛሬ ግን፤ በተለይም ከጣሊያን ወረራ ወዲህ፤ የተባለው 'ሥልጣኔ' የኢትዮጵያን የጉልተኛ ሥርዓት በርብሮታል::ምን ማለታችን እንደሆነ በጭሩ እናብራራ:—

በኢትዮጵያ፤ አሁንም ቢሆን ዋናው በሰዎች መካከል ያለው ግንኙነት ይበልጡን በመሬት ባለቤትነት ላይ የተመሠረተ ነው::ይሁን እንጂ የጥንቱ የጉልተኛና የጭሰኛ ግንኙነት መልኩን ለውጧል::የጥንቱ ጉልተኛ በዚያው በመሬቱ ላይ እየኖረ፤ ከጭሰኛው የእህልና የጉልበት ግብር እየወሰደ፤ በዚያው ወረዳውን፤ ወይም ቀበሌውን ያስተዳድር ነበር::ጉልተኛው ከካባቢው ሕዝብ ይለይ የነበረው በሀብቱ በዘሩና በርስቱ ላይ በተመሠረተው ሥልጣኑ ነበር በዚያን ዘመን የጉልተኛና የጭሰኛ ጥቅም መጋጨቱ ባይቀርም፤ መላ ሥርዓቱ ባይናጋ ተቻችሉ ይኖሩ ነበር::ተቻችሎ ለመኖር ጠቀሳሳው ሁኔታ ይፈቅድለት ነበር::

የገንዘብ ኢኮኖሚና የምእራባውያን ያስተዳደር ዘዴ ወዳገሪቱ ከገባ በኋላ፤ ከተሞችና ንግድ ተስፋፉ፤ መንገዶችና ሌሎች መገናኛዎች በመጠኑ ተዘረጉ::ባለመሬት ከጭሰኛው ርቆ፤ በከተማ እየኖረ፤ ጭሰኛው እህል ሸጦ ጥሬ ገንዘብ እንዲያመጣለት የሚጠይቅ ሆነ:: የባለመሬት ወጪም እየበዛ ስለሄደ — የምእራባውያን ሸቀጣሸቀጥ መግዛት ስለለበትና — ከጭሰኛው ይበልጥ ይጠይቅ ጀመር::ገን ጭሰኛው በዚያው በድሮው መሣሪያው እየሠራ፤ ከእለት ወደእለት ይበልጥ መዘረፉን ባይኑ እያየ፤ በሌላ በኩል ደግሞ እሪጡም ቢሆን ከዘመኑ ሥልጣኔ ለመጠቀም እየተመኘ፤ ግን ደግሞ ድሀ፤ መሃይም፤ በሽተኛ ሆኖ ሳለ፤ እንዴት አድርጎ ምርቱን ከፍ ሊያደርገው ይችላል ? በዚህ ሁኔታ ባለመሬቱ ከሶስት መንገዶች አንዱን ይይዝ ጀመር:— ወይ እንደዚያም ሆኖ ገበሬው እስኪፈርስ ድረስ ይዘርፈዋል፤ ወይንም ከመሬት ነቅሎ ዘመናዊ እርሻ ያስገባበታል፤ ወይንም መሬቱን ሸጦ በገንዘቡ አክሲዮን ይገዛበታል በየከተማው የኪራይ ቤት ያሠራበታል፤ ወዘተ. ::ለማንኛውም፤ ለጭሰኛው ያለው 'ምርጫ' ከሁለት አንዱ ሆኗል:— ወይ እየተዘረፈ፤ ሥቃዩን እያየ እስከመጨረሻው መቆየት፤ ያለዚያ ሁሉንም እርግፍ አርጎ ጥሎ ወደከተማ መሰደድ::

የዛሬይቱ ኢትዮጵያ የችግር አገብርት ይኸ ነው፡፡ባንድ በኩል፣ የጥንቱ የጉልተኛ እና የጭሰኛ ግንኙነት አሁንም ስላለ፣ የጉልተኛው መደብ በየጊዜው ከገበረው የበለጠ ይጠ ይቃል፡፡ባገሪቷ የገባው የገንዘብ ኢኮኖሚ ጉልተኛው ከገበረው የበለጠ ምርት እንዲጠይቅ ከመገፋፋቱም በላይ፣ ገበሬው አራሹም ሸቀጣሸቀጡን እንዲገዛ፡ እንዲገብር፡ ጤናውን እንዲጠ ብቅ፣ በጥቂቱ 'እንዲሠለጥን' ይገፋፋዋል፡፡በሌላ በኩል ደግሞ፣ ይህው የጥንቱ ግንኙነት አራሹ ገበሬው የበለጠ እንዳያመርት፡ እንዳይገብር፡ ጤናው እንዳይጠበቅለት፡ እንዳይሸለውም እንዲያውም እንዳይሠለጥን ያደርገዋል፡፡በዚህ ዓይነት ሁለገብ ተቃርኖ የጥንቱ ሥርዓት የዘ መኑን ግስጋሴ ለመገደብ ይጣጣራል፡፡አሮጌው አዲሱን በሙሉ ጉልበቱ ይቋቋማል፡፡የተጸነሰ አዲስ ግንኙነት፡ አዲስ ሥርዓት እንዳይወለድ አሮጌው አፍኖ ለማስቀረት ይሞክራል፡፡

ነገ ያረጀ ሳይሉ የግድ ቦታውን መልቀቅ የሕብረተሰብ ያስተሳሰረ ሕግ ስለሆነ፣ አሮጌው እየደከመ እየዛለ ሂዶ እየጠነከረ በሚመጣው በአዲሱ በመጠረሽ ይተካል፡፡የጥንቱ የኢትዮጵያ ሥርዓት ተብረክርኮ፣ በመፈረካከስ ላይ ነው ስንል እንግዲህ፣ በጭሰኛና በጉልተኛ መካከል ያለው ግንኙነት ከእንግዲህ ጊዜ አልፎበታል፣ አይዘልቅም፣ መጥፊያው ደርሷል ማለታችን ነው፡፡በዚህ ጽሁፍ ውስጥ የምናነሳው የየካቲት አንቀሳቃሴ ይህንን ያሳየናል፡፡

ከዚህ መሠረታዊ ተቃርኖ የተነሣ፣ የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የተበላሸ፣ ውጥንቁ የወጣ፣ ወደኋላ የቀረ የሚጋዝ ኢኮኖሚ ሆኗል፡፡ለዚህ ማስረጃ ቁጥሮችን መጥቀስ ባላስፈለገ ነበር፡፡የሚታይ፣ የሚዳሰስ መበስበስ ነው ለማለት ይቻላል፡፡በአገሪቷ ታሪክ ውስጥ እኩያ የሌለው የዛሬው የኢትዮጵያ ሕዝቦች ታላቅ ረሀብ በቂ ምስክር ነው፡፡ይሁንናም፣ የዘመኑ የሥርዓቱና የባእድ ዘራፊዎች ደጋፊዎች የሆኑ ቀኝት አዋናቢዎች ምሁራን በቁጥር ሰው ለማታለል ስለሚፍጨረጨሩ፣ የመንግሥቱን ቁጥሮች — ስታቲስቲኮች — አረብቸውን ጠቅሶ፣ የኢኮኖሚውን አዘቃቀቂ ማየቱ አይከፋም፡፡

የመንግሥቱ ቁጥሮች እንደሚነግሩን ሁሉ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር በዓመቱ በ2.5 በመቶ የሚጨምር ሲሆን፣ በዚህ በሚመጣው ዓመት ጠቅላላው ሕዝብ 28 ሚሊዮን ይደርሳል ተብሎ ተገምቷል፡፡ — አሁን በአገሪቷ የተንሠራፋው ችጋር ብቻ ሁለት ሚሊዮን ሕዝብ ካልፈጀ በስተቀር—፡፡የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር በ2.5 በመቶ በመጨመሩም፣ የኢትዮጵያ የእህል ምርት ባለፉት ሀያ ዓመታት በዓመቱ የጨመረው በ1 [illegible] በመቶ ብቻ ነው፡፡በሌሎቹ ዓመቶች ዋር ፋ፣ ከ1960 እስከ 1963 ያሉትን ቁጥሮች በመለከት፣ በነዚህ ዓመታት ውስጥ የጤፍ ምርት ለምባሌ የጨመረው እንደዚሁ በ1.5 በመቶ ብቻ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡በሌላ በኩል ግን ወደ ውጭ የሚላከውና ለከበርቴዎች ገንዘብ የሚያመጣው ቡና በነዚሁ ዓመታት ውስጥ በዓመቱ ከ4 እስከ 5 በመቶ ይጨምር ነበር፡፡ከዚህ ሁሉ የተነሣ፣ የገጠሩ ሕዝብ የኑሮ ደረጃ የዛሬ ሀያ ዓመት ከነበረበት እንኳንም ዝቅ አለ እንጂ ፈጽሞ አላደገም፡፡—ለዚህ ቻሌንጅ የሚባለውን የኢት.የዓ መጽሔትን፣ ጃንዋሪ 1971፣ መመልከት፡፡—



የዛሬ ስ ድስት ዓመት የምእራብ 'ኤክስፐርቶች' ስለኢትዮጵያ ኢኮኖሚና እርሻ የሚከተለውን ጽፈው ነበር፡—

'በቅርቡ የተደረጉ ምርመራዎች እንደሚያሳዩት፣ ኢትዮጵያ ተከታትሉ ወደሚመጣ የኢኮኖሚ ችግር በማምራት ላይ ናት፡፡የጊንሰበርግ 'የሰው ጉልበት ምርምር' ያገኛቸው ቁጥሮች፣ የርሻ ምርምር ሀላፊዎችና አማካሪዎች ቁጥሮች፣ እንዲሁም የተባበሩት መንግሥታት የምግብና የርሻ ድርጅት ኤክስፐርቶች ቁጥሮች እንደሚያሳዩት ሁሉ፣ በርሻ በኩል አንዱ ጥብቅ እርምጃ ካልተወሰደ አገሪቱ ወደምግብ እጦት በማምራት ላይ ናት፡፡ . . . በቅርቡ የተደረገው የስታቲስቲክ ጥናት እንደሚያሳየው በ1970—72——አአአ——በኢትዮጵያ ውስጥ ትልቅ የምግብ እጥረት ይኖራል፡፡'

ትግላችን ቁ.1 ፣ ጥቅምት 1963 ፣ ገጽ 5

የዛሬ አራት ዓመት የመንግሥቱ ጋዜጣ አዲስ ዘመን በሰኔ 3 ቀን 1962 ባወጣው 'ዱቄት በየቤቱ መቼ እስከመቼ?' በሚል ጽሁፍ ውስጥ፣ 'የኢት.የእህል ማህበር ዱቄትን በየቤቱ እያዞረ ለመሸጥ መወሰኑን ከጠቀሰ በኋላ እንዲህ ይላል—

'ይሁን እንጂ የሸያጩ መጠን ቤተሰብን የሚያጠግብ ነው ብሎ ለመገመት አዳጋች ባይሆን አይቀርም፡፡15 እና 25 ኪሎ የጤፍ ዱቄት በነፍስ ወከፍ እንኳ ቢሸጥ ሶስት ወር ክረምቱን እንደማያወጣና ችግሩን እንደማያሸንፍለት ግልጽ ነው፡፡'

የኢትዮጵያ የጉልተኞች ሥርዓት በፍጥረቱ ምንም እርምጃ ለዚህ ለመውሰድ እንደማይችል ትግላችን በጊዜው ገልጾ ነበር፡፡የትላልቅ ባለመሬቶች፣ የከበርቴዎችና የባእድ ዘራፊዎች የጥቅም ጠባቂ እንጂ የሕዝቡን ደህንነት ጠባቂ ያልሆነው የኢትዮጵያ መንግሥት ከያቅጣጫው የቀረበለትን ማስጠንቀቂያ ከመጤፍም ስላልቆጠረው፣ እላይ የተጠቀሰው ትንቢት ልክ በቁጥር ደረሰ፡፡ከግማሽ ሚሊዮን በላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ በ1965 እንደቅጠል ረገፈ፡፡ይህንን አሰቃቂ ወንጀል የፈጸመው ሥርዓት አሁንም በቦታው አለ፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር በዓመቱ በ2.5 በመቶ ሲጨምር፣ የእህል ምርት ግን ከዚያ በጣም ባነሰ እየጨመረ፣ ወደእህል እጥረትና ከዚያም ወደረሀብ ተደረሰ፡፡መንግሥቱ የከበርቴዎችን መብትና ጥቅም የሚጠብቅ ስለሆነ፣ እህል ያላቸው ከበርቴዎች ዋጋቸውን እንዳሻቸው እንዲጨምሩ እየተደረገ፣ ሠርቶ አደሩ ሕዝብ ያለችውን ሁሉ አሟጦ እንዲያስረክብ፣ ከዚያም እንዲራብ ተገደደ፡፡የዋጋን መጨመር በሚመለከተው በኩል ለምሳሌ የመንግሥቱ ስታቲስቲኮች አሁን በረሀብ ለተጠቃው ለደሴ ከተማ የሰጧቸውን ቁጥሮች እንመልከት፡—

የዋጋው በኩንታል ነው

| | ገብስ | በቆሎ | ጥቁር ጤፍ |
|---|---|---|---|
| 1960–61 | 12.00 | 10.50 | 22.67 |
| 1961–62 | 16.58 | 14.58 | 25.50 |
| 1962–63 | 26.00 | 22.79 | 33.25 |

ከነዚህ ቁጥሮች፣ ከመንግሥቱ የስታቲስቲክስ መጽሔት ከተገለበጡት፣ እንደሚታየው፣

ከ1960 እስከ 1963 ባለው አጭር ጊዜ ውስጥ በደሴ ከተማ የገብስ ዋጋ ከ133 በመቶ በላይ፣ የበቆሎ ዋጋ ከ115 በመቶ በላይ፣ የጤፍ ዋጋ ከ50 በመቶ በላይ ጨምረዋል:: የዘረፉቸ ስታቲስቲኮች የሉንምና ነው እንጂ የእህል ዋጋ ከ1960ው ዋጋ ጋር ሲመሰሰል የዚያኛው አራት ወይም አምስት እጅ ባይሆኑ አይቀሩም::በዚህ ሁኔታ ዘጠና በመቶው የኢትዮጵያ ሕዝብ በረሃብ: በረብና እንደቀጠለ ቢረገፍ ምን ያስደንቃል ??

ያገሪቷ ኢኮኖሚ የከሰረና ወደውድቀቱ የሚጓዝ ለመሆኑ ሌላ የማያወላውል ምልክት ከስፈለገ፣ በያመቱ እየተደጋገመና እየበሰ የሚሄደውን የውጭ ንግድ ሚዛን ጉድለት ለመጥቀስ ይቻላል::የመንግሥቱ ቁጥሮች እንደሚያሳዩት፣ በ1960–61 የ166.5 ሚሊዮን ብር: በ61–62 የ90.2 ሚሊዮን: በ62–63 የ123.2 ሚሉዮን ኪሣራ አለ::ገዥው መደብ ለመንደላቀቂያ በያመቱ የሚያስመጣቸው እቃዎች የዚህ ጉድለት አንዱ ትልቅ ምክንያት ለመሆናቸው ጥርጥር የለውም::

ዘጠና በመቶው የኢትዮጵያ ሕዝብ እየተራቆተና ይበልጡን እየደኸየ: እየተራበ ይሄዳ እንጂ: ገዥው መደብና የባእድ ኩባንያዎች ግን በያመቱ ትርፋቸውን እንደዛቁ ናቸው::እንደነወጊ ስሏ: እንደነሚቻልኮትስ: እንደነኮተኔሬችዮ ወዘተ. ያሉት ኩባንያዎች በያመቱ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ሀብት ያተርፋሉ::ማትረፍ ብቻ ባይሆን ወደያገራቸው ሕጋዊና ሕገወጥ በሆነ መንገድ ሁሉ እየዘረፉ ይልካሉ::ለዚሁም የንጉሠነገሥቱ መንግሥት ሙሉ ትብብሩን ሲያበረክትላቸው እንደኖረ የታወቀ ነው::

ኢኮኖሚ የሕብረተሰብ መቆሚያ መሠረት ስለሆነ፣ እርሱ ከተበላሸ፣ ከከሰረ፣ የተሸለ የትምህርት: የጤና: የሕዝብ ደህንነትና ወቀሳሳ ሰብአዊ የኑሮ ደረጃ ሊጠበቅ አይችልም::ስለዚህም በነዚህ ነገሮች ሁሉ አገራችን ወደኋላ ከቀሩት የዓለም አገሮች ከመጨረሻዎቹ ውስጥ እንደሆነች ዛሬ በግልጽ ታውቋል::ባለፈው ዓመት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በቀዳሚያ መረዳት ያለባቸው: ከሁሉ ደሀ የሆኑ አገሮች ብሎ የ25 አገሮችን ዝርዝር ሰጥቶ ነበር::ኢትዮጵያ ከነዚህ ውስጥ ከመጨረሻዎቹ ነች::በአፍሪካ ውስጥ ከኢትዮጵያ የበለ አገር ቢኖር ማሊ የሚባለው አገር ነው ይባላል::የቀረው ሁሉ በኑሮ ደረጃ: በትምህርት: በጤና አጠባበቅ: በመገናኛዎች፣ በሞሬ በልማት ሁሉ በጣም የደቀቀን ሂደክል::

እንኳንስ ከአፍሪካ ከዓለምም ቢሆን በጣም ሀብታም ሊሆኑ ከሚችሉት፣ የተፈጥሮ ሀብት ከሞላቸው አገሮች አንደኛዋ ኢትዮጵያ ስትሆን፣ እንኳንስ 25 ሚሊዮን ቀርቶ 250 ሚሊዮን በደንብ መግብ ልታኖር ትችላለች የተባለች አገራችን፣ ሥር የሰደደ ሕዝብ በነፍ ባይታይ ላቡንና ደሙን እንደፍጥፍ የሚሠራበት አገራችን እንደዚህ ወደኋላ የቀረችው የበሰበት ሥርዓት ጊዜው ያለፈበት ስለሆነ ብቻ ነው::ይህ ሥርዓት ያረጀ ያፈጀ ነው::ከገነ ዛሬ አሥር ጊዜ ቢወጋገኑት ምንም ፋይዳ የለውም::የሚያስፈልገው እርሱን አፍርሶ በቦታው አዲስ የሕዝብ ሥርዓት ማቆም ብቻ ነው::ይህም አስፈላጊና የሚቻልም መሆኑን የየካቲት አንቅስቃሴ አሳይቶአል::



ይህ የየካቲት እንቅስቃሴ ድንገት ከሰማይ ዱብ ያለ አይደለም::ብዙ ትግሎችና መሥዋእቶች ተደምውታል፣ እርሱም የነርሱ ውጤት ነው::እነዚህን ትግሎች በሚገባ ካልተመለከትን የጊዜውን እንቅስቃሴ ትርጉም ልንረዳው አንችልም::ከዚህም በላይ አስፈላጊ የሆነውን የወደፊቱን አዝማሚያውን ልንገነዘብ አንችልም::የየካቲትን እንቅስቃሴ አዝማሚያ ካልተረዳን ደግሞ እንዴት አድርገን የራሳችንን ተግባርና መንገድ እንቀይሳለን ?

የየካቲትን እንቅስቃሴ የቀደሙት ትግሎች እንዳሉ ሁሉ፣ ወደፊትም የሚከተሉት ገና ይኖራሉ::የኢትዮጵያ ሕዝቦች ሬቮሉሺናዊ ትግል ገና መጀመሩ ነው ለማለት ይቻላል::ገን እስካሁን የተደረጉት ትግሎች የኢትዮጵያን ሕዝቦች ከምን የታሪክ ደረጃ ላይ አድርሰውታል? ያሁኑስ ትግል ወዴት ያመራል ? ከዚህ በታች ከቀደሙት ትግሎች ዋናዋናዎቹን እነይ:—

## 1.2. 1953—1960::የኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል መረረም

የታህሣሥ 1953 የመንግሥት ግልበጣ ሙከራ በታሪክ ዘመን አንጻር ሲታይ ይህን ያህልም የቆየ አይደለም::ዛሬ 13ኛ ዐመቱን መያዙ ነው::ይህ በጣም ትንሽ ጊዜ ቢሆንም በነዚህ 13 ዓመቶች ውስጥ በኢትዮጵያ ያለው የመደቦች ትግል ትልቅ እርምጃን እያደረገ እስከዛሬው እንቅስቃሴ ደርሶአል::የታህሣሡ የነገርማሜ ነዋይ የመንግሥት ግልበጣ ሙከራ እንኳንስ ሕዝቡን ሊያንቀሳቅስ ቀርቶ፣ ሠራዊቱን እንኳን በሙሉ እንቀሳቅሶት እንዳልነበረ ይታወሳል::የየካቲቱ እንቅስቃሴ ገን የኢትዮጵያን ሕብረተሰባዊ መደቦች ሁሉ ነክቶቸዋል ይሆንናም የታህሣሡ የመንግሥት ግልበጣ ሙከራ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ተገቢውን ምእራፍ ይይዛል::ለኢትዮጵያ ሕዝቦች ሁለት ነገሮችን በተለይ አስተምሮ አልፏል:—

መጀመሪያ ነገር፣ የንጉሠነገሥቱ መንግሥት ሥልጣን ይነገርለት እንደነበረው ምንም መለኮታዊ እንዳልሆነና ሊደፈር፣ በኃይል ሊሞከር እንደሚችል ግልጽ አድርጓል::በዚያውም የንጉሠነገሥቱ መንግሥት ,ባሕርይ በልመና፣ በልምምጥ፣ በአቤቱታና በጸሎት ሊለወጥ እንደማይችልና ለውጥ ከተፈለገ በኃይል መጠቀም እንደሚያስፈልግ አሳይቶአል::

ሁለተኛ ነገር፣ ይህ ባገርወዳጆችና በዲሞክራሲያዊ ግለሰቦች የተመራ የግልበጣ ሙከራ ከሥርዓቱ ውስጥ ጥቂቶቹን ማስወገድና ከገዥው መደብ ሌላውን ክፍል በቦታው መተካት ለሕዝቡ ምንም ያህል ጥቅም ሊያመጣ እንደማይችል አስተምሯል::እንደኢትዮጵያ የኋለተኛ ሥርዓተ—ማህበር ያለውን ሕብረተሰብ በማሻሻል፣ ወይንም ሰዎችን በመሾም በመለዋወጥ ሥርዓቱን ሕዝባዊ ለማድረግ አይቻልም::ይህንን ሕብረተሰብ ለውጦ ሕዝባዊ ለማድረግ ከተፈለገ ዘጠና በመቶውን የኢትዮጵያን ሕዝብ አንቀሳቅሶ እንዲታገል ማድረግና ሕዝቡ እራሱ ሥልጣኑን በእጆቹ እንዲጨብጥ፣ አዲስ ሥርዓት እንዲፈጥር ማድረግ ያስፈልጋል::

ከታህሣሥ የገለበጣ ሙከራ በኋላ፣ የከተማው ነዋሪ፣ በተለይም ተማሪው ሥርዓቱን በግልጽ መቃወም ጀመረ::ከ1954 ጀምሮ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ተማሪዎች ነገሮችን እየገመ ያወግዙ ጀመር::በቲያትር መልክ እያደረጉ የሠርቶ ማ ከንጉሠነገሥቱ ከራሱ ፊት ሥርዓቱን አደፋን ሕዝብ የሥቃይ ኑሮ፣ ያገሬቷን ወቀሳ ወደኋላ መቀረት፣ የሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን አለመኖር በይፋ አወጡ::ሥርዓቱን ከሚያወጡት ሀይሎች የመጀመሪያዎቹ — ከታህሣሥ በኋላ — እነዚህ ነበሩ::

የኢትዮጵያ መንግሥት የኤርትራን የፌደሬሽን ውል ከመጨፍለቅ በይፋ ቆርጦ ኤርትራን ጠቅላይ ግዛት እንዳደረጋት፣ ወዲያው በ1953–54 የኤርትራ ነፃ አውጪ ግንባር ተቋቁሞ የመጀመሪያዎቹን ጥይቶችን በኤርትራ ገጠር ይተኩስ ጀመር::

የሶማሊያ ሪፐብሊክ የተፈጠረችው በ1952 ሲሆን፣ የርሷ መሬወርና ታደርግ የነበረው ፕሮፓጋንዳ የውጋዴንና የባሌን ሕዝቦች የፖለቲካ ንቃት ከፍ ስላደረገ፣ እነዚህ ሕዝቦች በኢትዮጵያ ሥርዓት ላይ ነቅተው መታገል ጀመሩ::በተረፈም የኢትዮጵያ መንግሥት እራሱ ከ1954 እስከ 1956 ባለው ጊዜ ውስጥ፣ የውስጥ ችግሮችን ለመሸፈን፣ የድንበር ግጭቶች እየፈጠረ ከሪፐብሊቷ ሶማሊያ ጋር ከመዋጋቱም በላይ፣ በውጋዴን ብዙ መንደሮችን ከርፍሳን በቦምብ እያስደበደበ ብዙ ሕይወትና ንብረት አጠፋ::በባሌም እንደዚሁ ያገሩን ሕዝብ በጦር ሠራዊት ከመጨፍጨፉም በላይ ከብቱን ነድቶበታል፣ መሬቱን ቀምቶታል::

የዚህ ዓይነቱ ትግል በየገጠሩ እየበረታ ሲሄድ፣ በከተማው ደግሞ ሠራተኞች የመብት ጥያቄ ማቅረብ ጀምረዋል::በ1955 ያታቄ ፋብሪካ ሠራተኞች የደሞዝ ጭማሪ ለመጠየቅ ሰላማዊ ሰልፍ ቢያደርጉ መንግሥቱ ፖሊስ ልኮ አስተኮሰባቸው::ብዙ ሠራተኞች ተገደሉ:: (ትግላችን ቁ.፩፣ 1960፣ ገጽ 82::) በዚያው ዓመት የኢትዮጵያ አየር መንገድና የምድር ባቡር ሠራተኞችም ለደሞዝ ጭማሪና ለሰለቀሳሳው የኑሮ ሁኔታቸው የጋሉ ትግሎች አድርገው እንደነበረ ይታወሳል::

ተማሪዎች በተለይ ሥርዓቱን መቃወም እንደጀመሩ ከዚህ በላይ ጠቅሰናል::የተማሪ ትግል በዚያን ጊዜ የሕዝቦች ትግል ነጸብራቅ ነው፣ የሕዝቦች ትግል ግልባጭ ነው ለማለት ይቻላል::በሕብረተሰቡ ውስጥ ያሉትን ቅራኔዎች በግልጽ የሚያወጧቸው ተማሪዎች ናቸው ለማለት ይቻላል::በተለይም የኢትዮጵያ ተማሪዎች ካሉበት ሕብረተሰባዊ አካባቢ የተነሣ፣ ለፍትህና ለሰብአዊ መብቶች፣ ለዲሞክራሲያዊ ኑሮና ለእኩልነት የሚቆሙ፣ የሚታገሉ መሆናቸውን ደጋግመው አሳይተዋል::ከዚህ በታች እንደምናየው ሁሉ፣ ግንኙነትም መምጣት ሲፈለግ በነዚህ ባለፉት አሥር ዓመታት ለኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል ትልቅ አስተዋጽኦ አድርገዋል::

ከታህሣሥ የመንግሥት ገልበጣ ሙከራ በኋላ፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ለመጀመሪያ ተሰልፈው የወጡት በ1957–58 ሲሆን፣ የያዟቸው ሰሌዳዎች 'ድህነት ወንጀል ነውን?' 'መሬት ላራሹ' የሚሉ ነበሩ::....



በሚቀጥለው ዓመት፣ በህዳር 10 ቀን 1959፣ በሲኒማ አምፒር ውስጥ ቦምብ ተወረወረ ተብሎ እነመቶ አለቃ ማሞ መዘምር ተያዙ::በ1958–59 በጣም ጠንክሮ የነበረው የሜጫ–ቱለማ የመረዳጃ ማህበር የኦሮሞዎችን ብሔረሰባዊ ስሜት ይቀሰቅሳል ተብሎ ስለተፈራ፣ የንጉሠነገሥቱ መንግሥት ይህንን የቦምቡን የቀስቃሽ — ፕሮቮከተር — ሥራ በገዛ ሰላዮቹ ካስፈጸመ በኋላ፣ ማሞ መዘምርን፣ ታደሰ ብሩንና ሌሎች መቶ የሚያህሉ የመረዳጃ ማህበሩ አባሎችን ያዘ::ከነዚህ ውስጥ ስምንቱን ብቻ 'ለፍርድ' አቀረበ፣ የተባለው ፍርድ በምሥጢር ከተካሄደ በኋላ፣ በ1960 በማሞ መዘምርና በታደሰ ብሩ የሞት ቅጣት ፈረደባቸው::ማህበሩም በሕግ ተከለከለ::ከዚህ በኋላ፣ ህዳር 4 ቀን ማሞ መዘምር በስቅላት ሲሞቱ፣ የታደሰ ብሩ ፍርድ ግን ወደቶም እስር ተለወጠ::በዚያን ጊዜ ከተያዙት ኦሮሞዎች ሀይለማርያም ገመዳ ከፖሊስ ከባድ ድብደባ በኋላ ሲሞቱ፣ ሰይፉ ተሰማ ደግሞ በቶም እስር እንግላ፣ መስከረም 16 ቀን 1964 በመርዝ ተገድሏል::(ትግላችን ቁ.2፣ ህዳር ጥር 1963፣ ገጽ 48–54:: ቁ.4፣ ታህሣሥ 1964፣ ገጽ 38)

በ1959 የተደረገው የኦሮሞ ብሔረሰብ እንቅስቃሴ፣ በተለይም በተባለው መረዳጃ ማህበር አማካይነት ገንዘብ ለመሰብሰብ፣ ትምህርት ቤቶችንና ክሊኒኮችን ለማቋቋም የተደረገው ጥረት፣ የኦሮሞ ሕዝብ ዋና ጠላት የሆኑትን የሸዋ የገዥ መደቦች አስደነገጧቸው ነበር::እነአክሊሉ–አካለወርቅ ሀብተወልድ፣ እነሣህሉ ድፋዩ፣ እነይልማ ሺበሺ ያሉ የነፍስገዳይ ቲያትር አዘጋጅተው የኦሮሞን ሕዝብ ብሔረሰባዊ እንቅስቃሴ ለመደምሰስ የተነሡት እና ለጊዜውም የደመሰሱት በዚህ ምክንያት እንደነበረ ምንም ጥርጥር የለውም::

ከሕዝቦች ትግል የተነሣ፣ በጠቅላላው 1959 ለኢትዮጵያ መንግሥት በጣም የፈተና ዓመት ነበር::ከኤርትራ፣ ከባሌና ከሌሎችም የገጠር ትግሎች ላይ በመደረብ የኦሮሞ እንቅስቃሴ በዋናው ከተማ በራሱ በመነሣቱ፣ በዚህም ላይ የተማሪው ትግል በመፋፋም መንግሥቱ ተጠነቀ::በዚህ ምክንያት ፍጹም ፋሺስታዊ የሆነ ሕግ በመጋቢት ወር 1959 አወጣ::በዚሁ ሕግ መሠረት ሰላማዊ ሰልፍን ለማድረግ ሳምንት አስቀድሞ ከአገር ግዛት ሚኒስቴር ፈቃድ መጠየቅ እንዳለበትና እንደዚሁም በማንኛውም ጊዜና ሁኔታ ያለመንግሥት ፈቃድ ከአምስት ሰው በላይ ሳሰበሰብ እንደማይቻል ታወቀ::በዚህ ሁኔታ፣ ያዲስአበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ሚያዝያ 2 ቀን 1959፣ 'ነቀፌታን የማይቀበል መንግሥት ዘለቄታ የለውም' በማለት ሰላማዊ ሰልፍ አደረጉ::በፖሊስ ተደበደበው ብዙዎች ቆሰሉ::(ትግላችን፣ቁ.6፣ 1960)

ይሁንናም፣ ፋሺስታዊ ሕጉን አስከማውጣት ከመድረሱ በፊት፣ በዚሁ ዓመት መጀመሪያ ላይ መንግሥቱ አንድ አጭበርባሪ እርምጃ ወስዶ ነበር::ይኸውም፣ የመንግሥቱን ሚኒስትሮች ከንግዲህ ጠቅላይ ሚኒስትሩ እየመረጠ ለንጉሡ ያቀርባል እንጂ፣ ንጉሡ እራሱ አይመርጥም የሚል ነበር::በጊዜው የመንግሥቱ የፕሮፓጋንዳ መሣሪያዎች ይህንን እንደትልቅ 'ለውጥ' እንደትልቅ 'እርምጃ' አድርገው ሊያቀርቡት ቢሞክሩም፣ ሕዝቡን በሚመለከተው በኩል ምንም ፋይዳ አልነበረውም::ነገሩ በገዥ መደቦች ውስጥ ለነበሩት የውስጥ ትግሎች እንደመፍትሄ የቀረበ እርምጃ ነበር::ሥርዓቱን ግን ከችግሮች አላዳነውም::

እንደሚታወቀው በሰኔ 1959 እሥራኤል የአረብ አገሮችን ወረረች::ከዚህ ወረራ በኋላ የስዊዝ ካናል ተዘጋ::የወጪው ንግድ እንደሚበላሸበት የተረዳው የኢትዮጵያ መንግሥት ወጪያውን በሕዝቡ ላይ ከዳር አስከዳር የገቢ ቀረጥ እንዲጨምር ለማድረግ የርሙ የጭማሪውን ዝርዝር ለፓርላማው አቀረበ::ፓርላማው ማቅማማትን ቢያይ ንጉሠ ነገሥቱ አባላቱን ጠርተ በቤተመንግሥት ማስጥ አድርገው ከሰደበቸው በኋላ፣ እርሱና ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ የመንግሥት ሚኒስትሮች ያቀረቡትን የሕግ አቀድ ወጪያውን ፓርላማው እንዲያጸድቀው አዘዘ::ፓርላማውም አጸደቀው::የዚህ የአዲስ ታክስ መጨመርም በየቦታው ሕዝባዊ ተቃውሞን አስከተለ፡

በዓመቱ መጨረሻ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ሠራተኞች ሀያ ጥያቄዎችን ለአሠሪያቸው ደርድረው ሥራ ቢያቆሙ፣ ቀጣሪው ሥራውን ዘጋባቸው፣ ማለት ወደሥራ እንዳይመለሱ ለማድረግ ሞከረ::ነገርግን የሠራተኞች አንድነት መጠንከሩ ለማንም ገልጽ ነበር::ስለዚህም ቀጣሪው ድልድል መቀበል የግድ ሆነበት::በዚሁ ጊዜ ያዲስአበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ማህበር ያንድነትና የድጋፍ ደብዳቤ በመጻፍ የአየር መንገዱን ሠራተኞች አበረታቷል::

የነአክሊሉ መንግሥት በግድ ፓርላማው እንዲያጸድቀው ያደረገው የታክስ ደንብ ከሁሉም በላይ ገበሬውን ያጠቃ የነበረ ነው::በዚህ መሠረት፣ በሚቀጥለው ዓመት፣ የመሬትን ግብር ለማሻሻል እንዲቻል ቶሎ በየቦታው ባለመሬቶች ይመዘገቡ የሚል ውሳኔ ተደረገ:: ይህ ውሳኔ በጎጃም ሕዝብ ዘንድ ያስከተለውን ተቃውሞ ሁሉ ኢትዮጵያ አውቆታል::የጎጃም ሕዝብ መሬታችንን አናስለካም አለ::በግንቦት 1960 ከሰባቱ የጎጃም አውራጃዎች አምስቱ በአንድነት አምጸው በመሣሪያ መንግሥትን መቋቋም ጀመሩ::መንግሥት ሠራዊትን ልኮባቸው ብዙ ጎጃሜዎች በቦምብና በመትረየስ ተጨፈጨፉ::ይሁን እንጂ ጀግናው የጎጃም ሕዝብ እስከ መጨረሻው ሰው ለመዋጋት ዝግጁ መሆኑ ቢታወቅ፣ ወታደሩ ጭፍጨፋውን እንዲያቆም ከተደረገ በኋላ፣መሬቱም ባይለካ ቀርቶ ጎጃምን የዘረፈው ፀሀፊ አንደምሳሌም ከጎጃም እንዲነሣ ተደረገ::ወደከፋ ተዘወረ ባበል፣ የጎጃም ሕዝብ እንዲህ ሲል ዘፈነ ይባላል:-

በግ ጎንደር፣ በግ ሸዋ....

ጎጃምን አሸረው ፣ ከፋ ከቦ ወጪ

1960ን ዓይነተኛ ከሚያደርጉት ሌሎች ትግሎች ያዲስአበባ ተማሪዎች የዝምባብዌን ሕዝብ በመደገፍ በሰላማዊ ሰልፍ አድርገው የእንግሊዝን ኤምባሲ ማጥቃታቸው፣ ያገሪቷን ባሕል ለማጥፋት በዩኒቨርሲቲ ሲደረግ የነበረውን 'የፋሽን' ትርኢት መደምሰሳቸው፣ በዚያውም ለዚህ ሀላፊ የሆነውን ያሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም በመቃወም ያሜሪካንን የፕሮፓጋንዳ መደብር-ዩኤስአይኤስ ን መደብደባቸው፣ እንዲሁም ሎሌዎቹን ሊጎበኝ የመጣውን ያሜሪካኑን ምክትል ፕሬዚዴንት ማባረራቸው ነው::በዚህ ሰውዬ ጉብኝት ጊዜ ያዲስአበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የጆንሰንን ቅርጽ ሠርተው ከሰቀሉ በኋላ በማቃጠል ከቪየትናም ሕዝብ ጋር ያላቸውን አንድነት ገልጸዋል::ይህንን ሁሉ በመመልከት፣ መንግሥት በመጋቢት ወር 1960 ብዙ ተማሪዎች ይዞ አሰረ፣ ዩኒቨርሲቲውን ዘጋ፣ የተማሪ ማህበርንና መጽሄታቸውን ከለከለ::



በጠቅላላው፣ 1960 በተፋፋመ የሕዝብ ትግል አለፈ::በዓመቱ መጨረሻ ንጉሠ ነገሥቱ በባሌ፡ በኤርትራ፡ በቦረናና በሌሎችም ቦታዎች የገጠሩን ሕዝብ የጨፈጨፉትን የጦር መኮንኖችንና በየከተማው ተማሪውንና ወዛደሩን የደበደቡትን ፖሊሶች ኒሻን በኒሻን አድርገ አሰናበቱ::ይህ እራሱ ለኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል መፋፋም ጥሩ ምክር ሆነ::

## 1.3. 1961–62::የፋሺስታዊ አመጽ ዓመታት

ከየካቲት 1961 እስከ ታህሣሥ 1962 ያለው ጊዜ፣ በኢትዮጵያ፣ ታላቅ ሕዝባዊ ትግል የታየበትና ሥርዓቱም ፍጹም ፋሺስታዊ አመጽን የፈጸመበት የታሪክ ወቅት ነበር::በዚህ ጽሁፍ ውስጥ ለዚህ ወቅት ለራሱ አንድ ምእራፍ የሰጠነው በዚህ ምክንያት ቢሆን፣ ይህ ወቅት ወደፊት በዝርዝር ሲጠና ብዙ አሁን የማይታዩንን ታሪካዊ እውነቶች እንደሚያወጣ ፈጽሞ አይጠረጠርም::

በየካቲት 1961፣ በደብረብርሃን፣ የሀይለማርያም ማሞና የዘርዐ ያዕቆብ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች፣ ሁለት በተማሪዎች የተወደዱ አስተማሪዎች ያለአግባብ ከሥራ መወገዳቸውን በመቃወም በከተማው ውስጥ በሰላማዊ ሰልፍ አደረጉ::በዚሁ አጋጣሚ መንግሥት ያወጀውን የትምህርት ታክስ ጭማሪም መቃወማቸውን ገለጹ::መንግሥት በተማሪዎች ላይ ፖሊስ ልኮ አስደበደባቸው::በዚህ ሁኔታ ተማሪዎች በከተማው ያለውን የንግድ ባንክ፡ አሥርቤትንና የባለ ጸጎች ሀብት የሆነውን የሱፍ ፋብሪካ ወገሩ::ፖሊስ በተማሪዎች ላይ ተኩሶ ሽፈራው በበደ የሚባል ተማሪ ተገደለ::ከዚህ በኋላ እንቅስቃሴው ወደአዲስአበባ ተዛወረ::በመጋቢት ወር ላይ ያዲስአበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የደብረብርሃንን ድርጊት በማውገዝ ትምህርት ለማቆም ወሰኑ::

'መትረየስ ደገኑ' በሚለው ባንዱ ጽሁፋቸው ውስጥ፣ ያዲስአበባ ተማሪዎች የኢትዮጵያ የትምህርት ይዘት በጠቅላላው ውጥንቅጡ የወጣ መሆኑን ከገለጹ በኋላ፣ እንደዚሁም በዚሁ ጸመትመጨረሻ የ12ኛ ክፍልን ፈተና ከሚቀበሉት 12 ሺ ተማሪዎች 11 ሺው እንደሚወድቁ በቅድሚያ የታወቀ መሆኑን ከመለከቱ በኋላ፣ በመጨረሻም ከ12ኛ ሆነ ከ8ኛ ወይም ከ6ኛ ወድቀው የሚቀሩትን ወጣቶች፣ ወንዶችን ሥራአጥነት፣ ሴቶችን ደግሞ ሽርሙጥና የሚጠብቃቸው መሆኑን ከጠቀሱ በኋላ፣ ለመንግሥት የሚከተሉትን ድርድሮች አቀረቡ:-

'ወደትምህርት ገበታ የምንመለሰው ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ስድስት ድርድሮች ሲፈጸሙልን ብቻ መሆኑን የኢትዮጵያ መንግሥት እንዲያውቅልን እንፈልጋለን:-

1::ለዚህ ሁሉ የትምህርት ይዘት መዛባት ከንጉሡ ቀጥሎ ተጠያቂው የትምህርት ሚኒስትሩ አቶ አካለወርቅ ሀብተወልድ ስለሆነ በቶሎታ ከሥልጣን ወርዶ ቅንነትና ችሎታ ባለው ሰው እንዲተካ፣

2፡፡ በያመቱ 3000 ስኮላርሺፕ ያህል ከውጭ መንግሥታት ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሚሰጥ ቢሆን ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በተገቢ መንገድ እየተመረጠ የተሰጠውን ስኮላርሺፕ በሙሉ እንዲጠቀምበት የማያደርግ ውሳኔ ሲወጣና በስኮላርሺፑ ዲሬክተር በአቶ ተድላ ምትክ ሌላ ትክክለኛ ሰው ሲተካ፣

3፡፡ በወላጆች ኮሚቴ አማካይነት የሚሰበሰበው 10 ብር ሲታገድና ለ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና የሚከፈለው ገንዘብ እንዲቀር ሲደረግ፡፡ በፈተና 3 ብር፡፡

4፡፡ ከኤርባሲዎች፣ ከነብዞ፣ ከሹርሹርና ከሚኒስትሮች ደሞዝ ቀንሶ፣ በማያስፈልጉ የቅንጦት እቃዎች ላይ ታክስ ጨምሮ ለትምህርት የሚደለደለውን በጀት ከፍ በማድረግ የሚወድቁት ልጆች በዛት የሚቀነስበት መንገድ ሲዘጋጅ፣

5፡፡ የቤቶችን ሕግ በመገሰስ የታወቁት፣ በጉብ አገራችን የገቡት ልክስክስ ህንዶችና በልገና ብቻ የሚያስጠኑት የአሜሪካን 'የሰላም ጓዶች' በአስቸኳይ ተባርረው በነርሱ ፈንታ የተሻሉ መምህራን የሚገኙበት መንገድ ሲወሰን፣

6፡፡ በደብረብርሃን በፋሺስታዊ ግፍ በመንግሥቱ ፖሊስ ለተገደለው ሺፈራው ከበደ ለተባለው ልጅ ቤተሰቦች የደም ዋጋ ሲከፈልና የአውራጃው ፖሊስ አዛዥና አገረገዢው ደጃዝማች ተስፋዬ እንቁሥላሴ ከሥልጣን ታግደው በነፍሰገዳይነት ወንጀል ለፍርድ ሲቀርቡ፣

እነዚህን ስድስቱን ድርድሮች ባናስፈጽም ትግበረችን አይታጠፍም፡፡

ከእንግዲህ ወዲህ እንደሕጻን አንታለልም፡፡

የአብዮታችን ጀግንነት በኛም ደም ስር ውስጥ እንደሚዘዋወር የምናስመሰክርበት ጊዜ አሁን ነው፡፡

በጥቂት ጅቦች በግፍ የተነጠቀውን የገበሬውንና የወዛደሩን የኢትዮጵያን ሕዝብ መብት ለማስከበር በወሰድነው ቆራጥ እርምጃ አንዲት ስንዝር አናፈገፍግም፡፡'

ከነዚህ ድርድሮች በኋላ፣ መጋቢት 25 ቀን፣ ወታደርና ፖሊስ ከእግር ጭፍራ እስከ ራስ ጠጉሩ ታጥቆ በከተማው በአዲስአበባ ውስጥ ዋና ዋናዎችን ቦታዎች ሲይዝ፣ የክብር ዘበኛ ደግሞ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ በግድ ገብቶ ተማሪዎችን ከተኙበት እየቀሰቀሰ አስወጥቶ ከዩኒቨርሲቲው አባረረ፡፡ የዚያን ለት በከተማው በሙሉ ፖሊስና ተማሪ፣ እንዲሁም ተማሪውን ለመርዳት ከጎኑ የተሰለፈው ሥራአጥ በሙሉ ሲጋጭና ሲደበደብ ዋለ፡፡ ብዙ ሺህ ተማሪዎች ተይዘው ገሚሱ ወደሰንዳፋ ገሚሱ ወደኮልፌ ተላኩ፡፡ ወደሰንዳፋ በማክ መኪና ተጭነው ሲወሰዱ ከነበሩት ተማሪዎች ውስጥ አንዱ፣ ደመቀ ዘውዴ 'ከመኪና ወድቆ' ሞተ፡፡ በማግሥቱ፣ መጋቢት 26 ቀን ተማሪዎች የደመቀ ዘውዴን ቀብር ለማክበር ሲፈልጉ፣ የመንግሥቱ ፖሊሶች እንደገና ብዙዎችን አፍሰው ወደማጎሪያዎች ወሰዷቸው፡፡ በበኩላቸው የዩኒቨርሲቲ አስተማሪዎች መዘጋት በመቃወምና ወዲያውኑ እንዲከፈት በመጠየቅ፣ የተማሪዎች መያዝና መታሰር ሕገወጥ መሆ



ኑን አመልክተው በመቃወምና ለወደፊቱ የዚህ ዓይነቱ ድርጊት እንዳይደገም በማመልከት አቋማቸውን ገለጹ፡፡ ይህንን አቋም ይዘው ንጉሡ ፊት ሲቀርቡ፣ ንጉሡ በተለመደው ፈላጭቆራጭነቱ ጥያቄዎቻቸውን ሳያዳምጥ፣ 'ተማሪዎቻችሁን ግብረገብነት አስተምሯቸው' ብሎ በደብ መለሰ፡

በ1960 በሕዝቡ ላይ ጨምሮት የነበረውን ታክስ ሕዝቡ ፈጽሞ እንዳልተቀበለው፣ የኤርትራ፣ የባሌና የጎጃም ሕዝቦች መደብደብና በሠራዊት አገዛዝ ስር መውደቅ መድረሱን ሰምቶ ሕዝቡ ማጉረምረሙን ያወቀው የኢትዮጵያ መንግሥት፣ በየካቲት—መጋቢት 1961 በሬ የሕዝብ አመጽ ይነሣብኛል ብሎ ፈርቶ እንደነበረ ግልጽ ነው፡፡ ከተማውን በሙሉ በሠራዊት ማስያዙ የፍርሃቱ ምልክት ነበር፡፡ ተማሪውን እንደዚያ ያለርሀራኄ ማስደብደቡና ወስዶ ማጎሩ የዚህ የፍርሃቱ ምልክት ነበር፡፡ ነገርግን የተርበደበደው መንግሥት በነዚህ ፋሺስታዊ እርምጃዎች ከፍርሃቱ አልተላቀቀም፡፡ ስለዚህም፣ ባይውል ባያድር ወዲያውኑ ፍጹም ፋሺስታዊ የሆነ ሌላ አዋጅ አወጀ፡፡ ይህ አዋጅ በቀጥታ ከደቡብ አፍሪካና ከጽዮናውያን የተቀዳ ቀጥታ ፋሺስታዊ አዋጅ ነው፡፡ እርሱም በነጋሪት ጋዜጣ ቁጥር 13፣ መጋቢት 27 ቀን 1961 የወጣ ሲሆን፣ የሚከተሉትን አንቀጾች በውስጡ ይዟል፡—

'3 ሀ. ለሕዝብ ፀጥታ ጥበቃ፣ ደህንነትና ሰላማዊ ኑሮ አስፈላጊ መሆኑን የአገር ግዛት ሚኒስትራችን ለማመን በቂ ምክንያት ካለው ማናቸውም ሰው ከዚህ በላይ በአንቀጽ 2 የተመለከተውን ግዴታ እንዲገባ ሳይጠየቅ (ግዴታው ዋስ የመጥራትና ገንዘብ የማስያዝ ነው) በተወሰነ ቦታ ከሦስት ወር ለማይበልጥ ጊዜ ተይዞ እንዲቆይ በራሱ ፊርማ በሚሰጥ የጽሁፍ ትእዛዝ የፖሊሱን ጠቅላይ አዛዥ ለማዘዝ ይችላል

ለ. የመጀመሪያዎች ተይዞ የመቆየት ሦስት ወራት ከተፈጸመ በኋላ ለሕዝብ ፀጥታ ጥበቃ፣ ደህንነትና ሰላማዊ ኑሮ የተያዘው ሰው ባለበት ቦታ እንዲቆይ መደረጉ አስፈላጊ መሆኑን ያገር ግዛት ሚኒስትራችን ለማመን በቂ ምክንያት ካለው ይዞ የማቆየቱ ጊዜ ለሌሎች የየሦስት ወራት ጊዜ ሊቀጥል ይችላል፡፡ ስለሆነ ግን ጠቅላላው ተይዞ የመቆየው ጊዜ ይህ ትእዛዝ ጸንቶ ከሚቆይበት ጊዜ መብለጥ የለበትም፡

4 ሀ. የፖሊስ ጠቅላይ አዛዥ፣ አንድ የመሰብሰቢያ ሥፍራ የሀይል፣ የማስፈራራት ወይም የሕዝብን ጥቅምና ደህንነት የሚያታርግ ተግባር የሚሠሩ ሰዎችን ለሚያበረታታ ወይም ለሚረዳ ማህበር አገልግሎት የሚውል መሆኑን ለማመን በቂ ምክንያት ካለው፣ ይህን የመሰለው የመሰብሰቢያ ስፍራ ይህን ለመሰለው አገልግሎት እንዳይውል በጽሁፍ ለመከልከልና ይህንኑ ተስማሚ በሚመስለው ረገድ ተጠርጣሪዎች ሰዎች ሁሉ እንዲያውቁት ለማድረግ ይችላል፡፡

ለ. ይህን ትእዛዝ በእምቢተኛነት ወይም በቸልተኝነት የማያከብር ሰው በዚህ ትእዛዝ ቁጥር 3 ላይ በተመለከተው መሠረት በአገር ግዛት ሚኒስትራችን ትእዛዝ ተይዞ እንዲቆይ ማድረግ ይቻላል::' (ትንሳኤን ቁ.3፣ ግንቦት–ሰኔ 1961)

መንግሥቱ ይህንን ፋሺስታዊ 'ትእዛዝ' ያወጣው፣ በገዱ በኩል ተቃውሞውንም በሕግ የሚሠራ ለማስመሰል ሲሆን፣ ዋናው ዓላማው ግን ተቃዋሚዎችን ለማስፈራራት ይጠቅማል በሚል እምነት ላይ የተመሠረተ ነበር::ለማንኛውም፣ ትእዛዙን እንዳወጣ ወዲያውኑ አንዳንድ ከውጭ አገር የተመለሱ ምሁራንንና አንዳንድ ያዲስአበባን ዩኒቨርሲቲ የተማሪ መሪዎች ያዘ:: ወዲያውኑም ከስድስት ወር እስከሰባት ዓመት ተኩል በእስር እንዲቆዩ ወሰነባቸው::ይሁንናም እነዚህ የምርዐቱ ተቃዋሚዎች የሕዝቡን ድጋፍ እንዳገኙ በማየት መንግሥቱ በነሀሴ ወር 'ምሕረት' አደረገላቸው::

በዚህ በየካቲት–መጋቢት 1961 ውስጥ የተማሪው ትግል በታላቅ ግለት እንዲነሣሣ ካደረጉት ምክንያቶች አንዱ — ምናልባትም ዋናው — የትምህርት ሁኔታ ነበር::ተማሪዎችም ከተሰለፉባቸው በሌዳዎች አንዱ 'ትምህርት ለሁሉ' የሚል ነበር::በትምህርት በኩል ይህ ዓመት ከሌሎች ለየት ያለ ነበር::አንደኛ ነገር፣ ከ1955 እስከ1960 ባለው ጊዜ ውስጥ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ቁጥር በያመቱ ከፍ ይል የነበረው ከ31 እስከ 38 ሺ በሚሆኑ ተማሪዎች ሲሆን፣ በ1961 ግን — ለጊዜው ለኛ ባልታወቀ ምክንያት — ይህ ቁጥር በድንገት ወደ 60 ሺ ከፍ አለ::ይህም ከፍተኛ ጭማሪ ለመንግሥቱ ችግሮችን እንደፈጠረ ግልጽ ነበር::ሁለተኛ ነገር፣ በዚሁ ዓመት የ12ኛን መልቀቂያ ፈተና ይቀበላሉ ተብለው ይጠበቁ የነበሩ ተማሪዎች ቁጥር ለመጀመሪያ ጊዜ 12 ሺ ሲደርስ፣ ከነዚህ ውስጥ፣ ከዚህ በላይ እንደተባለው ሁሉ፣ 11 ሺው እንደሚወድቁ በቅድሚያ ታውቆ ነበር:: ይህንኑም የትምህርት ሚኒስቴር በይፋ ገልጾት ነበር::ሦስተኛ ነገር፣ በዓመቱ መጨረሻ ፈተናውን የወሰዱት 12 ሺ ሳይሆን 3 ሺ 552 ብቻ ነበሩ::ከነዚህም ውስጥ ፈተናውን ያለፉ የተባሉት 738 ብቻ ሆኑ::ዞሮ ዞሮም 11 ሺ 262 ተማሪ ፈተናውን እንደወደቀ ተቆጠረበት::እንግዲህ በዚህ ዓይነቱ ሁኔታ የተማሪዎች አስቸኳይ 'ትምህርት ለሁሉ' የሚል የትግል መመሪያ መያዝ ምን ያህል የጊዜው ጉዳይ እንደነበረ ለመረዳት ይቻላል:: (ለነዚህ ዜናዎችና ትንተናዎች፣ ትንሳኤን፣ ልዩ ቁጥር፣ ነሀሴ 1961፣ ገጽ 66–67)

በመጋቢት ወር የኢትዮጵያ ተማሪዎች ያደረጉትን ትግል ሙሉ በሙሉ በመደገፍ፣ በውጭ አገር የሚገኙት የኢትዮጵያ ተማሪዎች የመንግሥቱን ኤምባሲዎች ያዙ::በሁለት ቀኖች ውስጥ፣ በተቀናበረ አኳኋን፣ በስቶክሆልም፣ በመስኮብ፣ በፓሪስ፣ በዋሽንግተንና በሎንዶን ያሉት ኤምባሲዎች ተያዙ::ይህም ድርጊት በዓለም ጋዜጦች በሬ ትችትን ስላገኘ፣ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል ለዓለም ሕዝቦች ሊታወቅ ችሎአል::እንግዲያውም በሀምሌና በነሀሴ ወሮች



የምእራብ ጋዜጦች እራሳቸው የሀይለሥላሴ መንግሥት ወቷኛና ጊዜው ያለፈበት የጌልተኛ መንግሥት መሆኑን፣ ይህም ሥርዓት ዴሞክራሲንና ልማትን፣ መሻሻልንና የወደፊት እርምጃን ለማምጣት አለመቻሉን እየገለጹ በመንግሥቱ ላይ ዘመቻ በሰፊው ያደርጉ ጀመር::እንዲያውም ከዚህ እያያዙ፣ ምናልባት አሜሪካኖች ፈረስ ለመለወጥ በማሰብ ሀይለሥላሴን ለመገልበጥ አስበው ይሆናል የሚል ጥርጣሬ ነበር::

በዚህ፣ ሥርዓቱ በተወጠረ ሁኔታና በተደናገጠ አከባቢ ተውጦ ባለ፣ ንጉሠነገሥቱ በሀምሌ ወር የተለመደውን የመሣሪያና የገንዘብ እርዳታ ለመለመን ወደአሜሪካ ሄዱ::ተደምብሎ በመጋቢት ወር መጨረሻ ላይ አንዳንድ የቼኮዝሎቫኪያና የሶቭየት ሕብረትን ዲፕሎማቶችን ከአገር በማስወጣት፣ 'ኮሙኒዝም ለኢትዮጵያ አደጋ ሆኗል' የሚለውን ከንቱ ወሬ የበላይ ጠባቂው ያሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም እንዲያምንለት ለማድረግ ሞክሮ የነበረው መንግሥት፣ እስከዋሽንግተን ሄዶ ያደረገው ልመና ያለውጤት ቀረ::ያሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም በዚያን ጊዜ ለራሱ በኢንዶቻይና ተወጥሮ ተይዞ ስለነበር፣ የመሣሪያም ሆነ የገንዘብ እርዳታ ለንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ለመስጠት ሁኔታው አልፈቀደለትም ነበር::ንጉሡ በዚህ አኳኋን አፍሮ ባዶ እጁን ወደቤት መመለስ የግድ ሆነበት::

መሣሪያው የተፈለገው በዚያን ዓመት ተስፋፍቶ የነበረውን የኤርትራ ሕዝብና የባሌ ሕዝብ ትግል ለመደምሰስ ነበር::እንደሚታወቀው፣ እስከ መጋቢት — ግርች — 11 ቀን የኤርትራ ነጻነት ግንባር ተዋጊዎች የኢትዮጵያ አየር መንገድን አውሮፕላን ፍራንክፈርት ላይ በቦምብ መትተውት ትልቅ ጉዳት አደረሱበት::ከሁለት ወሮች በኋላ የዚሁ ዓይነት ድርጊት በካራቺ ተደገመ::ቀጥሎም በነሀሴ ወር የግንባሩ ሰዎች አንድ አውሮፕላን ጠልፈው ወደአደን ወሰዱ::በነዚሁ ወራት ውስጥ ግንባሩ ትግሉን በማጠንከር ያስመራን የውሃ ቧንቧዎች ቆረጠ፣ አንዳንድ የፖሊስ ጣቢያዎችን አጥቅቶ ብዙ መሣሪያ ቀማ፣ አንዳንድ የቤንዚን ማጠራቀሚያዎችን አፈነዳ::በነሀሴ ወር፣ ግንባሩ በሁለት ሳምንቶች ውስጥ 113 መኮንኖችንና ወታደሮችን እንደገደለ አስታወቀ::

በዚሁ በነሀሴ ወር ሰባት ተማሪዎች አንድ አውሮፕላን ጠልፈው ከርቱም ገቡ::

በዚህ ሁኔታ፣ መንግሥቱ በመላ ኢትዮጵያ፣ በተለይም በአዲስአበባና በአስመራ ፀረ አረብ ሰላማዊ ሰልፎችን በማዘጋጀት ትልቅ ጋጋታ ለማድረግ ከመሞከሩም በላይ፣ በኤርትራ የነበረውን ጦር ከ2000 ወደ 8000 ወታደር ከፍ አደረገው::

በበኩሉ፣ በዚሁ ዓመት የባሌው ውጊያ በጣም እይሉ ነበር::በዋቆ ጉቶ ይመራ የነበረው ይህ ውጊያ በዘመናዊ ጠመንጃዎችና በፈንጂዎች በመጠቀም፣ በባሌ የሰፈረውን ጦር ደጋግሞ አጥቅቶ የመንግሥቱን ሠራዊት አስከማበረርና እንደነገሌ ያሉትን ከተማዎች ከወታደሩ ነጻ ለማውጣት የቻለበት ጊዜ ነበር::ያን ጊዜ እንደተነገረው ከሆነ፣ በ1960 በተደረጉት ውጊያዎች እስከ 10 ሺ የባሌ ሕዝብ ተዋጊዎች ተሰልፈው ነበር ይባላል::እንደሚታወቀው፣ በሚቀጥለው ዓመት የኢትዮጵያ መንግሥት ጃገማ ኬሎን ልኮ እነዋቆን እንዲደልል

ከደረገ በኋላ አቋቋሙን አስጠቶ፤ በዚህ በኩል ለጥቂት ጊዜ ፋታ ለማግኘት ችሎአል:: እነቀኝ አቋቋሙን ሲሰሙ ያስረከቡትን መሣሪያ ብዛትና ዓይነት የመንግሥቱ ጋዜጦች በዝርዝር አውጥተው ነበር::ከርሱ እንደሚታየው፤ የባሌ ሕዝብ ትግል በፖለቲካ ሳይሆን በትጥቅ በኩል በጣም ዳብሮ እንደነበር ግልጽ ነው::ግን ያለፖለቲካ መሣሪያ ምን ይሠራል ??

ለማጠቃለል ያህል፤ 1961 ለኢትዮጵያ መንግሥት የታላቅ ፈተና ዓመት ሆኖ ሲያልቅ፤ በሕዝቡ ትግል በኩል ግን፤ አንዳንድ ወደኋላ መመለሶች ቢታዩም፤ ትልቅ መሻሻሎችና አንዳንድ ውጤቶችንም አስገኝቶአል::በነሀሴ ወር መጨረሻ በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ከሉንድ አስከማልሞ፤ በስዊደን፤ ያደረጉት የሀያ ኪሎሜትር ሰላማዊ ሰልፍ የዓለምን ሕዝብ አስተያየት ወደኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል ለመሳብ ችሎአል:: 'መሬት ላራሹ': 'ጠላቶቻችን ፊውዳሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም ናቸው': 'የኢትዮጵያን ሕዝብ ትግል እንደግፍ' ... የሚሉት የትግል መፈክሮች ለአገርቤቱ አንቀስቃሴ ድጋፍ በመሆን አስተጋብተዋል::በዚህ ሁኔታ፤ ለኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል ፍሬያማ፤ ለአድሀሪው ሥርዓት ግን መጥፎ ዓመት የነበረው፤ ታሪኩ ገና ወደፊት መጻፍ ያለበት 1961 አለቀ::

1961 በትግል እንዳለቀ ሁሉ፤ 1962 ደግሞ በትግል ጀመረ::

ከነሀሴ 21 ቀን 1961 ጀምሮ ከጂማ፡ ከውጋዴን፡ ከነገሌና ከአሰመራ የመጡ የኮንጎ ዘማቾች ወኪሎች በአዲስአበባ ተሰብስበው፤ በመንግሥቱ እጅ ስለቀረባቸው ገንዘብ በሰፊው ተወያይተው ነበር::መስከረም 15 ቀን 1962፤ በአዲስአበባ ሰላማዊ ሰልፍ በማድረግ፤ የመንግሥቱ ባለሥልጣኖች አጭበርብረው የበሉባቸው ገንዘብ እንዲመለስላቸው ጠየቁ:: የነአክሊሉ መንግሥት ግን ፖሊስ ልኮ ወታደሮችን ካስደበደበ በኋላ፤ ብዙዎች በማክ መኪና ታጭቀው ወደማጎሪያ ሥፍራዎች እንዲላኩ አደረገ::ከዚህ ገና በኋላ፤ ትግላችን የሚተቀለውን፤ ከአራት ዓመታት በኋላ በየካቲት 1966 አንቀስቃሴ ውስጥ ያስተጋበውን ታሪካዊ ቃል ጽፎ ነበር:-

'ወታደር ቆብ ከመድፋቱ በስተቀር ከላብአደሩ ወገን የሚለይበት ነገር የለም:: ትናንት አበው አራሹ ገበሬ፤ ሸማኔ ወይም የቀን ሠራተኛ ነበር::ዛሬ ዘመዶቹ በሙሉ የዚሁ መደብ ክፍል ናቸው::ወታደር በሥራው ላይ ባለበት ጊዜ የዘራፊዎችን ጥቅም ለመጠበቅ በሚወሰደው እርምጃ የወገኖቹን ጠላትነት አፍርቶ፤ ጭቁንና ብዝበዛ እንገፍግፎት የተነሣውን ሰፊ ሕዝብ ለመደብደብ በየበረሃው ቢርቅ እንደኳንጫ ደርቶ፤ በጠቀሳሳ ኑሮው የሰው ልጅ መብት ተነጥቆ ይኖራል::ከውትድርናው ሲያበቃ ወጥቶ – በጡረታ ስም – ለይስሙላ እንጂ የሚሆን የኑሮ ዋስትና አይሰጠውም:: ታዲያ ለጥቂት ተበዋቾች ጥቅም ሲባል የገዛ ወገኖቹንና እህቶቹን የሚረግጠው ለምንድን ነው ? ተራ ወታደሮችና ዝቅተኛ መኮንኖች ጥቅማቸውም ሆነ ጉዳታቸው ከተቀረው ተበዝባዥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር አብሮ የሚሄድ እንጂ የሚለይ አይደለም. ወታደር፤ ገበሬና ሠራተኛ፤ ተማሪና ምሁር ተዋሃዱ !!!'
(ትግላችን ቁጥር 1፤ 1962፤ ገጽ 36–37)

በ1962 መጀመሪያ ላይ ትምህርት ቤቶች እንደገና ሲከፈቱ፤ ያዲስአበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ማህበርና መጽሔታቸው እንደገና ተፈቀዱ::በዚህ ሁኔታ ተማሪዎች ወደትምህርት ገበታቸው ተመልሰው በሰላም መሥራት እንደጀመሩ፤ የመንግሥቱ ጋዜጦች በተማሪዎች ላይ



ይዘምቱ ጀመር::ለዘመቻው መነሻ ምክንያት የሆነው በህዳር ወር በተማሪዎች መጽሔት፤ በታገል፤ የወጣው፤ የብሄረሰቦች መብት መከበር እንዳለበት የሚያስረዳ ጽሁፍ ነበር:: በህዳር 19፤ 20 እና 22 የወጡት አዲስዘመን፤ የዛሬይቱ ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ድምፅ ጋዜጦች ፍጹም ታይቶ በማይታወቅ አኳኋን በተማሪዎች ላይ በመውረድ፤ መንግሥቱ 'ጥብቅ እርምጃ' እንዲወስድባቸው ይጠይቁ ነበር::ያዲስዘመን አዘጋጅ በነበረው፤ በነጋሽ ገብረማርያም አስተያየት

'የተማሪዎች ዓላማ ... በአገሪቱ ውስጥ ብጥብጥ ማንሳት፤ አሁን ያለውን ሕግና የመንግሥትን አቋም ማፍረስ፤ ሃይማኖት መሻር፤ ያለውን ባሕልና ልማድ መሻር፤ የአገሪቱን የነገዶች የጎሣ አንድነት እንዳልነበረ ማድረግ ...' ነው

የዛሬይቱ ኢትዮጵያ አዘጋጅ የነበረው ከበደ አኒሳም:-

'አገር አንድ ናት፤ ልትነጣጠልና ልትከፋፈል አትችልም::አንድነቷን የሚያናጋ፤ ሥርዓቷን የሚያፋልስ፤ ባህሏን የሚያፈርስ ቢኖር የሕዝቦችዋ ጥቅም ተፃራሪ ነው: አገር አትሸጥም አትለወጥም:: ... ሕዝቡ አምኖ የተቀበለውን ሥርዓት ለመሻር በባዕድ አሳብ የሚሰነዝር፤ የቆየውንና የኖረውን ልማድ ሁሉ የሚያፈርስ፤ ሃይማኖትን የሚያቃልል፤ አበቶችን የሚያዋርድ፤ የተደነገጉትን ሕጎች የማይታዘዝ .... ዝንባሌው አደገኛ ነው::' ብሎ ጽፎአል::

((ይህ ሰውዬ ከአራት ዓመታት በኋላ፤ ወይ ሕሊናው በርግጥ ወቅሶት እንደሆነ፤ ወይንም ያ የተለመደው የትንሽከበርቴ አድርባይነቱ እንደሆነ አይታወቅም፤ ሚያዝያ 4 ቀን 1966 በወጣው አዲስዘመን እንደሚከተለው ይጽፋል:– 'ከአሥር ዓመታት ወዲህ የሕዝቡ አፈጉባዔ ሆነው በዱላና በጥይት ሲደበደቡ፤ በጋዝ ሲታፈኑ፤ ሲታሰሩና ሲሰቃዩ በግልጽ የተከራከሩት ተማሪዎች ብቻ መሆናቸውን እናውቃለን:: ...' !!!))

በበኩሉ፤ የኢትዮጵያ ድምፅ አዘጋጅ የነበረው ፍቅረሥላሴ ወልደሀና፤ 'ኢትዮጵያ አንድ ናት::አትከፈልም::አትነጣጠልም::ለዘለዓለም በአንድነቷ ትኖራለች:: .. ተማሪዎች ለኢትዮጵያ ሕዝብ ባህልና ልማድ ተፃራሪ የሆነ ጽሁፍ ማሰራጨታቸውንና መብታቸውን አሳረጡም' ካለ በኋላ፤ ዓይን ባይን ሲዋሽና ሲያወናብድ የሚከተለውን አስፈሪ ሀሰት ጽፏል

'አንዳንድ አገሮች በሰላም በማጣታቸው ጦርነት ባስከተለው ረሀብና በሽታ እጅግ በመረረ ስቃይ የሚሰቃዩ መሆናቸውን እንሰማለን::ኢትዮጵያ ግን በጸጥታና በሰላም የልማት ሥራዋን በማካሄድ ላይ ነች::የሚያስቀና እድል ነው::'
(ትግላችን ቁ. 1፤ 1962፤ ገጽ 1–10)

በዚህ አኳኋን የኢትዮጵያ መንግሥት ጋዜጦች በተማሪዎች ላይ ዘመቻ ለአንድ ወር ሙሉ ሲያደርጉ ቆይተው፤ በመጀመሪያ መንግሥቱ የተማሪዎችን ጋዜጣ ታገልን ከለከለ::ይህም አይበቃም ሲል፤ ሄራልድ የተባለው ጋዜጣ በቀጥታ ፋሺስታዊ እርምጃ በተማሪዎች ላይ እንዲወስድ ጠየቀ::እስከ በታህሣሥ 19 ቀን 1969 በወጣው ቁጥሩ ውስጥ፤ 'ባለፈው ሳምንት የተማሪዎችን መጽሔት በመከልከል የተወሰደው እርምጃ ትክክለኛውን አቅጣጫ የያዘ ነው: ይህ እርምጃ ወደ ተገቢ መደምደሚያው መቀጠል አለበት::' አለ::ይህ ሁሉ ዘመቻ ለአድሃሪው መንግሥት ወንጀለኝነት ቀርጊ ጉዳዩን ለማዘጋጀት የተጠነሰሰ ተንኮል እንደነበር የተከተሉት ድርጊቶች አሳይተዋል::

ተማሪዎች አገር ከፋፋዮች፣ ሃይማኖት አጥፊዎች፣ የውጭ እጅ አስገቢዎች፣ ወዘተ.
ብለው፣ አንድ ወር ሙሉ በመንግሥት ጋዜጦች፣ በሬዲዮና በቴሌቪዥን ዘመቻ ከተደረገ
በኋላ፣ በኖ ታህሣሥ 19 ቀን 1962፣ ከምሽቱ ሶስት ሰዓት ላይ፣ ገዥው መደብ ጥላሁን
ግዛውን የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ማህበርን ፕሬዚዴንት በነፍሰ ገዳዮች በግልጽ አስገደለ::
በማግሥቱ፣ ታህሣሥ 20 ቀን፣ የጥላሁንን የቀብር ሥነሥርዓት ለማክበር በተሰበሰቡ 25
ሺ ሰላማዊ ተማሪዎች፣ አስተማሪዎችና ሕዝብ ላይ ሠራዊት ተኩሶ ከሰላሳ በላይ ተማሪዎች
ሲሞቱ ከሁለት መቶ በላይ ሰዎች ቆሰሉ::በዚህ አኳኋን የሀይለሥላሴ—አክሊሉ መንግሥት
በገሃድ በዓለምና በኢትዮጵያ ሕዝቦች ፊት ፋሽስታዊ አመጹን ፈጸመ::

## 1.4. 1962—1965:: የጭቆናና የችጋር ዓመታት

የታህሣሥ 1962 ፋሽስታዊ ፍጅት በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ሲታወስ የሚኖር፣
የሀይለሥላሴን መንግሥት ወንጀል በግልጽ ያሳየ ድርጊት ነው::ይህ ሥርዓት አደጋውን ለማ
ራዘም ማንኛውንም አስፀያፊ ወንጀል ለመፈጸም ዝግጁ መሆኑን በገሃድ አሳየ::በሌላ በኩል
ግን ይህ ወንጀል አራሱ፣ ሥርዓቱ አስከምን ድረስ የኢትዮጵያን ሕዝቦች ሬቮሉሽናዊ መንፈ
ትና አንቅስቃሴ እንደፈራ በይበልጥ ገልጭ አድርጎ አሳይቶበታል::በመጨረሻም፣ የታህሣሥ
ፍጅት ያሳየው ዋናው ነገር፣ ከታህሣሥ 1953ቱ የገልበጣ ሙከራ በኋላ ተደራርበው የመጡ
በትን ችግሮች በፋሽስታዊ አመጽ ካልሆነ ሥርዓቱ በሌላ በምንም መንገድሊቋቋማቸው እንዳልቻ
ለ ነው::የኤርትራ ሕዝብ ትግል፣ የባሌ፣ የቦረና፣ የውጋዴን፣ ሕዝቦች ትግሎች፣ በከተማ
ም የወዛደሩና የተማሪው፣ የምሁሩ ትግል በዚህ ፋሽስታዊ አመጽ ምክንያት አልቆሙም::
እንዲያውም ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ ዘጠና በመቶው ያገሪቷ ነዋሪ ሥርዓቱን እንዲጠላውና
ትግሉን በየፊናው እንዲያፋፍመው አደረገው::

አድሃሪ ሀይሎች ከታሪክ የማይማሩት፣ ሊማሩ የማይችሉት አንድ እውነት ይህ ነው፣
በጸጥታና በሰላም ለመበዝበዝ እንዲመቻቸው ጭቆናቸውን ከፍ ባደረጉት ቁጥር፣ የሕዝቡም
ቁጣቸውና ተቃውሞ በዚያው መጠን፣ እንዲያውም በይበልጥ፣ ከፍ ይላል::ይህ ተቃውሞ ተፋፍሞ
ካንዱ ከተወሰነ ታሪካዊ ደረጃ ላይ ሲደርስ፣ የሕዝቡ ሬቮሉሽናዊ አመጽ የገዥ መደቦችን
ፀረሬቮሉሽናዊ አመጽ ይደመስስና አዲስ ሕብረተሰብ ይቋቋማል::ይህንን፣ ታሪክ ደጋግሞ
ያሳየውን እውነት፣ አድሃሪ ሀይሎች ምንጊዜም ቢሆን አይረዱትም::የኢትዮጵያ አድሃሪ ሥር
ዓትም የታህሣሥን ፍጅት ሲያካሂዱ፣ ከእንግዲህ ተቃውሞ የማይመጣበት፣ ሕዝባዊ ሀይሎች
የተደመሰሱበት መስሎት ነበር::ነገርግን በኤርትራም ሆነ በሌሎች የንጉሠነገሥቱ መንግሥት
ግዛቶች፣ በከተማም ሆነ በገጠር፣ በያቅጣጫው ትግሉ እየተፋፋመ እንደሄደ ሌላው ቢቀር
የዛሬው ደረጃው ይመሰክራል::



ከ1962 እስካለፈው ዓመት፣ 1965፣ የነበሩት ድርጊቶችና ትግሎች ሁሉ ትኩስ
ስለሆኑና የሚታወሱ ስለሆኑ እዚህ ላይ በዝርዝር አንመለከታቸውም::በጠቅላላው እነዚህን
ሶስት ዓመቶች ዓይነተኛ የሚያደርጋቸው የሥርዓቱ ጭቆና መባበስና በዚያም መጠን የተቃውሞ
መብዛት፣ የዘረፋው መባበስና የችጋር ባገሪቷ መግባት ናቸው::

በጥቅምት ወር 1963፣ የኤርትራ ተዋጊዎች ትግላቸውን በማጠናከር በአስመራና
በከረን መካከል ሁለት ድልድዮችን፣ በአጐርዳትና በተሰነይ መካከል ሁለት ድልድዮችን፣
በአጐርዳትና በከረን መካከል አንድ ድልድይ አፈረሱ::እንደዚሁም ህዳር 12 ቀን 1963
የሁለተኛ ክፍለጦርን አዛዥ ጄኔራል ተሾመ ኤርገቱና ተከታዮችን አጠፉአቸው::ይህንን
ምክንያት በማድረግ የኢትዮጵያ መንግሥት በኤርትራ ላይ አስቸኳይ አዋጅ አድርጎ በተለይም
የከረንን ከተማ በታላቅ ጭካኔ በአውሮፕላን አደብድቦ ከ500 የማያንሱ ሰዎች ገደለ::
ይህ ፋሽስታዊ ድርጊት በኤርትራ ብቻ ሳይሆን በውጭ አገር ባሉት ኢትዮጵያውያን ዘንድና
በዓለም ሕዝቦችም ዘንድ ትልቅ ተቃውሞን አስከትሏል::

በ1963 እና 64፣ በወሎ፣ በአሩሲ፣ በሲዳሞ፣ በትግራይና በሌሎችም ቦታዎች
የገበሬዎች አመጾች ተስፋፍተው ነበር::በወሎ ጠቅላይ ግዛት፣ በራያና ቆቦ አውራጃ፣ በአ
ላማጣ ወረዳ፣ ቆጆ ከሚባለው መንደር አጠገብ፣ ገባሮች የሚዘርፏቸውን ባለመሬታቸውን ደጃ
ዝማች ጉበና አመዴንና አሽከሮችን ገድለዋል::እንደዚሁም በዚሁ በወሎ ጠቅላይ ግዛት
በ1964 ወደ 600 የሚጠጉ ገበሬዎች አደም አረጋው በሚባል መሪ ስር አምጸዋል::በአሩ
ሲ ጠቅላይ ግዛት፣ በጭላሉ፣ ገበሬዎች መሬታቸውን የቀሟቸውን ሰዎች ሰብል በማቃጠል
ተቃውሞአቸውን አሳይተዋል::በሲዳሞ ጠቅላይግዛት፣ በወላሞ አውራጃ፣ ተማሪዎችና ሕዝቡ
ተባብረው፣ አገሬቸውን በመዝረፍና ሕዝቡን በመጨቆን የታወቁትን ባለሥልጣኖች በሕዝባዊ
ፍርድ ቀጥተዋቸዋል::በትግራይ ጠቅላይ ግዛት፣ በአጋሜ አውራጃ፣ ታላቅ የሕዝብ ንቅናቄ
በ1963 ተጀምሮ ነበር::ባጭሩ ብቻ፣ በገጠሩ በየቦታው የገበሬው ኑሮ በመቀርቀዙ፣ ዘረ
ፋውና ጭቆናው ከመጠን በላይ ስለበዛበት፣ ሕዝቡ ከማንኛውም ጊዜ ይበልጥ ታጋይ ሆኖ ቆየ:

በሌላ በኩል ደግሞ፣ በነዚህ ዓመታት ውስጥ በብዙው ገጠር ሀይለኛ ችጋር ገብቶ
ነበር::በ1965 ጁኝም ተርቦ፣ ከ10ሺ እስከ 20ሺ የሚሆን ሕዝብ ወደአዲስ አበባ ሊጎ
ርፍ ሲል፣ መንግሥቱ እህል እዚሁ ድረስ ይመጣላችኋል ብሎ ከአባይ ማዶ እንዳስቀራቸውና
በመጨረሻም ሁለት—ሁለት ብር በነፍስወከፍ ሰጥቶ እዚያው እንደገታቸው ታውቋል::

በከተሞችም ገን፣ እህል በማነሱና ዋጋ ወደሰማይ በመውጣቱ፣ የከተማው ነዋሪ በጣ
ም ተጨንቆ ቆየ::በመስከረም 30 ቀን 1963 የወጣው አዲስዘመን ጋዜጣ፣ 'በአንዳንድ
ጠቅላይ ግዛቶች እህል እየታጣ፣ ችግሩ ወደችጋር መለወጥ ይዞ ነበር::' ብሎ ጽፏል::
'ይዞ ነበር' በማለት ፈንታ 'ይዞአል' ቢል ሀቀኛ በሆነ ነበር::በበኩሉ እንደ በነሀሴ
16 ቀን 1970 የወጣው ሄራልድ የእህል ዋጋ ባንድ ዓመት ውስጥ በ25 በመቶ መጨመሩን

የሚያበዩ ምሕል ይዞ ነበር::በተረፈም፣ በሚያዝያ ወር 1963፣ በሩሲካ ሰዎን በአዲስ
አበባና በሌሎችም ከተሞች የቀበና የእህል ዋጋ ከሁለት እስከ ስስት እጅ የወረበት
ወቅት ነበር!!! ሠርቶአደሩ ሕዝብ ከሚራበበት ሁኔታ ላይ ደረሰ:: ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በከተማው ወጥተው ከፖሊሱ ጋር

በዚህን ጊዜ ነው ያዲስአበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በከተማው ወጥተው ከፖሊሱ ጋር
ከተቀን በኋላ የእህልና የቀበን ዋጋ ያስቀነሱት::የኋላ ኋላማ ተማሪዎች በዚህ ድርጊታቸ
ው የፖሊሱንና የወታደሩን ዱጋና ሰላገኙ፣ መንግሥቱ እራሱ እነርሱ ያስቀነሱትን ዋጋ ያጸ
ደቀው ጀመር::ይሁንናም፣ በ1963–64 ያዲስአበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በብዙ ሺህ አየ
ታሰሩ ወደጊቤ በረሃ፣ ወደጅጅጋ፣ ወደደብረማርቆስና ወደሌሎችም እሩቅ ቦታዎች ተወሰደው
በግድ የማይረባ የጉልበት ሥራ እንዲሠሩ ተደርገዋል::

የተማሪን ትግል በሚመለከተው በኩል፣ በታህሣሥ 1965 በሀይለሥላሴ መንግሥት
ነፍሰገዳዮች በአውሮፕላን ውስጥ በሩቢስታዊ ጭካኔ የተገደሉትን ዋለልኝ መኮንንን፣ ማርታ
መብራቱን፣ አማኑኤል ዮሐንስን፣ ጌታቸው ሀብቴን፣ ተስፋዬ ቢረጋንና ዮሐንስ በረታውን
ታሪክ ሲያስታውሳቸው ይኖራል::

ከ1961 እስከ 1962–63 የነበሩት የሕዝብ ትግሎች፣ ሲጠበቅ እንደሚችለው ሁ
ሉ፣ በገጠሩ መደብ ውስጥ ነትርኮችንና ትንንቶችን አስከተለው ነበር::በ1962 መጀመሪያ
ላይ መንግሥቱ አርበኛውን ታከለ ወልደሐዋርያትን አስገደለ::ቀደም ብሎ ደግሞ፣ በ1961
ውስጥ እነአበይ አበበ–አምሬተ ካሣ፣ የመሳፍንት መደብ፣ የነአከሊሉን የቢሮ ክበርቴ መደ
ብ በመቃወም፤ አያገኘነት ሚኒስትር የዚህኛው ወይንም የዚያኛው መምሪያ ቤት ወይንም ሩብ
ሪከ የቦርድ አባል ነኝ እያለ በየወሩ የሚያገኘው ገብ ይመርመር ብለው ጠይቀው ነበር::
ይህ ባይሆንላቸው ቢቀር፣ ዘርዝሩን እነርሱ አራባቸው አዘጋጅተው በፓርላማውና በከተማው
ውስጥ እንዲሠራጭ አደረጉ::ይህንን የወረቀት መበተን ሥራ ፈጽሟል የተባለውና ጥላሁን ገ
ዛውንም ያስገደለው እርሱ ነው ብሎ የተጠረጠረው ደጃዝማች አሉላ በቀለ፣ የነአምሬተ
ካሣ ወገን፣ በመጋቢት 1962 ተይዞ ታሠረ::የነአከሊሉ ሀብ ተወልዱ የቢሮ ክበርቴዎች
መደብ በነአምሬተ ካሣ የመሳፍንት መደብ ላይ የወሰደው ማስፈራሪያ እርምጃ መሆኑ ነው::

በገዢ መደቦች ውስጥ ያሉት ቅራኔዎች ብዙውን ጊዜ ሲፈቱ የኖሩት በኩዴታ ስለ
ሆነ፣ ነሀሴ 13 ቀን 1963 ገዥው ኩዴታ አደረገ::በዚህ ኩዴታ የነአከሊሉ–አካለወ
ርቅ የቢሮ ክበርቴዎች መደብ ተወናከሮ ሲወጣ፣ ሥልጣኑን ሲቀናቀነው የነበረው የነአምሬተ
የመሳፍንት መደብ ገን ተሸነፈ::ይህ በገዢው መደብ ውስጥ የነበረው ትግል በየካቲት አነ
ቀስቃሽ ምን ወሬት እንደነበረ ታይቷል::በዚህ ላይ ወደፊት እንመለስበታለን::

የኤርትራ ትግል፣ የገበሬ ሕዝብ ትግል፣ የሠርቶአደሩ የከተማ ነዋሪና የተማሪው
ትግል፣ በጨቀሳሰው የኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል በብሩትም በጥልቀትም ከ1962 እስከ 65
ወሰርሷል::ይሁንናም ዛሬ ከሁሉም በላይ በዚህ ወቅት ላይ ምልክት የሚለው የሰሜን
ኢትዮጵያ ታላቅ ረሀብ ነው::



ከዚህ በላይ በነጥብ ቦታ እንደተገለጸው ሁሉ፣ በጨቀሳሳ በገሪቷ ላይ ታላቅ ችጋር
እንደሚመጣ የዛሬ ስድስት ዓመት በቀደሚያ ታውቆ ነበር::ይህ በተነገረ በስስት ዓመቱና
ጉኝም መረቡ ከታወቀ በኋላ፣ ሌላው ቀርቶ የመንግሥቱ ጋዜጣ አዲስዘመን በመስከረም 30
ቀን 1963 በጻፈው ርእሰአንቀጹ የሚከተለውን ማስጠንቀቂያ አስፍሮ ነበር:–

> 'ካለፈው ሀናቴ – ኢክስፒሪየንስ – ተምረን ለወደፊቱ ተመሳሳይ ችግር እንዳይገ
> ጥመን፣ ዘዴውን በፍጥነት ማግኘት አለብን::የመጀመሪያው ጥረታችን፣ ከረሀብ ተርፈ
> ለመከላከያው ምሥረት 'የግብ ቀርጫት' ለመሆን በቂ የተፈጥሮ ሀብት ያላት አገራ
> ችን፣ በሰብል በኩል ራሷን እንድትችል ማድረግ ነው::ይኸንንም ለማድረግ፣ በዘመ
> ናዊ የእርሻ ይዞታ የሚዘጋጅ፣ ሰብሉ ሲያመች የሚከማች፣ ሲታጣ የሚወጣ፣ በተፈለ
> ገበት ወቅት፣ በተፈለገበት ሥፍራ ሊቀርብ የሚችል የእርሻ ሀብት የሚገኝበትን የ
> ኢኮኖሚ እቅም መፍጠር ነው::' (በትንሳኤን ቀ.2፣1963፣ ገጽ 9 የተጠቀሰ)

በወቅቱ፣ ትግሳችን፣ የችጋሩ ዋና ምክንያት ድርቀት ወይንም ሌላ የፍጥረት 'መቅሰፍት'
አለመሆኑን፣ ዋናው ምክንያት የመሬት ሥሪትና የጉልተኞች ሥርዓት ማህበር እራሱ መሆኑን፣
የኢትዮጵያ ሥርዓት የኢትዮጵያን ሕዝብ ከረሀብ ለማዳን በፍጥረቱ የማይችል መሆኑንና ለዘ
ላቂ መፍትሄ ዘላቂ ለውጥ መምጣት እንዳለበት አስረድቶ ነበር::ይህ ሥርዓት አሁንም በሳ
ለ፣ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ችግሮች አሁንም እንዳሉ ናቸው::

በሰሜን ኢትዮጵያ ከ1962 ቀደም፣ ለስስት–አራት ዓመታት እስከ1965 ድረስ
እንዳችም ዝናብ እንዳልወረደ የኢትዮጵያ መንግሥት ያውቅ ነበር::ከ1962 እስከ
1964፣ የወሎ፣ የደብብ ትግሬይና የሰሜን ሸዋ ሕዝብ ያለውን ሁሉ አሟጦ መብላት የገ
ደ ሆነበት::ከብት፣ መሬት፣ ያለ የሌለው ነበረት ሁሉ ተሸጦ የእህል መግዣ ለማድረግ
ተሞከረ::ሕዝቡ ይህንን ሁሉ ሲያይ ቢቀበል፣ መንግሥቱ እንዲት ጣት እንኳን እንሥቶ ሊረ
ዳ አልፈቀደም::እንዲያውም በ1963 በጉኝም ረሀብ በሐረርጌ ከሰራ እንደተስፋፋ ለመሸሸግ
እንደሞከረ ሁሉ፣ በ1965 ደግሞ የወሎን፣ የትግራይንና የሰሜን ሸዋን ድርቀትና በሕዝቡ
ላይ የደረሰውን አስፈሪ ረሀብ ለመሸሸግ ሞከረ::በግንቦት 1965 የደሴ ከፍተኛ ተማሪዎች
ሰላማዊ ሰልፍ አድርገው ስለድርቁ እቤቱታ ሲያቀርቡ፣ አገረገዢው ደጃዝማች ሰለሞን አበ
ተኩሰባቸው ወደአምሥራበበት የሚወጡ ተማሪዎች ተገደሉ::ቁጥራቸው ያልታወቁ ብዙዎች ቆሰሉ:

በዚሁ በግንቦት ወር የሰሜን ኢትዮጵያ ሕዝብ በየእለቱ በሺህ እየተቆጠረ ሲሞት፣
የሀይለሥላሴ መንግሥት ገን ለከተማው ማስጌጫ ብቻ አምስት ሚሊዮን ብር አውጥቶ፣ ያፍሪካ
አንድነትን አሥረኛ ዐመት በታላቅ ፌስታ ያከብር ነበር::ከመላ አፍሪካና ከመላው ዓለም
የመጡት ጋዜጠኞች ስለሰሜን ኢትዮጵያ ሕዝብ ሥቃይ አንዳች ነገር ሳይሰሙ በጭፈራው ተበት
ረው ወደያገራቸው ተመለሱ::የሀይለሥላሴ መንግሥት በዚህ አኳኋን በኢትዮጵያ ሕዝቦች ላይ
የፈጸመውን ወንጀል አንድ ቀን የኢትዮጵያ ሕዝቦች ይበቀሉታል::

በሰሜን ኢትዮጵያ የደረሰውን ታላቅ ረሀብ ለውጪው ዓለም ለማስታወቅ የቻሉት ያዲ
ስአበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችና አስተማሪዎች ናቸው::ይሁንናም፣ ከግንቦት 1965 እስከ

ጥቅምት 1966 ባለው ጊዜ ውስጥ፣ የወጪው ዓለም በጥቅምት ወር የረሀቡን ዜና እስከሰማበት ወቅት ድረስ፣ በዚህ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ መቶ ሺህ — 100 000 — ኢትዮጵያውያን በረሀብ አልቀው ነበር::የኢትዮጵያ መንግሥት ከ1965 መጀመሪያ አንስቶ የረሀብን መኖር ሲክድ ቆይቶ፣ ረሀቡ በርግጥ መኖሩን ያመነው በጥቅምት 1966 ብቻ ነበር:: ይህንንም ያደረገው ሁኔታው ከንገዲህ ሊሸሸግ ከማይችልበት ደረጃ ላይ ስለደረሰበት ነበር

በጥቅምት 1966 አንድ የንግሊዝ ጋዜጠኛ በወሎ ያነሣውን ፊልም በምዕራብ አገሮች አሳየ::በዚህን ጊዜ መላው ዓለም የሀይለሥላሴ መንግሥት የፈጸመውን ወንጀል ኮነነ:: ወዲያውም ከየቦታው የእህል፣ የመድሃኒትና የልብስ፣ የገንዘብ አንዲሰበሰብ ተደረገ::

የ1965ቱ የሰሜን ኢትዮጵያ ረሀብ በኢትዮጵያ ሕዝቦች ዘንድ አንደታወቀ፣ ለዚህ ለወንጀለኛ ሥርዓት ትልቅ ጥላቻን አሳድሮባቸዋል::በዚህ ፍጹም አሰቃቂ በሆነ ችጋር ከገዢው መደብ በስተቀር ልቡ ያልተነካ፣ ያልተናደደ፣ ያልጨሰ የሕብረተሰብ መደብ፣ ክፍል ወይም ነሰብ አልነበረም::ያልለማ አገር፣ ድሀ አገር፣ የተበዘበዘ አገር መሆን አንድ ነገር ነው፣ ነገርን ደግሞ በችጋር አንደቅጠል መርገፍ፣ ከሁሉ አነስተኛ የሆነችውን የአለት ጉርስ ማጣትና አሰቃቂ በሆነ ኢሰብአዊ ሁኔታ ማለቅ ደግሞ ሌላ ነገር ነው::የወሎን ሕዝብ ሁኔታ በፊልም ያዩት የዓለም ሕዝቦች ለሁኔታው ማመሳሰያ ያገኙት ምሳሌ ሂትለር አይሁዶችን ያጐረበትን የጋዝ ማረፊያ በረት ብቻ ነበር::

ይህንን ኢሰብአዊ ሁኔታ በኢትዮጵያ ሕዝቦች ላይ ያደረሰው ሥርዓት አሁንም አንዳለ አለ፣ ፈጽሞ አልተነካም::ይህ ሥርዓት ከመሠረቱ አስካልተለወጠና አዲስ ሕዝባዊ ሥርዓት በኢትዮጵያችን አስካልተቋቋመ ድረስ የዚህ ዓይነቱ ሁኔታ ተደጋግሞ መፈጠሩ አይቀርም አዲስ ሕዝባዊ ሥርዓት ካልተገነባ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ከረሀብ፣ ከመሃይምነትና ከበሽታ ሊላቀቁ ፈጽመው አይችሉም::

ከዚህ ተጥሰን የምንመለከተው የየካቲት 1966 የኢትዮጵያ ሕዝቦች ረቮሉሽናዊ አንቅስቃሴ ያንን ተፈላጊውን ሕዝባዊ ሥርዓት ሊያቋቁመው አልቻለም::በፍጥረቱም ይህንን ሥርዓት ሊፈጥረው አይችልም ነበር፣ አይችልምም::ይሁን አንጂ፣ ይህ አንቅስቃሴ አፊቱ የብዙ ትግሎች ወጪት ሆና ባለ፣ ለሌሎች ከፍተኛ ትግሎች መንገድ ከፍቷል፣ በመከፈት ላይ ነው::ከንገዲህ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ነቅተዋል፣ መልሶ ሊያስተኛቸው የሚችል አንዳችም ሀይል በዚህ ዓለም ላይ የለም፣ ሊኖርም አይችልም::ከንገዲህ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ሕዝባዊ ሥርዓትን በገዛ እጃቸው ለራሳቸው ለመገንባት የሚችሉበት ጊዜ ተቃርቧል::

---



## ምዕራፍ 2::የየካቲት አንቅስቃሴ ጥያቄዎችና ውጤቶች

> The times of that superstition which attributed revolutions to the ill-will of a few agitators have long passed away. Everyone knows nowadays that wherever there is a revolutionary convulsion, there must be some social want in the background, which is prevented, by outworn institutions, from satisfying itself. The want may not be felt as strongly, as generally, as might ensure immediate success; but every attempt at forcible repression will only bring it forth stronger and stronger, until it bursts its fetters.
>
> K. Marx. (1851)

በየካቲት 1966 መላ ኢትዮጵያን ከነገሌ አስከምጽዋ፣ ከጂጂጋ አስከጂማ ያንቀጠቀጣት የረቮሉሽናዊ አንቅስቃሴ ትኩሳት በገሪቷ ታሪክ ውስጥ ታይቶ የማይታወቅ፣ በሰፋትና በጥልቀቱ በሦስት ሺ ዓመታት የአበሻም ሆነ በመቶ ዓመት የኢትዮጵያ ሕይወት ውስጥ ተወዳዳሪ የሌለው ታላቅ የሕዝብ አንቅስቃሴ ነው::ምኒልክ በገነባው በዚህ የገዥ ነገሥት መንግሥት ግዛት ውስጥ ያሉትን መደቦች፣ የሕዝብ ክፍሎች፣ የሥራ ዓይነቶችና ሠራተኞቻቸውን፣ የመንግሥትና የግል ድርጅቶችን ሁሉ በሙሉ ኃይል ቀስቅሶ ከመደብ ትግል ወላፈን ውስጥ አስገብቷቸዋል::የየካቲት አንቅስቃሴ፣ ጌታንና ሎሌን፣ አዛዥንና ታዛዥን፣ ሀብታምን እና ደሀን፣ ጨቋኝንና ተጨቋኝን ፊት ለፊት አፋጠጠ::ከዚያም የተዳቀቁ ጥጋበኞች አቀርቀረው፣ ተሸሩፍነው አየተገላመጡ አንዲሄዱ፣ ተዲም የተረገጡት ደግሞ ቆመው፣ አንገታቸውን ቀና አድርገው በድፍረት ወደነጻነት ጎዳና አንዲያመሩ አደረገ::ተዲም ስማቸው ብቻ ቢነሣ ተጨቋኙ ሕዝብ የሚንቀጠቀጥላቸው 'አንበሶች' ዘሬ ቤተራቸው በተስለያን አንደገባች ውሻ ወዲያና ወዲህ ሲቁከቡ፣ ኩሽ በሉ ቶጥር የሚርበደበዱ ሆኑ::ተዲም በነዝት ፍራቻ ሕሊናቸውና ምላሳቸው ተለጉሞ ይኖሩ የነበሩት ዘሬ ዘረው 'ቀቺስን ብፁእን' ይሏቸው የነበሩትን ይገዝቱ ገቡ።

የየካቲት የኢትዮጵያ ሕዝቦች ረቮሉሽናዊ አንቅስቃሴ በኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ውስጥ ታምቀው ሲበሳሰሉ የኖሩት ሕብረተሰባዊ ቅራኔዎች ፈንድተው በገሃድ ባደባባይ አንዲደረደሩ አድርጓል::ጨሰኛው የቀማውን ባለመሬት መልስ ሊቀማው ተነሣ፣ ወዛደር ከበርቴውን ወጥሮ ይዞ መብቱንና ጥቅሙን አስከበረ፣ ትንሽ ከበርቴው የቢሮ ከበርቴውንና የጌልተኞችን ሥልጣን ከጃቸው ፈልቅቆ ሊወስድ ሆነ፣ የተጨቆኑ ብሄረሰቦች፣ ተጨቋኙ የእስላም ሃይማኖት፣

ተጨቋኞቹ ቤት፣ ሁሉም ብዱን በሰው ለመብታቸው የሞ፡፡ የሕብረተሰቦችን ቅራኔዎች በዓይነ የሚታዩ በጅ የሚዳበሱ ሆኑ ብነል ያስኬዳል፡፡ እንደየካቲት የገዥ መደቦችን ባንድ ወገን፣ ዘዴና በመቶውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ በሌላው ወገን፣ የሬተኞችን ሳብቻ ነጥሉ አጥ፣ እነዚሁናችን ደግሞ በሳሳ አቢጌንም ቢሆን፣ አስተባስሮ አሰወልና ያበየ አንቀስቃሴ በገራችን ታሪክ ውስጥ የለም፡፡

የየካቲት አንቀስቃሴ የኢትዮጵያን ሕዝቦች አንደገና በዓለም ታሪክ መድረክ ላይ በቁ አንጊሉ አድርጉአቸዋል፡፡ ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ፣ በሰላሳ ዓመት ውስጥ ያላገኙትን የፖለቲካ ትምህርት በቀቲት በሳምንቶች ውስጥ እንዲቀስሙ አድርጉአቸዋል፡፡

የኢትዮጵያ ወቀሳሳ የሕብረተሰብ ሁናቴ ሬቮሉሽንን የሚጠይቅ መሆኑን ይህ የየካቲት አንቀስቃሴ አስይቷል፡፡ አስከዛሬ በገዢዎቻችን ቢነዛ የነበረው፣ የተደረገውን ትግል ሁሉ የቀቲቶች የተነኮሰ ሥራ ሊያስመስል ቢፍጨረጨር የየየው ፍልስፍና አንገዓርጌ ገል ተሰብሯል፡፡ ለኢትዮጵያ ሕዝቦችም ለረሀባቸው፣ ለመላው ዓለምም ገልጽ ሆኖ የታየው፣ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ከዓር አስከዓር በፊውዳሎ–ቡርዧ ሥርዓት ላይ መነሣታቸው ነው፡፡ የተባለው ሥርዓት ጊዜ ያለፈበት፣ የበሰበሰ፣ ያገረጀ አድገትና የወደፊት እርምጃ አፍኖ የያዘ አንደሆነ ለዓፀቀ ለኢትዮጵያ ሕዝቦች ከነገዚህ ሌላ ምስክር አያስፈልጋቸውም፣ አነርሱ ራሳቸው በገዛ ድርጊቶቻቸው ተገንዝበውታል፡፡ ምናልባት በጥብቅ ያልተገነዘቡት ነገር ቢኖር ይህ ሥርዓት አንደምን ተወርን መጥፋት አንዳለበትና በቦታው ሌላ ምን ዓይነት አዲስ ሥርዓት መተካት አንዳለበት ነው፡፡ ገን ይህም በተራው ይመጣል፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግሉን ጀመሩት አንጂ ገና አልፈጸሙትም፡፡

አንዳንድ የውጭ አገር ጸሀፊዎችና የኛም አንዳንድ ምሁራን የየካቲትን አንቀስቃሴ እአአ. በ1905 በሩሲያ ከተደረገው ዲሞክራሲያዊ ሬቮሉሽን ጋር ከሁኑ ለማመሳሰል ሞክረዋል፡፡ የሁለቱ አገሮችን ታሪክ ማመሳሰልና የሚገኘውን ትምህርት አጥርቶ ማወቁ ተገቢ ነገር ቢሆንም፣ የዚህ ዓይነቱ ድርጊት ጥንቃቄን ይጠይቃል፡፡ በተለይም፣ ያንዱን አገር መልኮችና ሁኔታዎች ወደ ሌላው ሳይ የመለጠፍ አደጋ አለ፡፡ አንዳንድ የኛ ምሁራንም ከሁኑ የዚህን ዓይነት ስሕተት በማድረግ ጽፈዋል፡፡ እነዚህን ለጊዜው ወደጎን ትተናቸው፣ የ1905 የሩሲያ ዲሞክራሲያዊ ሬቮሉሽንና የየካቲት እንቅስቃሴ አስከምን ድረስ እንደሚመሳሰሉ በጭሩ ብንመለከት ይጠቅማል፡፡ (ይህንን የሩሲያን ዲሞክራሲያዊ ሬቮሉሽን ታሪክ በዚህ ጽሁፍ መጨረሻ በጣም በጭሩ አስፍረናል፡፡) እነገዚህ ሁለቱ አስከምን ድረስ ይመሳሰላሉ?

መጀመሪያ ነገር፣ የ1905ቱ ሬቮሉሽን በሚደረግበት ወቅት፣ ምንም አንኳን አሁንም የሀብታም ገበሬዎችና የትላልቅ ባለመሬቶች የቀን ሠራተኞችና የነርሱም በስአላ ቢሆንም፣ እአአ በ1861 ጪሰኝነት በሕግ ቢከለከል፣ በሬው የሩሲያ ገበሬ መጠነኛ ነጻነትን አገኝቶ ነበር፡፡ ከ1861 አስከሬቮሉሽኑ ባሉት 45 ዓመታት ውስጥ የከበርቴ ኢኮኖሚ –



ፋብሪካዎች፣ ንግድ፣ መገናኛዎች፣ በተለይም የምድር ባቡር፣ ወዘተ. – በሩሲያ በፈጣን እርምጃ በመስፋፋት፣ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ወዛደር ተፈጥሮ ነበር፡፡ እአአ. በ1900 ገደማ በማእድን፣ በምድር ባቡርና በፋብሪካዎች ብቻና ደግሞ በውሮፓው ሩሲያ ብቻ 2 ሚሊዮን 207 ሺ ወዛደሮች ነበሩ፡፡

ይህንን የወዛደር መደብ እአአ. በ1883 የተቋቋመው 'ወዛደርን ነጻ ለማውጣት' የተባለው የሩሲያ ሬቮሉሽናውያን ከባብና ከርሱም በኋላ፣ ከ1898 ጀምሮ የሩሲያ ሶሻል–ዲሞክራቲክ ፓርቲ ያስተምሩትና ያደራጁት ነበር፡፡ በመጨረሻም፣ ምንም አንኳ ቢጀምር የፖለቲካ አመራር ያልነበረው ቢሆንም፣ የ1905ቱ ሬቮሉሽን ወደማለቂያው ላይ የፖለቲካ ፓርቲዎች አመራር ነበረው፡፡

የየካቲቱ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ሬቮሉሽናዊ አንቀስቃሴ በነዚህ ሁሉ ነጥቦች ከሩሲያው ሬቮሉሽን በጣም የተለየ ነው፡፡ ጪሰኝነት ገና ከገራችን ባለመጥፋቱ – ወይንም ቢያነስ ባለመቀነሱ – የከበርቴ ሥርዓት ቢኖርም በጣም አልተስፋፋም፣ አንደያኔው ሩሲያ አለመሆኑም አንደዚሁም፣ ዛሬ የኢትዮጵያ ወዛደር መደብ ፈጽሞ ሊናቅ የማይችል የፖለቲካ ሀይል ቢሆንም፣ ይህንን መደብ ስለሬቮሉሽን ያስተማረውና ለሬቮሉሽን ያደራጀው የፖለቲካ ፓርቲ የለም ስለዚህም፣ በሩሲያው ሬቮሉሽን ዋናውን ትግል ያደረገውና ዋናውንም መሥዋእትነት የተቀበለው የወዛደሩ መደብ ቢሆን፣ በየካቲት አንቀስቃሴ ውስጥ ገን የወዛደሩ ሚና፣ ከዚህ በታች አንደምናየው ሁሉ፣ የተወሰነ ነበር፡፡

ሁለተኛ ነገር፣ በርግጥም ሁለቱ አንቀስቃሴዎች የሚመሳሰሉበት አንድ ዋና ነጥብ አለ፡– ይኸውም ሁለቱም ያቀረቡት መሠረታዊ ጥያቄ የዲሞክራሲ ጥያቄ መሆኑ ነው፡፡ በሩሲያ፣ የነገሡ ፊውዳሎ–ቡርዧ አገዛዝ አንደወደቀና ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በቦታው አንዲተካ በተደራጀ አቢጌን ቢጠየቅ፣ በገራችን ገን፣ ከገሪቷ የታሪክ ደረጃ ጋር በመመጣጠን፣ ይህንን የመጨረሻ የዲሞክራሲ ጥያቄ ከሁሉ ንቁ የሆነው የሕብረተሰቡን ክፍል ቢያቀርበው፣ በሬው ሕዝብ ገን በደፈናው ዲሞክራሲያዊ ነጻነቶችን ጠይቋል፡፡ በዚህም በኩል ቢሆን የየካቲት አንቀስቃሴ በደረጃው ከ1905 የሩሲያ ዲሞክራሲያዊ ሬቮሉሽን ወደ ኋላ የቀረ ነው ማለት ነው፡፡ በተረፈም፣ ሁለቱ አንቀስቃሴዎች የሚመሳሰሉበት ሌላ ነገር ካለ ያው ሁለቱም መላ ሕብረተሰቡን ከትግል ውስጥ ማስገባታቸው ነው፡፡ ይህ ገን ምንም ያህል የሚጠቀመን የማመሳሰያ ነጥብ አይደለም፡፡

ሁለቱን አንቀስቃሴዎች አናመሳስል ከተባለ፣ ከዚህ ማመሳሰል ልናገኘው የምንችለው ፍሬ ነገር ቢኖር፣ የኢትዮጵያ ተጨቋኝ መደቦች – ወዛደሩ፡ ገበሬው፡ ትንሽ ከበርቴውም አንኳን ይበልጡ ክፍል – በፖለቲካ ነፃነት በኩል ከ1905 የሩሲያ ተጨቋኝ መደቦች ወደኋላ የቀሩ መሆናቸውን ነው፡፡ ይህ መቼስ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ወደኋላ የመቅረት ተሰጥኦ ስላላቸው፣ ወይንም ምናምሉን ስለያዙ፣ ወይንም በተፈጥሮ ወደኋላቀሮች በመሆናቸው አንዳይደለ ገልጽ ነው፡፡ ነገሩ፣ በዚያን ጊዜ የሩሲያ ሁኔታና በዘሬ ኢትዮጵያ መካከል፣ በዚያ

ጊዜ የዓለም ሁኔታና በዘረው ጸለም ሁኔታ መካከል ልዩነት ስላለ፣ የታሪክ ደረጃዎች የተለያዩ በመሆናቸው ነው::

ወዳገራችን አንቀስቃሴ አንመለስና፣ በዚህ ምእራፍ ውስጥ ለማቅረብ የምንፈልገ ጥያቄዎች አሉ::ከነዚህም ውስጥ አንዳንዶች አንደሚከተሉት ናቸው:— የየካቲትን ሀንቀስቃ ሴ ዓይነተኛ የሚያደርጉት የተጠበቡ ድርጊቶች የትኞች ናቸው ? በዚህ አንቀስቃሴ ውስጥ የኢትዮጵያ መደቦች አሰላለፍ አንዴት ነበር ? የየካቲት አንቀስቃሴ ያቀረባቸው ጥያቄ ቾና ያገኙቸው ውጤቶች የትኞች ናቸው ?

ይሁንናም አነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ ከመሞከራችን በፊት፣ ሁለት ማስጠንቀቂያዎ ችን ለማቅረብ አንወዳለን::አንደኛ የየካቲት አንቀስቃሴ ገና አላከተመም::ይህ ጽሁፍ በሚሰናዓበት ወቀት — የሰኔ ወር መጠረሻ፣ የሀምሌ መጀመሪያ — የጦር ሀይሉች ቀናውን ሥልጣን ይዘውታል ይባላል::በየከተማውና በየገጠሩ ም ዓየነት አንቀስቃሴዎች አንዓሉ ለ ማወቀ — በተለይም በውጭ አገር ሆኖ — አስቸጋሪ ነው:: ... አንቀስቃሴው ገና በሳሳከ ተመ በሚተቸሉት ገጾች ነጥቦችና የአስተያየት አቀጣጫዎች የመጠረሻ ፍርድ አይደሉም:: ሊሆኑም አይችሉም::ወደፊት የነዱ በነርሱ ሳይ መመለስ ያስፈልጋል::

ሁለተኛ፣ አንዓንዱ በጣም አስፈላጊ የሆኑትን ጥያቄዎች አሁን ለመመለስ አልቻልን ም::ለምሳሌ፣ በጦር ሀይሉች ውስጥ ያለው አሰላለፍ — ማን ወደቀኝ፣ ማን ወደግራ፣ ማን መሃል አንደሆነ — በፍጹም ገልጸ አልሆነልንም::አንደዚሁም አንደሚያዝያ 12ቱ ያለውን ሰላማዊ ሰልፍ ማን አንደመራና አንደመራ አሳወቀንም::ከበታው ርቀን በመገኘታችንና ዜና በማጠሩም ነው::ይሁንናም፣ በትንተናችን ውስጥ የምናቀርበው ቀና አዝማሚያ ተገባሬችንን ለማስጦር አንደሚበቃ በመተማመን፣ አንባቢ አንገባቢዎች በዜናዎችም ፣ በትንተናም ይህንን ጽሁፍ አንደሚያርሙትና አንደሚያሟሉት ተስፋ አናደርጋለን::

2.1. ቀና ቀና ድርጊቶች

ከዚህ በታች የምናቀርባቸው ዜናዎች ከኢትዮጵያ ጋዜጦች፣ ከውጭ አገር ጋዜጦችና በአውሮፓ የኢት. ተማ. ማ. ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ካወጣቸው የዜና ሪፓርቶች የተጠረቀሙ ናቸው::ምናልባት የቀን አቆጣጠር ስሕተት ሊኖር ይችላልና አዚህም ላይ አንባቢ አረቡ አንዲያጣሪ አናስታውቃለን::

ቀር 4 ቀን 1966::በነገሌ የሚገኘው አራተኛ ብሪጌድ ከፍተኛ መኮንኖችን ይዞ በማሰር አመጸ::ያመጹ ቀና ምክንያት የምገበና የውሃ አቀረት፣ አንደዚሁም ወታደሮች ለከ ፍተኛ መኮንኖች አንደአሽከር ማገልገል በሳነገሬገቹቸው ነው::ወታደሮች ካመጹ በኋላ ወደ



አዲስአበባ ማመልከቻ ላኩ::የምድር ጦር አዛዥ ድረቤ ጥበሉ ሁኔታውን ለማረጋገጥ ቢመጣ አመጸ ያደረጉት ወታደሮች አርሱንም ይዘው ወታደሩ የሚበላውንና የሚጠጣውን አንዲበላል አድርገው አቆዩት::ጄኔራሉ በኋላ አዲስ አበባ ቢመለስ ሆስፒታል መግባት የገዶ ሆኖበታል

የካቲት 4::የኢትዮጵያ አስተማሪዎች ማህበር ደጋገም አቤቱታ አቀርቦ መልስ ካጣ እና የትምህርት ሚኒስትሩ ሀሳቦዎችን አልቀበል ብሉ ቢያስቸገር፣ ማህበሩ ለንጉሡ አቤቱታ ያቀርበል::አቤቱታው የደሞዝ ጭማሪን የሚመለከት ቢሆን፣ በተጨማሪ 'አጠቃላይ ትምህርት' የተባለውን አቀዶ የሚቃወምና በዚያውም የመሬት ዶልዶልን ጥያቄ የሚያቀርብ ነበር::

በዚሁ ቀን፣ የነአከሊሉ መንግሥት በሀምሌ ወር ለሪሱ ወምር የነበረውን የ750 ብር የደሞዝ ጭማሪ 'መሥጭአት' በማድረግ ለረሀብተኞች አንዲዉል ማድረጉን ገልጸዉል::

በሚቀጥለው ቀን ንጉሡ የባህር ሀይልን አው መኮንኖች ለመመረቀ ወደአስመራ ተጓዘ በዚሁ ቀን፣ በቢሾፍቱ ያለው አየር ሀይል አምጾ በበኩሉ አርሱም አዛዡን ያዘ::የካቲት 6 ቀን ጄኔራል አሰፉ ሂደ ከአየር ሀይሉች ጋር ከተገናኘ በኋላ፣ አቤቱታቸውን ለንጉሡ አንደሚያቀርብ ቃል ገብቶ አዛዛቸውን አንዲፈቱ አደረገ::

የካቲት 7::ከዚህ ቀን ጀምሮ ከአንዱ ሳምንት በላይ የቆየው የተማሪዎች ተቃውሞ ተከፈተ::ተማሪዎች አውቶቡሶችንና መ ኪናዎችን ሰበበሩ::ከአንዱ ሳምንት በኋላ የመንግሥ ቱ የማስታወቂያ ሚኒስቴር ባወጣ መግለጫ መሠረት፣ 75 አውቶቡሶች፣ 36 መኪናዎች፣ 26 የመንግሥት መኪናዎች፣ 7 የዲፕሎማቶች መኪናዎች..ወዘተ. ተወገረው ነበር::'ሌሎችን ሲያጠቀ ወይንም ሲቀሙ የተያዙት 558 ናቸው' ይል ነበር መግለጫው::ይህንን የረብሻና ዊ አመጸ ድርጊት መንግሥቱ አንደተለመደው 'የቀቲት ወንበዴዎች' ሥራ ነው ይል ነበር::

የካቲት 11::መምህራን በመላ ኢትዮጵያ ሥራ አቆሙ::መንግሥቱ ደገም ቀደም ብሉ ከቀር 1 ቀን ጀምሮ የነዳጅ ቀጋ በ50 በመቶ ከነዲጨምር ማድረጉን አስታውቆ ስለነበር፣ የታክሲ ነጂዎችም የዚህኑ ለቶ ሥራ አቆሙ::በዲስ አበባ፣ በነዶ በኩል አስተማሪዎች ተማሪዎችና ታክሲ ነጂዎች፣ በሌላ በኩል ፖሊስ ሆነው ይጋጩና ብዙ ሰው ይቆሰላል፣ የሞተ ም አንደነበሩ ተገልጸአል::

የካቲት 16::በዚህ በአመጸ ሁኔታ ንጉሡ በቴሌቪዥን ቀርቦ የቤንዚን ቀጋ ጭማሪ መሰረዙንና 'የአጠቃላይ ትምህርት ጥናት' የተባለውም 'ለሕዝባችን አስኪገባው ድረስ' ከሥራ ላይ የማይውል መሆኑን አስታወቀ::ስቀኑን የተደረገው የተማሪዎች፣ ያስተማሪዎችና የታክሲ ነጂዎች ትግል መንግሥትን አንዓርበተበተው ለሁሉም ገልጸ ሆነ::ይህ የንቀስቃሴው የመጀመሪያ ድል ሆነ::

የካቲት 19::ኤርትራ የሰፈረው ሁለተኛ ክፍለጦር ቀና አዛዡን፣ ከፍተኛ መኮንኖ ችንና የጠቅላይ ገዛቱን ቀና አስተዳዳሪዎች ይዞ ካሰረ በኋላ፣ ከተማውን ያዘ::አስመራ ለውጭ ትራፊክ ተዘጋ::ካዲስአበባ ጋር ያለው ገንኙነት በሰልክ ብቻ ሆነ::በዚህ ሁኔታ፣

ሁለተኛው ክፍለጦር በሬዲዮን ለመንግሥት 23 የሚሆኑ ጥያቄዎችን አቀረበ::ከነዚህ ውስጥ የደሞዝ ጭማሪ፣ የወታደር የኑሮ ሁኔታ መሻሻል፣እንደዚሁም የዲሞክራሲያዊ ነጻነቶች ጥያቄ ዎች ቢኖሩ፣ የነአክሊሉን መንግሥት ሠራዊቱ እንደሚታወቀው የሚያስታውቅ ነጥብ ነበር:: በዚሁ እለት የቢሾፍቱ አየርሀይልና ያዲስአበባው አራተኛ ክፍለጦር፣ እንደዚሁም የባህር ሀይል አመጹን እንደሚደግፉ አስታወቁ::

በማግሥቱ፣ የካቲት 20 ቀን፣ መንግሥቱ የአራት ጄኔራሎች አስታራቂ ጓድ ወደአስመራ ላከ::ያመጸው ክፍለጦር ከንቱ በስተቀር በሰቶን ጄዛ አሰረ፣ አራተኛው መልእክቱን ይዞ ወደአዲስአበባ እንዲመለስ አደረገ::

በዚሁ እለት፣ በምጽዋ፣ የባህር ሀይልም ዝቅተኛ መኰንኖችና ተራ ወታደሮች ከፍተኛ መኰንኖችን ይዘው ከሠፈሩ በኋላ ያስመራውን አመጽ በድርጊት ጭምር ደገፉ::የባህር ሀይል ዋና አዛዥ እስክንድር ደስታ በመርከብ ወደጂቡቲ ሸሸ::

በዚያም ከመደናገጡ የተነሣ፣ ንጉሡ ነገሥቱ የዚያን ለት ማታ በደገብ መናገር አቅቶት እንደነበር ይነገራል::የሆነ ሆኖ፣ የአክሊሉ መ ንግሥት ወዲያው ከሥልጣን መውረዱን፣ የተራ ወታደር ደሞዝ፣ በየካቲት 17 — ማለት ከስድስት ቀናት በፊት — ከ75 ብር ወደ 100 ብር ከፍ ብሎ የነበረው፣ አሁንም ተጨምሮ 112 ብር መድረሱን ንጉሡ አስታወቁ::ይህም እንግዲህ በአንድ ሳምንት ውስጥ የ 50 በመቶ ጭማሪ መሆኑ ነው::

ሆኖም፣ ይህ የደሞዝ ጭማሪ፣ ያዲስአበባውንም አራተኛ ክፍለጦር ከማመጽና ከተማውን ከመያዝ አላስቀረውም::ይህ ክፍለጦር የካቲት 21 ቀን ያዲስ አበባን ሬዲዮ ጣቢያዎች መገናኛዎችን፣ የከተማውን ዋና ዋና ሥፍራዎች ያዘ::በሄሊኮፕተር በአዲስአበባ ላይ ባበተነው ወረቀት ክፍለጦሩ ያስመራውን ሠራዊት እንደሚደግፍ ከማስታወቁም በላይ፣ እርሱም በበኩሉ ያሉትን መብ ድርጅቶች አቀረበ::በዚህ ሁኔታ፣ ንጉሡ የዚያኑ ለት እንደገና በቴሌቪዥን ብቅ ብለው ያክሊሉን መንግሥት ሥራ መልቀቅ ያጸደቁ መሆኑንና እንዳልካቸው መኰንን በቀዳሚ ሚኒስትርነት፣ አቢይ አበበ በጦር ሚኒስትርነት፣ ወልደሥላሴ በረካ በምድር ጦር አዛዥነት መሾማቸውን አስታወቁ::የነአክሊሉ መወገድ ሁለተኛው የየካቲት ትርፍ ሆነ::

<u>የካቲት 22</u>::ከአምስት ሺ በላይ የሆኑ ተማሪዎችና አስተማሪዎች በሰላማዊ ሰልፍ አድርገው አክሊሉ በቶሎ እንዲቀጡ፣ እንዳልካቸው እንዲወገዱና ሕዝባዊ መንግሥት እንዲቋቋም ጠየቁ::በውጭ አገር ጋዜጦች እንደተነገረው ከሆነ፣ ያራተኛው ክፍለጦር ወታደሮች በሰልፉ ላይ ተኩሰው ሁለት ሰው ገደሉ::

በዚሁ እለት፣ ተይዘው የነበሩትን አንዳንድ ሚኒስትሮች ወታደሮች ወስደው ለንጉሡ 'አስረከቡ'::በውጭ አገር ጋዜጦች እንደተጻፈው ከሆነ፣ ወታደሮች ሚኒስትሮችን ለንጉሡ የሰጡበት ምክንያት ንጉሡ 'እንዲቀጧቸው' ነበር::አክሊሉና ወንድሙ ከመጀመሪያውም ከንጉሡ ዘንድ ተሸሽገው ስለነበር፣ ከተያዙት ውስጥ አልነበሩም::ለማንኛውም፣ አራተኛው ክፍለጦር የዚያኑ ለት ከተማውን ለቀቀ::እንዳልካቸውም ከወታደሩ ድጋፍ አለኝ ብሎ ተናገረ::



<u>የካቲት 26</u>::ንጉሡ፣ በሁለት ሳምንቶች ውስጥ ለስድስተኛ ጊዜ በቴሌቪዥን ወጥተው፣ ሕገመንግሥቱ እንዲሻሻል መፍቀዳቸውንና ይህም መሻሻል ጠቅላይ ሚኒስትሩ በፓርላማው ፊት ሀላፊነት እንዲኖርበት የሚያደርግ መሆኑን አስታወቁ::ሕገመንግሥቱ በስድስት ወር ውስጥ ተሻሽሎ ይቀርባል ተባለ::

<u>የካቲት28</u>::ቀደም ብሎ የ16 ነጥቦች ጥያቄ ካቀረበ በኋላ፣ ለነዚህ ምንም መልስ ባያገኝ ቢቀር፣ የኢትዮጵያ ሠራተኞች አንድነት ማህበር ጠቅላላ የሥራ ማቆም ትእዛዝ አውጥቶ፣ በዚህ ጊዜ የመላ አገሪቱ ሥራ በሙሉ ጉደል ቆመ::ይህም በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያው ጠቅላላ የሥራ ማቆም አድማ ነው::አድማው የቆየው እስከመጋቢት 2 ሲሆን፣ የማህበሩ አባሎችና ሌሎችም ሠራተኞች፣ በጠቅላላው 120 000 ሰው ተሳትፎበታል::

<u>መጋቢት 3</u>::የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን አገልጋይ ቄሶች ጥያቄዎች አቀረቡ::ከጥያቄዎች ውስጥ የደሞዝና የሥራ ሁኔታ ነጥቦች ቢኖሩ፣ በጠቅላላው ግን ታላላቅ የቤተክህነት ሹማምንትም እንደነዚያው እንደወደቁት ባለሥልጣኖች ሊፈረድባቸው የሚገቡ ወደኞችና ዘራፊዎች መሆናቸውን የሚገልጹ ነጥቦች ነበሩ::

<u>መጋቢት 8</u>::ከ 5000 በላይ ያዲስአበባ ወዛደሮች ሴቶች በሰላማዊ ሰልፍ አድርገው፣ ለእኩል ሥራ እኩል ደሞዝ፣ የሥራ ሁኔታን መሻሻልና ጠቅላላ መብቶችን ጠየቁ:

በመጋቢት 3 የተደረገው የቀሳውስት ጥያቄና ይህ የሴቶች ሰላማዊ ሰልፍ ፍጹም ያልተጠበቁ፣ በአገሪቱ ታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ የታዩ ድርጊቶች ነበሩ::

<u>መጋቢት 15</u>::የኤርትራ ግንባር የደበርዋን የነሀስ ማእድን አጥቅቶ ሁለት ዘበኞችን ገደለ ተባለ::

<u>መጋቢት 16:</u>:ወታደሮች ብሥራተወንጌልና ያዲስአበባን ሬዲዮ ጣቢያ ከበቡ:: ይህ የተደረገው፣ በአመጽ ተሳትፈው የነበሩ 25 ያህል ዝቅተኛ መኰንኖች ታሥሩ ስለተባለ ይመስላል::ማታውኑ ንጉሡ የቀድሞ ሚኒስትሮችን ዘረፋና ጥፋት የሚመረምር ኮሚሽን እንደሚቋቋም አስታወቁ::ወታደሮችም ጣቢያዎችን ለቀቁ::

በዚሁ እለት፣ በአስመራ ውስጥ በማዘጋጃ ቤት ሠራተኞችና በፖሊስ መካከል ግጭት ነበር::በበኩሉ ያዲስአበባ ከንቲባ ሀይለጊዮርጊስ ወርቅነህ ሠራተኞቹ ላቀረቧቸው የ 23 ነጥብ ጥያቄዎች መልስ አጠፉ::በሌላ በኩል ግን፣ አቶ ልጊስ ዓለማየሁ ስለጋዜጣና ንግግር ነጻነት የሕግ ረቂቅ ለፓርላማው አቀረቡ::

<u>መጋቢት 17 — 22</u> ::በአገሪቱ ያለው ሁኔታ እንደገና ቀቀ ያለ ሆኖ፣ በርግጥ ግን በየቦታው ምን እንደሚደረግ ገልጾ አልነበረም::በመጋቢት 17 ሌሊት ሁለተኛ ክፍለጦር አስመራን ይዞ አዛዦቹንና የፖሊስን ዋና አዛዥ አሠረ::በአስመራ ከተማ እንዳልካቸው ይወገዱ የሚሉ ወረቀቶች ተሠራጩ::በሚቀጥለው ቀን፣ የኤርትራ እንደራሴ የሠራዊቱን ስድስት ተጨማሪ ጥያቄዎች ይዞ ወደአዲስአበባ በሠራዊቱ እንደተላከ ተነገረ::

አዲሱ የአንዳልካቸው መንግሥት ሥራ ለመልቀቅ ማቀዱን ሲገልጽ አስታወቀ የሚል ወሬ ነበር::በኋላ ግን ተስተባብሏል::

በሌላ በኩል ግን፣ መጋቢት 19 ቀን መላው የጂማ ሕዝብ በሥርዓቱ ላይ ተነሥቶ ሀይለኛ ሰላማዊ ሰልፍ አደረገ::ፖሊሶች ተኩሰው ብዙ ሰው ገደሉ::በማግሥቱ ሕዝቡ እንደ ገና ሰላማዊ ሰልፍ አድርጎ ፖሊሶችን አባርሮ በሠፈራቸው ውስጥ እንዲዘጋበቸው አድርጓል፣ የሚያስተ-ባብረውንም የ 34 ሰዎች ኮሚቴ መርጧል::

መጋቢት 20 ቀን፣ የመቂ ሕዝብ መሬትን በቀሙት ላይ ተነሥቶ ከተቀጋ በኋላ በውጊያው 11 ሰው ሞተ::የቀማኞች ንብረት ተያዘ::የመንግሥቱ ፖሊስም ከ 500 ሰው በላይ ይዞ በበረት ውስጥ አጎረ::

መጋቢት 22 ቀን፣ መንግሥትን ለመገልበጥ የዶለቱ ሰዎች እንደነበሩና እንደተነሳባቸው፣ እነዚህም ሰዎች ከሠራዊቱ ጋር ምንም ግንኙነት እንደሌላቸው አቢይ አበበ አስታወቀ::ይሁን እንጂ፣ ምንም እንኳን የአየር ሀይል ስም በሀሜት ቢነዛ፣ ዶለቱ የተባሉት እነማን እንደሆኑ ፈጽሞ ሳይታወቅ ቀርቷል::የጊዜው መንግሥት የፈጠረው መሆኑ ነው::

በተረፈ ግን፣ በዚሁ ጊዜ ውስጥ — ማለትም ከመጋቢት 17 ጀምሮ — በየቦታው የየመሥሪያ ቤቱና የየድርጅቱ ሠራተኞች ባለቆቻቸው ላይ እየተነሡ፣ ዘራፊና ወደኙ መሆናቸውን እያጋለጡ፣ ጥያቄዎች እየደረደሩ፣ ሥራም እያቆሙ በመታገል ብዙዎች ከቦታቸው እንዲመነቀሉ አድርገዋል::

መጋቢት 23::ሕገመንግሥትን ያሻሽላል የተባለው ጉባዔ ተከፈተ::

መጋቢት 30::ጊዜያዊ ነኝ ብሎ የነበረው የእንዳልካቸው መንግሥት የረጅም ጊዜ የመሸሻ እርምጃዎች አቅዶ ሠርቶ አሠረ::

ሚያዝያ 2::በአሰላ ከተማ ከ 15 000 ሕዝብ በላይ ሰላማዊ ሰልፍ አድርጎ መሬት ላራሹ እንዲመለስ፣ መሬትን ወደፊት ከሕዝብ መቀማት እንዲቀር፣ እነዚሁ ዱቄ የበረቀቱትን የልማት የሕዝብ ሀብት እንዲከፍሉ ወዘተ. ጠየቀ::

ሚያዝያ 3::ያዲስአበባ ሕዝብ በተራው ከ 10 000 በላይ ሆኖ ተሰልፎ የኮንቲባውን የሀይለጊዮርጊስን መነሣት ጠይቋል::

ሚያዝያ 8::የዱሬዳዋ፣ የደሴ፣ የመቀሌ (ትግሬም)፣ የጅብትና ሜጫ አውራጃ ሕዝብ (ሸዋ)፣ የጨቦና ጉራጌ ሕዝብ፣ የሐረር ሕዝብ በየበኩሉ መብትና ነጻነት በመጠየቅ ትላልቅ ሰላማዊ ሰልፎችን አደረገ::

ሚያዝያ 12 ::በአገሪቷ ታሪክ ውስጥ እስከዛሬ ለት ታይቶ የማይታወቅ፣ ከመቶ ሺ ሰው በላይ የሰበሰበ ታላቅ ሰላማዊሰልፍ ባዲስአበባ ተደረገ::ሰልፉ የእስላሞችን እኩልነት ለማስከበር የተደረገ ቢሆን፣ ቤተክህነትና መንግሥት እንዲለያዩ፣ የእስላም ሃይማኖት እንዳይጠቃ፣ ለዚህ ሁሉ እኩል መብት እንዲኖር ወዘተ. ይጠይቅ ነበር::ሃይማኖት የግል አገር የጋራ፣ ሃይማኖት በትምህርት ፕሮግራም ውስጥ አይገባ፣ ለእስላም [illegible]



እኩል መብት፣ ወዘተ. የሚሉ ሰሌዳዎች ነበሩት::ከመቶ ሺው ተሰላፊ ውስጥ ወደግማሽ የሚጠጋው የእስላም ወንድሞቹን ጥያቄዎች የሚደግፍ ክርስቲያን ነበር::በሰልፉ ላይ ከተዘመሩት መዝሙሮች 'ክርስቲያኑ ወንድሞቻችሁ፣ ተሰልፈናል ከጎናችሁ'፣ 'ክርስቲያኑ ወገናችን፣ ተጠብቆ መብታችን፣ እንድንሠራ ላገራችን፣ ተሰልፏል ከጎናችን'.... የሚሉ ነበሩ::

ሚያዝያ 15::ሠርቶ አደሩ ሕዝብ በየቦታው የሚያደርገውን የመብት ትግል ለማደናቀፍ፣ መንግሥቱ የሥራ ማቆምን መብትና ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግን መብት የሚነሳ አዋጅ አወጣ::ይሁን እንጂ ይህንን ፀረሕዝብ አዋጅ ችላ በማለት፣ በሚቀጥለው ቀን 2000 ያውራ ጎዳና ባለሥልጣን ሠራተኞች መሥሪያ ቤታቸውን ይዘው ጥያቄዎቻቸውን ደርድረዋል::

ሚያዝያ 18::አራተኛው ክፍለጦር እንደገና አዲስአበባን ከያዘ በኋላ፣ የቀድሞዎቹን ሚኒስትሮችና ወደ 200 የሚጠጉ ከፍተኛ መኮንኖችን ይዞ አሰረ::

በሚቀጥለው ቀን፣ 'የጊዜያዊ ፕሮብሌሞች ሰላማዊ መፍትሄ አቀናባሪ ኮሚቴ' የሚባል፣ ኮሎኔል አለምዘውድ ተሰማ በተባለ ሰው የሚመራ የጦር ሀይሎች ኮሚቴ ለመጀመሪያ ጊዜ ብቅ ብሎ ሚኒስትሮችና የተባሉት መኮንኖች ለምን እንደተያዙ ለጋዜጦች አስታወቀ::ወዲያውኑ ግን 'የጸጥታ ኮሚቴ' የተባለው ሌላ የጦር ሀይሎች ቡድን ከንጉሡ ፊት ቀርቦ ታማኝነቱን ከመግለጡም በላይ፣ ያዲስአበባን ጸጥታ በምን አኳኋን ለመጠበቅ እንደተደራጀ ለንጉሡ ገለጠለት::

ግንቦት ወር::ይህንን ወር ዓይነተኛ የሚያደርገው፣ የየመሥሪያ ቤቱና የየድርጅቱ ሠራተኞች፣ ሌቦች ባለሥልጣኖችን በማጋለጥ፣ የደሞዝ ጭማሪን በመጠየቅ፣ ማህበር የማቋቋም መብት፣ የሥራ ሁኔታን መሻሻል፣ ወዘተ. በመጠየቅ ያደረጓቸው የሥራ ማቆም ትግሎች ናቸው ሠራዊቱ ሁለት-ሶስት ጊዜ ሥራ ያቆሙትን ሠራተኞች — ለምሳሌ ቴሌኮሙኒኬሽን፣ መብራት ሀይል — በግድ እንዲሠሩ አድርጓል::የእንዳልካቸው መንግሥት በበኩሉ የሰዎችን የሹመት ቦታ ከመለዋወጥና በሠርቶአደሩ ሕዝብ ላይ እንግዳ ማስፈራሪያዎችን ከመሰንዘር በስተቀር፣ እንዳችም የመሻሻያ እርምጃዎች ከተባሉት ውስጥ አልፈጸመም::ያገሪቷ የኢኮኖሚ ሁኔታ እየባሰ ሲሄድና ረሀብ በሌሎች ጠቅላይ ግዛቶችም ሲስፋፋ፣ የውስጥ ንትርኩንና ትንንቅን መደለትን የቀጠለው የገዥዎች መደብ ምንም እርምጃ ሊወስድ አልቻለም::ይሁንና የመንግሥቱ ጋዜጦች 'ላዲሱ ካቢኔ ጊዜ እንስጠው' እያሉ፣ መሠረታዊ ጥያቄዎችን በሚያነሡትና ለመብት በሚታገሉት ሠራተኞች ላይ መዝመት ቀጥለዋል::በጠቅላላው ግን በገሪቷ መንግሥት አለ ለማለት አስቸጋሪ ነበር::ይህ ሁኔታ እስከሰኔ ወር አጋማሽ እንደዚሁ ቆይቷል::

ሰኔ 13::በውጭ አገር ጋዜጦች እንደተወራው ከሆነ፣ በቢሾፍቱ በአየርወለድና በአየርሀይል መካከል ግጭት ተደርጎ፣ አንድ ሰው ሲሞት 19 ቆሰሉ::

ሰኔ 21::አራተኛ ክፍለጦር ለአራተኛው ጊዜ አዲስአበባን ያዘ:: በ22 እና በ 23 እንደነአሥራተ ካሣ ያሉትን ትላልቅ ባላባቶች ይዞ አሠረ::

ሀምሌ 2::ሠራዊቱ በሙሉ ኃይል የመንግሥት ሥልጣን የያዘ ይመስላል::በዚህ ቀን፣ 'ኢትዮጵያ ትቅደም' የሚባል የጦር ሀይሎች አቀናባሪ ኮሚቴ 13 ነጥቦች ያሉበት ፕሮግራም ለንጉሡ አቀረበ::የዚህ ፕሮግራም ዋና ነጥብ ከንግዲህ ሠራዊቱ በአገር አገዛዙ ሥራ በቀጥታ የሚሳተፍ መሆኑን፣ እንዲያውም ዋናዉ የሥልጣን ምንጭ መሆኑን ማስታወቁ ነው::

---

## 2.2. በየካቲት አንቅስቃሴ የመደቦች አሰላለፍ

በንዱ ሕብረተሰብ ውስጥ የሚገኙት መደቦችና በነርሱም መካከል ያሉት ግንኙነቶች ጥርተው የሚታዩት ከሰላም ጊዜ ይልቅ በሕብረተሰቡ ውስጥ ትልቅ ችግርና ግጭት ሲነሣ ነው:: በሰላም ጊዜ፣ ማን ከማን ጎን እንደተሰለፈ በደፈናው ለመመዝገብ የሚቻል ቢሆንም፣ ይህ አሰላለፍ ጥርት ብሎ የሚታየው ደንበኛ የመደቦች ግጭት ሲኖር ብቻ ነው::

በጭሩ የተቀጨው የ1953ቱ የታህሣሥ የመንግሥት ግልበጣ ሙከራ ረዘም ላለ ጊዜ ባለመቆየቱ መላ ሕብረተሰቡን ሊነካው አልቻለም ነበር::ስለዚህም፣ የኢትዮጵያን መደቦች — ምናልባት ከገዥ መደቦች በስተቀር — አሰላለፍ ሊያሳየን አልቻለም ነበር::የየካቲቱ የኢትዮጲያ ሕዝቦች ረቮሉሽናዊ አንቅስቃሴ ግን፣ ከዚህ በላይ በንዱ ቦታ እንደተመለከተው ሁሉ፣ መላ ሕብረተሰቡን ከዳር አስከዳር ስላንቀሳቀሰ፣ እስከዛሬ ታይቶ በማይታወቅ አኳኋን የመደቦችን ሰልፍና የትግላቸውን አቅጣጫ አሳይቶአል::እንዴት ?

(ሀ) <u>ገዥ መደቦች</u>::

በአውሮፓው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር ስብሰባዎችና በማህበሩ መጽሄቶች ተደጋግሞ ባለፉት ቀደምት ዓመታት ውስጥ በተሰጠው ትንተና መሠረት — ደግሞም ባሁኑ ጊዜ ባለን አውቀት ይህ ትንተና ትክክል ነው — የኢትዮጵያ ገዥ መደቦች የቢሮክራሲያዊ ከበርቴ መደብና ፊውዳላዊ(ጉልተኛ )መደብ ናቸው::ከታህሣሥ የመንግሥት ግልበጣ ሙከራ በኋላና በተለይም ባለፉት አሥር ዓመታት ውስጥ፣ ዋናውን የመንግሥት ሥልጣን ለጊዜው የጨበጠው በነአክሊሉ—አክለወርቅ—ማሞ ታደሰ የሚመራው የቢሮ ከበርቴው መደብ ነበር::በሁለት ክንፎች ሊከፈል የሚችለው የጉልተኞች መደብ በሥልጣን የሚካፈለው በሁለት መንገዶች ነበር::አንደኛ፣ የቀንነት ባላባቶች፣ የአቀንነት የጫሬዎች ክንፍ፣ በነአሥራቴ ካሣ ዙሪያ የተሰበሰበው፣ ወይ በዘውዱ ምክርቤት አማካይነት፣ ወይንም በሕገ መወሰኛ ምክርቤት አማካይነት፣ ያለበለዚያም በቀጥታ ፊውዳላዊ ምርት መሠረት ከንጉሡ ጋር ባለው ቀጥታ የሰው—ለሰው ግንኙነት በኩል በመንግሥት ሥልጣን በተከታይነት፣ በሁለተኛ ደረጃ ተካፋይ ነበር::ሁለተኛ፣ የተማረው የጉልተኛ መደብ ክንፍ — በእንግሊዝኛ 'ኢንላይትንድ አሪስቶክራሲ' የሚባለው — እነእንዳልካቸውን፣ ሚካኤል እምሩን ወዘተ. የመሰለው ደግሞ በቀጥታ ከቢሮ ከበርቴዎች ጋር በሙሉ ኃይል አክል የሥልጣን ተካፋይ ሆኖ፣ በቢሮ ከበርቴ መደብ ላይ ያለውን ቀሳቹ ሸሪፍና



ችሉ አብሮት ሲሠራ ቆየ::

ካለፉት ስድስት—ሰባት ዓመታት የገዥ መደቦች ትንንቅ ውስጥ በአሜሪካኖችና በሌሎችም ኢምፔሪያሊስት አገሮች — ለምሳሌ በፈረንሣይ — ይደገፍ የነበረው የነአክሊሉ—አካለወርቅ—ማሞ ታደሰ የቢሮ ከበርቴዎች መደብ አሸናፊ ሆኖ በመውጣት ብዙዎቹን አቀንት የጫሬ ባላባቶች ከሥልጣን እያራቃቸው መጥቶ ነበር::በየካቲቱ አንቅስቃሴ፣ የተማሩ ጉልተኞች ክንፍ 'በድንገት' ከሥልጣን! ላይ ጉብ ማለቱን ሊያስረዳን የሚችለው አንድ ዋና ምክንያት ይህ ከቀድሞውም በሁለቱ ዋና የገዥ መደቦች መካከል የነበረው የሥልጣን ሽሚያ ነው::

የቢሮ ከበርቴዎች የሥልጣን መሠረት ምን ነበር የሚለውን ጥያቄ ዛሬ በቀላሉ ለመመለስ ይቻላል::ይህ መደብ፣ አሁን እንደታየው ከሆነ፣ በጠቅላላው ሕብረተሰብ ውስጥ የነበረው መመርኮዝ መደብ በጣም ጠባብ ነበር::ከንጉሡ ነገሥቱ ጋር በመሻረክ፣ በየቢሮው የራሱን ደጋፊዎች በመሾም፣ በኢምፔሪያሊዝም ድጋፍና በመጠረሸም፣ በንጉሡ አማካይነትም ሆነ በራሱ፣ በመጨቆኛ ሀይሎች ላይ — ማለት በፖሊስና በወታደር ላይ — በነበረው ቁጥጥር፣ በጉልበት፣ በማስፈራራት፣ አፍኖ በመያዝ ሲገዛ ቆየ እንጂ ሕብረተሰባዊ መሠረት፣ ማለት ከመደቦች ውስጥ የሚመረኮዝበት ሰፊ መደብ አልነበረውም::አሁን ሠራዊቱ ሲያምጽና ሕዝቡ ከዳር አስከዳር ሲነሣበት፣ አንድም ተነሥቶ የሚቆምለት አልተገኘም::በየቢሮው ያስቀመጣቸው ሰዎች ሊረዱት አልቻሉም፣ እነርሱን እራሳቸውን ዝቅተኛ የመንግሥት ሠራተኛና ወዛደር እያጋለጠ፣ ይነሣልን እያለ፣ ላብነታቸውን አረጋገጠባቸው ወጥሮ ያዘ::ንጉሡ ወደመጀመሪያ ንዱም ከለላ ሊሆናቸው ቀኪር ነበር::በየካቲት 23 የአድዋ በዓል ሲከበር አክሊሉ ከንጉሡ ጎን ሆኖ በአደባባይ መታየቱ ለዚህ ምስክር እንዲሆን ነበር፣ ነገርግን ይህም ከለላ ምንም ያህል አልሠራም::

እንደዚህ በሕብረተሰቡ ውስጥ መመርኮዝ ያጣ መደብ መጀመሪያውኑ ከየት ፈለቀ የሚል ጥያቄ ሊቀርብ ይችላል::ይህ መደብ የፊውዳላዊው ሥርዓትና የኢምፔሪያሊዝም ፍጡር ነው::እንደሚታወቀው፣ ከጦርነቱ በኋላ ፊውዳላዊው ሥርዓት አስተዳደሩን 'ዘመናዊ' ማድረግና ከውጭው ዓለም ጋር — በተለይም ከኢምፔሪያሊስት አገሮች ጋር — የሚያገናኘውን የመንግሥት መኪና (በተማሩ ሰዎች የተሞሉ ቢሮዎችን፣ ደጊ የጦርና የፖሊስ ሀይሎችን፣ወዘተ.) የግድ መፍጠር ነበረበት::ቢሮክራሲያዊ ከበርቴው የዚህ ድርጊት ውጤት ነው::ለመታዘዝ፣ በአሽከርነት የጉልተኞችን መደብ ለማገልገል፣ የጉልተኞች መሣሪያ ለመሆን የተፈጠረ ሆኖ ሳለ፣ ቀስ በቀስ አዛዦችን አስወግዶ የመንግሥትን ዋና ሥልጣን የያዘ መደብ ነው::

የቢሮ ከበርቴዎች መደብ በየካቲት አንቅስቃሴ መጀመሪያ ላይ የወታደሩ አመጽና የሕዝብ ቁጣ ዋና ኢላማ፣ ዋናው ተጠቂ ሆነ፣ እንደዚያ ሲያስፈራ የነበረው ሥልጣኑ በሦስት ቀኖች ውስጥ ፍርክስክሱ ወጣ::የነበይ ከዝብ ሆነ::ይህ ብቻ ሳይሆን፣ የመደቡ መሪዎች እነአክሊሉ—አካለወርቅ መግቢያ አጥተው እንደአውሬ ይታደኑ ገቡ::እነዚህ ደብተሮች ሌላው ቀርቶ የቤተክርስትያንን እንኳን አርዓያ ሊያገኙ አልቻሉም::ያ ሁሉ የጀርመቢ ሠራዊ

ታቸው፣ ያ ሁሉ የዘረፉ ሀብታቸው፣ ያ ሁሉ በየቦታው ያስቀመጡት 'ባለሥልጣን' ሊደርስላ
ቸዉ አልቻሉም::ለማጭበርበሪያ ከቡልጋና ከይፋት ጥቂቶች ደጋፊዎችን አስከቤተመንግሥቱ
ቢያስመጡም፣ በገጠሩም ቢሆን፣ ምንም ከቁጥር የሚገባ ድጋፍ እንደሌላቸው ይበልጡን ገልጽ
ሆነባቸው እንጂ ከውድቀት አላዳናቸውም::

የቢሮ ከበርቴዎች ሥልጣን እንደወደቀ ወዲያውኑየማንም ምሣር መውደቂያ ሆኗል::
በተለይም የመንግሥትን ጋዜጦች የሚሸፉት ትንሽ ከበርቴዎች ድሮ የተንቀጠቀጡለትን ያህል
አሁን ይጠናፉበት ጀመሩ::ሥልጣኑን የያዘው የተማሩ ኋለኞች መደብ በተቀጥታ በዘመቻው በ
ይብተናም — ነገ በኔ ነው — እነዚህን ፍጹም ወሳኞች በማበረታታት የኢትዮጵያ ችግሮ
ቹ ሁሉ የተፈጠሩት 'በተደቀው ከቢኔ' መሆናቸውንና 'አዲሱ ከቢኔ' ተአምርን በመሥራት
መናትኚ እንደሚያቀርብላቸው ወዘተ. ጋዜጦች እንዲያወናብዱ አድርጉአል::በነዚህ ጋዜጦ
ች ነገር ከዚህ በታች እንመለከታለን፣ እዚህ ላይ ግን ለማመልከት የምንፈልገው፣ የነአ
ክሊሉ ሀብተወልዴ የቢሮ ከበርቴዎች መደብ ባንድ በኩል የመላ ሕዝቡ ተገቢ ጥላቻ ማረፊያ
ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ተደሞ ሲያስፈራ የነበረው ሥልጣኑ በምንም ከቁጥር የሚገባ የ
መደብ መሠረት ላይ ያልቆመ እንደነበረ ነው::ስለዚህም ፣ ሕዝቡ አንዴ ከተነሣ ወዲያና
የተለመደውን የጭቆና መሣሪያ ከሥራ ላይ ለማዋል እንደማይቸል ገልጽ ከሆነ ወዲያ፣ የሚጠ
በቅ መደገፊያ፣ ከሕዝብ ቁጣ የሚያድን ከለላ ጠፋ::ያንድ መደብ ሥልጣን እንደዚህ በስስ
ት ቀናት ውስጥ ከቶ አመለጠ::

የነአክሊሉ የቢሮ ከበርቴ መደብ መመርከዝ እንደሌለው ገልጽ የሆነውን ያህል፣
የንጉሠነገሥቱና የትላልቅ ባላባቶችም መደብ በሕብረተሰቡ ውስጥ ያለው ድጋፍ በጣም ደካማ
እንደነበረ የየካቲት እንቅስቃሴ አሳይቶአል::ይህ ደካማ ድጋፍ የመጣው ከገጠሩ የዝቀተኛ
ባላባቶች መደብ ነው::

እንደሚታወቀው፣ በተለይ ከመጋቢት 4 ቀን ጀምሮ ከየገጠሩ የዚህን ወይንም የዚያ
ን ከፍለአገር ሕዝብ 'ታማኝነት' ለንጉሡ ለመግለጽና በተለይም አስተማሪዎችን ለማውገዝ
በየክለቱ ዝቀተኛ ባላባቶች ወደአዲስአበባ ይጎርፉ ነበር::የነዚህ ሰልፍ በመንግሥቱ የ
ጸጥታ ድርጅቶች ይዘጋጅ፣ ወይንም የዝቀተኛ ባላባቶችን ነጻ ፍላጎት ይገለጽ፣ የትኛው
እንደሆነ አሁን ቁርጥ አድርጎ ለመናገር አይቻልም::የፊተኛው ሆነ የኋለኛው፣ ለማንኛውም
ድጋፉ በዓይነትም ሆነ በመጠን ደካማ እንደነበረ፣ እንደሆነ፣ ገልጽ ነው::ከበጫን ጠቅላ
ይ ገዢዎች የመጡት ገበሬውን፣ ያንን በችጋር የተጉበቀለውን የሰሜን ኢትዮጵያን ሕዝብ
ለሀይለሥላሴና ለትላልቅ ባላባቶች ድጋፍ ለማሰለፍ እንደማይቸሉ ገልጽ ነበር::የዘሬይቱ
ኢትዮጵያ ከምኒልክ ኢትዮጵያ የተለየች ናት::ገበሬው ዘሬ የየመንደሩን ባላባት ተከትሎ
ለመዝመት ዝግጁ አይደለም::ይህ መሠረታዊ የታሪክ ሀቅ ያልገባቸው እነፀሀዩ እንቆሥላሴ
ጫካ ገብተው የሰው መሳቂያ ሆነዋል::በበኩላቸው እነመስፍን ሰለሺ፣ እነአቢይ አበበ፣



ትንሽ ከቀማሙ በኋላ የነፀሀዩ መንገድ የማያዋጣ መሆኑን ተገንዘበው ባይሆን አይቀርም፣
እንደተጠየቁት፣ በዚህ በሀምሌ ወር መጀመሪያ ላይ እጃቸውን ለሠራዊቱ ሰጥተዋል::

ከደቡብ ጠቅላይ ገዢዎች የሚመጡትን ዝቀተኛ ባላባቶች ከሁለት ከፍሎ ማየት ያስፈ
ልጋል::ነፍጠኞች የሆኑት ያሁኑ አገዛዝ ከወደቀ ከተጫኑበት ገበሬ ለማምለጥ እንደማይቸሉ
ስለሚያውቁ በተቻላቸው መንገድ ሁሉ ትላልቅ ባላባቶችንም ሆነ የቢሮ ከበርቴውን መደገፋቸ
ው የማይቀር ነው::ያገር ተወላጅ የሆኑት ደግሞ እራሳቸውም ከሥርዓቱ ጋር በብሄረሰብ
ደረጃ ግጭት ስላላቸው፣ ለንጉሡም ሆነ ለትላልቅ ባላባቶች የሚሰለፉ አይደሉም::

እንግዲህ፣ የታላላቅ ባላባቶችም ሕብረተሰባዊ የድጋፍ መሠረት ደካማ እንደነበር
ገልጽ ነው::ንጉሡ ነገሥቱና እነአሥራተ ካሣ፣ እንዲሁም እነእንዳልካቸውም ቢሆኑ፣ እንቀ
ስቃሴው ሲጀመር ይህንን የተረዱት አይመስልም ነበር::የካቲት 20 ቀን፣ ንጉሡ ያገሪቷን
''ትላልቅ ሰዎች'' ተቀብሎ ሲያነጋገር፣ ያሁኑ ችግር የመጣው ከዓለም የኢኮኖሚ ውድቀት መ
ሆኑን ከጠቀሰ በኋላ፣ 'ቀደሞም ብዙ ችግሮች ደርሰውብን አሸንፈናቸዋል፣ ይህንንም እንወ
ጣዋለን' ብሎ በድፍረት ተናገሮ ነበር::በዚያውም የገዥውን መደብ ደባዊ ማወናበጃ፣ 'የው
ጭ ጠላት' የተባለውን የተነታበትን ማታለያ እንደገና አንስቶት ነበር::ይሁንናም፣ የዚያ
ኑ ለት ማታ እነአክሊሉ ሥልጣኑን እንዲለቁ ሲገደዱ፣ አሁን የተነሣው ችግር በቀላሉ የማ
ሸነፍ መሆኑ ለብዙዎች አዳማጮች ገልጽ ባይሆን አልቀረም::

የነአክሊሉ መንግሥት እንደአንበይ ካብ ቢፈርስ፣ እነዚህ ኢትዮጵያን በፋሺስታዊ
አመጽ ቢገዙ የቆዩት የቢሮ ከበርቴዎች ቢገለሉ፣ የዚህን ዓይነት ሁኔታ ተዘጋጅቶ ሲጠብቀ
የነበረው፣ በእንዳልካቸው የሚመራው የተማሩ መስፍንነት ክንፍ ድንገት የመጣ ይመስል በሥል
ጣኑ ላይ ገብ አለ::ወታደሩና ሕዝቡ በጭቆና ተንገፍግፎ ያነሣውን ትግል ባይውል ባያድር
ለራሱ ጥቅም ለማዋል መሞከሩ ነበር::የዚህ ወገን ከሥልጣን ኮርቻ ላይ መውጣት እራሱን
የቻለ ታሪክ ነው::የፊውዳላዊ ሴራዎችንና የተንኮል ክብትቡን አፈጻጸም ወደጎን ትተን እ
ንዳንድ ዋና ዋና ነገሮችን ብቻ እዚህ ላይ መመልከት አለብን::

እንዳልካቸው መኰንን፣ ይህ ስሙን ለማስጠራት ያህልና እንዲታወቅ ለማድረግ ያህል
ብቻ፣ ወደጠቅላይ ሚኒስትርነት ይመረጥ ብሎ ያሰበውን ጎዳና ለመጥረግ ሲል ብቻ ለተባበ
ሩት መንግሥታት ዋና ጸሀፊነት ማንም እንደማይመርጠው እያወቀ ተወዳዳሪ ሆኖ የነበረው
ይህ ብልጥ ሰው፣ ለሥልጣን ባለው ጉጉት በጣም የታወቀ ነው::ከዚህ በፊት ደጋግሞ 'መን
ዘት ያለበን እኛ ነን' ያለ ሰው ነው::እንደሚወራው ከሆነማ እርሱና አሥራተ ካሣ ከጥቂ
ት ዓመታት በፊት ንጉሡን 'ለምን ሥልጣን አትለቁልንም ? አንተ እንደሆንክ ከንግዲህ አር
ጅተሃል::' ብለው መክረውት ነበር ይባላል::ይህ የታሪኩ አንድ ወገን ቢሆን፣ በሌላ
በኩል ደግሞ፣ እነእንዳልካቸው—አሥራተ ካሣ—አቢይ አበበ የነአክሊሉን ወገን 'የደሀ ልጅ
ሁሉ' እያሉ ያጥላሉ እንደነበር ያደባባይ ምስጢር ነው::በተረፈም፣ እንደተባለው ሁሉ፣
የነአክሊሉን መውደቅ ተዘጋጅተው ይጠብቁ ነበር::ከዚያም አልፎ ይህንን ውድቀት ለማፋጠን

አንዳንድ አርምጃዎችን ወስደው እንደነበር ይታወሳል::የዛሬ ሶስት ዓመት እነአቢይ የነአ ከሊሉ ገቢ ይመርመር ብለው ጠይቀው ነበር::እነአክሊሉ ያቀረቡትን የመሬት ዱልዱል አቅድ ፓርላማው እንዳያጸድቀው ያደረጉት እነዚህ መሳፍንት ናቸው ይባላል::በሁኑም አንቀሳቃሴ ብዙ ሴራዎችን በነዚያ ላይ ፈጽመዋል ብሎ ይወራል::በቢሮ ከበርቴዎችና በነዚህ መሳፍንት መካከል የቀየው ትግል ሲታወስ፣ የነአንዳልካቸው ወገን ይህን አያደርገውም አይባልም::

የነአንዳልካቸው—እምሩ—አቢይ ወገን አጭበርበርና አሻጥሮ፣ እንደምንም ከሥልጣን ላይ ሲወጣ፣ አሁኑም ቢሆን እንደነገሡ ነገሥታ ሁሉ የየካቲት አንቀሳቃሴ ከድሮዎቹ 'ችግሮች' የተለየ መሆኑን ፈጽሞ አልተረዳውም ነበር::በተለይም አንዳልካቸው የልብ ልብ ተሰምቶት ወዲያውኑ እንደተሾመ ሠራዊቱም ሕዝቡም ይደግፈኛል ብሎ ለመናገር በቅቷል::በተረፈም የዚህ የአጭበርባሪ ሰው ብልጠት እስከዛሬ ከነአክሊሉ ጋር እንዳይታሰር ያደረገው ይመስላል::በቀድሞው መንግሥት ሥልጣን የተባተረ፣ እንደሌሎቹ ሁሉ በዘራፊነቱ የታወቀ ሆኖ ሳለ እስከዛሬ አለመያዙ በውኑ ከብልጠቱም ጋር ምናልባት ከሠራዊቱ ውስጥ ጥቂት ደጋፊዎች እንደሚያገኝ ያስብ ይመስለናል::ይህ ወደፊት መጣራት አይቀርም::

የሆነ ሆኖ፣ አንዳልካቸው ሥልጣኑን በደካማ እጆች እንደያዘ፣ ወዲያውኑ የገዥ መደቦች በተሉ አንዳንድ ማስታረቂያዎችን ለሕዝቡ እንዲጥሉለት አደረጉአለ::በየካቲት 26 ቀን ንጉሡ ባደረገው ንግግር፣ ከንግዲህ ሕዝቡ በአስተዳደሩ ውሳኔዎች እንዲሳተፍ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን እንደሚያምን፣ ስለዚህም አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስቴር ሕገመንግሥትን የሚያሻሽል ኮሚሲዮን እንዲያቋቁምና ውጤቱንም በስድስት ወሮች ውስጥ እንዲያቀርብ ማዘዙን ገለጸ ሕዝቡን ለጊዜው ገብ ያደርገዋል ብሎ የተሰነዘረ ሀሳብ ነው::ይህ አለመብቃቱ ሲታወቅ፣ ፍጹም የሚይዙትን የሚጠብቁትን ያውቁ የገዥ መደቦች ከአንድ ሳምንት በኋላ ንጉሡ አንደገና ሌሎችን የማስታረቂያ አርምጃዎች ለማምጣት ቃል እንዲገባ አደረጉት::'የሕዝቡ ፍላጎት ከንጉሠ ነገሥቱ ሥልጣን በላይ እንደሚሆን'፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ካስፈለጉ እንደሚቋቋሙ፣ በተለይም አንድ ፓርቲ ብቻ ቢቋቋም ንጉሡን ደስ እንደሚለው፣ ወዘተ. ንጉሡ ገለጸ::ይህ የሆነው በመጋቢት 2 ቀን ሲሆን፣ በዚያን ቀን የሀይለሥላሴ ፈላጭ—ቆራጭ ሥልጣን ለመጀመሪያ ጊዜ በሕዝብ ትግል ተወገደ ማሸነፍ እንደጀመረ እንደቀን ብርሃን ገለጸ ሆነ::

ይሁንናም የሕዝቡ ዲሞክራሲያዊ ትግል አዝማሚያ ለገዥ መደቦች ሁሉ አስጊ መሆኑ ሲታወቅ፣ ሁሉም — ከወደቀቶት የቢሮ ከበርቴዎች በስተቀር — በሀይለሥላሴ ዙሪያ መሰብሰብ ጀመሩ::የቢሮ ከበርቴዎችም በበኩላቸው እስከተያዙበት ቀን ድረስ፣ ውስጥ ለውስጥ ሴራቸውን ቀጠሉ::በተረፈ ግን፣ መጋቢት 4 ቀን፣ የገዥ መደቦች ያላቸውን ድጋፍ ሁሉ ሰብስበው አስበልረው ለሕዝብ አሳዩ::በርግጥም በዚህ እለት፣ 'የሕዝብ መሪዎች'፣ ያገርፍቅር ማህበር አባሎች፣ የአሠሪዎች ፈደረሽን መሪዎች፣ ከሠራዊቱ ውስጥ እነአንዳልካቸው—አቢይ የገዟቸው የሁለተኛ ክፍለጦርና የኤርትራ ፖሊስ 'ወኪሎች'፣ በመድረክ ላይ የሚገኙ የጦር ሠራ



ዊት፣ የፖሊስና የክብርዘበኛ አባሎች፣ ከንጉሡ ፊት ቀርበው ያላቸውን ታማኝነት ገለጹ፣ የሠርቶአደሩን ሕዝብ ትግል 'አገር ለመበታተን'፣ 'የውጭ እጅ በማስገባት'፣ ወዘተ. በማለት አወገዙ::ከዚያም በኋላ፣ ከዚህ በላይ እንደተጠቀሰው፣ ከየገጠሩ የሚመጣው የዝቅተኛ ባላባት ጦርና ተጣሏል::

'አሊቡን ካቢኔ' በመደገፍና የኢትዮጵያ ሕዝቦችም የሚደገፉት በማስመሰል፣ የመንግሥቱ ጋዜጦች በነዚህ ዝግጅቶች ላይ የተነገረውን ሁሉ በሰፊው ጽፈው ያወጡ ነበር::በተለይም በሰተማሪዎችና በሠርቶአደሩ ሕዝብ ትግሎች ላይ ከነዚህ አድሃሪ ሀይሎች ይሰነዘሩ የነበሩትን ዘለፋዎች፣ ማስፈራሪያዎችና መሠረተቢስ ክሶች እንዳሉ በጋዜጦች ላይ ያሰፍሩ ነበር::በዚህ ሁኔታ የአንዳልካቸው መንግሥት — 'መንግሥት' ሊባል ከተቻለ — እስከሚያዝያ መጨረሻ ድረስ ሥልጣኑን በርግጥ ለመያዝና ለመደላደል ቢፍጨረጨርም::የተጠቀመባቸው ዘዴዎች በታሪክ የታወቁት የወዳቂ መደቦች ዘዴዎች ነበሩ:— በአንድ በኩል የማስታረቂያ የማባበያ፣ የማታለያ አርምጃዎች፣ በሌላ በኩል ደግሞ ማስፈራሪያዎች፣ ተንኮሎች፣ ሴራ፡

ቅልጥ ካሉት የማባበያ አጭበርባሪ አርምጃዎች ውስጥ የሕገመንግሥትን አሻሻይ ኮሚሲዮንና የነአንዳልካቸውን የረጅም ጊዜ የማሻሻያ ፕሮግራም ለመጥቀስ ይቻላል::በመንግሥቱ ጋዜጦችም ጥምር ተደጋግሞ እንደተነገረው፣ ዋናው የጊዜው ጥያቄ ሕገመንግሥትን ማሻሻሉ አልነበረም::ይሁንናም፣ ይህ አርምጃ ይወበዓል ከተባለ ወዲያ፣ ሕገመንግሥቱን ያሻሽላሉ ተብለው የተመረጡት ሰዎች ኮበሿሎች የገዥ መደቦች አባሎች ወይንም ደጋፊዎች ናቸው!! ፓርላማው እራሱ ሕገመንግሥትን ያሻሽለው፣ ወይንም የሕገመንግሥት ኤክስፐርቶች መርጦ እንዲያሻሽሉት ያድርግ፣ ወይንም የዩኒቨርሲቲው ኢትዮጵያውያን አስተማሪዎች እንደጠየቁት ሁሉ ሕገመንግሥትን የሚያሻሽሉት ሕብረተሰቡን ከሚወክሉ የሕዝብ ክፍሎችና ድርጅቶች ይውጣ ማለት አንድ ነገሬ ነበር::የአንዳልካቸው መንግሥት በየካቲት እንቅስቃሴ የተባበሩትን ሕብረተሰባዊ ሀይሎች በማሳጉደል ወደጎን ትቶ፣ የዲሞክራሲ ጠር የሆኑትን የጉልተኞችና የቢሮ ከበርቴ ወኪሎችን ዋና የሕገመንግሥት አሻሻዮች አድርጎ አቀረበ!! መቼስ በመደብ ጥቅም ጉዳይ ሀፍረት የለም::ይሉኝታ የለም:: (በነገራችን ላይ፣ የዚያ ታላቅ የሕገመንግሥት ኮሚሲዮን የሥራ ውጤት ከምን እንደደረሰ አልታወቀም::)

ሁለተኛው የአንዳልካቸው መንግሥት ማጭበርበሪያም ከዚህ ከላይኛው እኩል ዓይናውጣ ማታለያ ነበር::በእንቅስቃሴው መጀመሪያ ገደም፣ ማንም ገዥ መደብ በተፈጠረው ሁኔታ ላይ እንዳችም ጥቀጥር ባጣበት ወቅት፣ አንዳልካቸው 'የኔ መንግሥት ጊዜያዊ ነው፣ ሕገመንግሥቱ ከተሻሻለ በኋላ ሥራውን ለመልቀቅ ዝግጁ ነኝ፣ወዘተ'.' ብሎ እንደነበር 'ረስቶ'፣ መንግሥቱ የረጅም ጊዜ 'የማሻሻያ' ፕሮግራም አውጥቶ በርሱ ላይ ትልቅ ጫጫታና ጋጋታ እንዲፈጠር አደረገ::በዚህ ፕሮግራም ይዘት ላይ እንመለስበታለን፣ ዋናው ቁምነገሩ ለማጭበርበር የተሰነዘረ፣ 'ላሊቡ ካቢኔ' ሩታ ለመስጠት የታቀደ መሆኑን እናስታውስ::

ይህ የሚቁበርበር ቱክኒክ ሁሉ አልሠራም። ስለዚህም 'አዲሱ ካቢኔ' በሁለተኛውም ቱክኒክ — በማስፈራሪያና በተንኮል — ይሠራ ጀመር። በግልጽ ማለት ነው። 'አንድነታችን እንዳይፈርስ'፣ 'የውጭ ወሰሮች አሉን'፣ 'ኢኮኖሚያችን እንዳይበላሽ' ወዘተ. የሚለው ሁሉ ማታለያም አልሠራም። ስለዚህም፣ መንግሥቱ ሚያዝያ 15 ቀን ሠራተኞች ሥራ የማቆም መብት እንደሌላቸውና ከእንግዲህ በሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ ልዩ ፈቃድ ማስፈለጉን፣ እነዚህን ትእዛዞች የማይጠብቁ፣ ጸጥታን የሚያደፈርሱ፣ ወዘተ. ይቀጣል የሚል አዋጅ አወጣ። በተጨማሪም፣ ከሠራዊቱ ውስጥ አንዳንዶችን በመግዛትና በመደለል በሠራተኛው ሕዝብ ላይ አንጻነቱና ለመብት የሚያደርገውን ትግል እንዲደመስሱ ለማድረግ ሞከርኩል። ይህ ሁሉ ሴራና ተንኮል ግን ለእነአንዳልካቸው—አቢይ ምንም ውጤት እንዳላመጣላቸው የዚህ የሰኔ ወር መጨረሻ እንቅስቃሴ በማሳየት ላይ አለ....

እንግዲህ የየካቲት እንቅስቃሴ ገዥ መደቦችን ከምን አደረሳቸው ?

ታላላቁ ባላባቶች፣ በንጉሡ ያሉት ወይንም የነበሩት፣ ቀደም በቀጥታ በሥልጣን ባይካፈሉ የቆዩት፣ እንደነእሥራተ ካሣና አቢይ አበበ ያሉት፣ መጀመሪያ ላይ ቀናቸው የመጣላቸው መስሎአቸው ነበር። የነርሱ ወገን የሆነው የተማሩ ባላባቶች ከንፍ ሥልጣኑን ቢይዙ እነርሱም በቀጥታ በገሪቷ አገዛዝ መብተፍን የያዙ መስሎአቸው ነበር። እነርሱም ሆኑ እነአንዳልካቸው ክፉኛ ተሳስተዋል። ንጉሡም ክፉኛ ተሳስቷል። የየካቲት እንቅስቃሴ እንደቀደሞዎቹ የገዥ መደቦች የውስጥ እንቅስቃሴዎች በቤተመንግሥቱ ዙሪያ የተፈጠረ ሴራ አልነበረም፣ አይደለም። መላ ሥርዓቱን ከመሠረቱ ያናጋው ሰፊ የሕዝብ ሪቮሉሺናዊ እንቅስቃሴ በመሆኑ ፈጽሞ ከቁጥጥራቸው ውጭ ሆነኋል። ስለዚህም በጥንቱ የባላባት መደብ ዘርቦታል። ከሕብረተሰቡ ውስጥ መቆርከዝ የለው፣ እንደምኗሉ ዘመን ወደየትውልዱ አውራጃው ሂዶ ገበሬውን አሰልፍ ለማመጽ አይሆንለትም፣ ማስፈራሪያዎቹ፣ ተንኮሎቹና ሴራዎቹ ረከሱ፣ ነፈሰባቸው። ከሁሉ መደብ ተሰባብሮ ደቀቀ የሚወጣ እርሱ ይሆናል።

አሁን ባለንበት ሰዓት፣ እንደነአንዳልካቸው፣ ሚካኤል እምሩ፣ ዘውዴ ገብረሥላሴ ያሉት የተማሩ መሳፍንት እንደምንም ብለው ከወታደሩ ጋር በመሻረክ ሥልጣኑን ይካፈሉት እንደሁ አይታወቅም። በዚህ በሀምሌ ወር መጀመሪያ የሚታዩት የወታደሩ ድርጊቶች ወደዚህ የሚያመሩ ይመስላሉ። ለማንኛውም፣ ለሥልጣን ከሁሉም በላይ ሲንገበገብ የኖረው አንዳልካቸው የወታደሩን ጫማ እየሳመ ይኖራታል እንጂ ከአገዛዙ ለመራቅ አይፈልግም። ተይዞ መታሠርንማ እንደሞት ባይቆጥረው አይቀርም። እነአንዳልካቸው ከወታደሩ ጋር ተስማምተው ሥልጣን ከተካፈሉ፣ በኢትዮጵያ የነበረው የቢሮ ከበርቴና የጉልተኞች ሕብረት በትንሽ ከበርቴና በተማሩ መሳፍንት ሕብረት ተተካ ማለት ነው። የዚህ ዓይነቱ ሕብረት ምን ያህል ሊዘልቅ እንደሚችል ከአሁኑ ለመናገር አይቻለንም። ስለሕብረቱ መሠረት ስለራሱ ገና እርግጠኞች አይደለንም የሚመጡት ቀናት ሳምንታት ወይም ወሮች ያበሩናል።



የነአክሊሉ—አካለወርቅ—ማሞ ታደሰ የቢሮ ከበርቴዎች ሥልጣን ተደምስሷል። መደቡ እራሱ ከእንግዲህ ትስሉን ጠግኖ በቀሉ ወደሥልጣን ለመመለስ መቻሉ ያጠራጥራል።

የገዥ መደቦች ቁንጮና አልቢትር፣ ንጉሠነገሥቱ፣ የነበረውን ፈላጭ—ቆራጭ ሥልጣን በሙሉ ተገፈፈ ለማለት ይቻላል። የወታደሩ ደጋግሞ ለጆሮ እስኪያሰለች ድረስ 'ታማኝነቱን' መግለጽ ይህንን እውነት አይሽረውም። ሀይለሥላሴ ከእንግዲህ የኢትዮጵያ አዲስ ገዢዎች የሚነግሩትን በቴሌቪዥን እየወጣ መናገር ብቻ እንጂ የቀንቱን በርሱ ዙሪያ ይተብተብና ከዚያም የውሰኒዎች ምንጭ ይሆን የነበረውን የቤተመንግሥት የመደለት ሥርዓት ከሥራ ላይ ሊያውለው አይችልም። የዘርዓ ያዕቆብ 'ተጠባባቂ' አልጋወራሽ መሆንና የልኡላን መጣላት—መጋባት የሠርቶአደሩን ሕዝብ ዓይን ወደቤተመንግሥቱ እንዳልሳበ ሁሉ፣ የንጉሡም የድሮውን ለመምሰል መሞከር ማንንም አያታልልም። ለንጉሡም በሞላጎደል አልቀለታል ለማለት ይቻላል።

ይሁን እንጂ፣ በርሱ ላይም ሆነ በቀሩት የገዥ መደቦች ቁና ቁና ሀላፊዎችና አባሎች ላይ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ገና የመጨረሻውን ድል እንዳላገኙ ግልጽ ነው። ንጉሠነገሥቱ፣ ንጉሣዊ ቤተሰብ፣ መሳፍንትና መኳንንት ከሕዝቡ የዘረፉትን መሬትና ሌላም ንብረት ሁሉ ገና አልመለሱም። በኢትዮጵያ ሕዝቦች ላይ ለፈጸሙት ቁጥር ስፍር ለሌለው ወንጀል ገና ከሕዝብ ፊት ቀርበው ፍርዳቸውን አልተቀበሉም። ከዚህ ሁሉም ይልቅ ደግሞ እነርሱ በሕዝቡ ላይ የጫኑትን የመንግሥት መዋቅር ሁሉ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ገና አልሰባበሩትም። ባጭሩ፣ ለኢትዮጵያ ሕዝቦች ዋናው ትግል እንዲያውም ገና ወደፊት የሚመጣ ነው።

ይህንን የገዥ መደቦችን ታሪክ ከመደምደማችን በፊት ሁለት ነገሮችን ለማስታወስ እንወዳለን። የመጀመሪያው የኮምፕራዶር ከበርቴ (ከባእዱ ከበርቴዎች፣ ማለት ከኢምፔሪያሊዝም ጋር የተሻረከ ቱጃር) ጉዳይ ነው። ይህ መደብ ከቢሮ ከበርቴዎች ጋር ተስማምቶ የኢትዮጵያን ወዘደር ሲዘርፍና ሲጠባን ቆይቷል። በየካቲት እንቅስቃሴ ውስጥም ከማን ጋር እንደሚሰለፍ በግልጽ አሳይቷል። የኢትዮጵያ አሠሪዎች ፌደሬሽን ፕሬዚዴንት በቀለ በሻህ ሊያወናብዱ ሲሞክሩ፣ ሥራ ማቆምና ለመብት መታገል 'ከኢትዮጵያ ባህል ውጭ ነው' ቢልና ኢ.ሠ.ኦ.ማ.ን ከስ 'ቢያስፈርድበት' ታይቷል። ሰሎሞን ማህተመሥላሴ ዘጠኝ ሠራተኞችን በየካቲት ምክንያት ከሥራ ሲያስወጣ፣ ገብረሥላሴ ኦዓም በበኩሉ ይህንኑ የመሰለ እርምጃ በመውሰዱ 38 ሠራተኞች አስወጥቷል። እንደዚሁም ከዚህ መደብ ጋር ሆነው የወዘደሩን ጉልበት የሚበዘብዙት የባእዱ ኩባንያዎች ብዙ ወዘደር ከሥራ እንዳስወጡ የታወቀ ነው። በኢሠአማ መሠረት፣ እስከመጋቢት 21 ድረስ 590 ሠራተኞች ከሥራ ተወግደዋል። ለማንኛውም፣ እዚህ ላይ ለማመልከት የፈለግነው ዋናው ነገር፣ የኮምፕራዶር ከበርቴ መደብ ጥቅሙ በደፈናው ከሥርዓቱ መቀጠል ጋር የተያያዘ ስለሆነ፣ የኢትዮጵያ ወዘደር ጠላት መሆኑን ከአሁኑ በበቂ ማሳየቱን ነው። ይሁንናም ይህ መደብ በየካቲት እንቅስቃሴ ምክንያት የደረሰበት ምንም ያህል ጉዳት የለም። የርሱና የወዘደሩ ትግል ገና ወደፊት የሚከር ነው ማለት ነው

ሁለተኛው ነጥብ ሌላውን የከበርቴ መደብ ይመለከታል።እስከዛሬ በተደረጉት የኢትዮጵያ መደቦች ትንተና ውስጥ አልፎ አልፎ ስለብሔራዊ ከበርቴ ተጠቅሷል።አንዳንድ ጓዶች ይህ መደብ አለ ቢሉ፣ ሌሎች ደግሞ በፍጹም ብሔራዊ ከበርቴ የሚባል መደብ የለም፣ ከትንሽ ከበርቴው በላይ ያሉት ኮምፕራዶርና የቢሮ ከበርቴዎች ናቸው ይላሉ።በየካቲት እንቅስቃሴ ውስጥ 'ጴምጽ ካቦሜት' መደቦች ውስጥ የትኛውን ብሔራዊ ከበርቴ ለማለት እንደሚቻል በርግጥም በግልጽ አይታይም።ባለንበት ሁኔታ፣ ወደፊት በቦታው ላይ ጥናት እስኪደረግ ድረስ፣ የዚህን መደብ ጉዳይ ወደጎን ልንተወው ተገደናል።

እንግዲህ የኢትዮጵያን ገጠር መደቦች በሚመለከተው በኩል ባንዳንድ ቁምነገሮች እናጠቃል:-

አንደኛ፣ እነዚህ መደቦች — የቢሮ ከበርቴና የትላልቅ ባላባቶች — በየካቲት እንቅስቃሴ ደቀው ወድቀዋል።የነርሱው አንድ ክንፍ የሆነው የተማሩ መሳፍንት ክንፍ አሁንም በመንግሥት ሥልጣን ዙሪያ እያንፈነፈ ነው።ይህንን ሥልጣን በመወረስ ከትንሽ ከበርቴው ጋር ይካፈለው እንደሁ፣ ወይንም እርሱም እንደነዚያኞች ይወገድ እንደሁ፣ ወይንም ትንሽ ከበርቴውን ከፋፍሎ እርስ በርስ ካጋጨና ካስወገደ በኋላ ዋናውን ሥልጣን እርሱ ይይዝ እንደሁ አሁን ለመናገር አይቻልም።ወጣም ወረደም ነገ፣ ከንግዲህ የገጠር መደቦች ትግል በቢሮ ከበርቴና በትላልቅ ባላባቶች መካከል በመሆን ፈንታ በትንሽ ከበርቴውና በተማሩ መሳፍንት መካከል መሆኑ ነው።

ሁለተኛ፣ የገጠር መደቦችን ያደቀቃቸው የሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል እንደሆነ ግልጽ ነው።ይህ ትግል ደግሞ በተለይ በገጠር መደቦች ውስጥ ግጭት በየጊዜው እንዲናር አድርጓል።ቢሆንም የገጠር መደቦች ግጭት መሠረታዊ ግጭት አይደለም፣ 'አህያ ላህያ ቢራገጥ ...' እንደሚባለው ነው።በነበረው — 'የነበረው' እንበል̣ና — ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ጥላ ሥር በተደረገው ዘረፋ ሁሉም የራሱን ድርሻ ለማሸሸል በወገቡ ካለው ጋር ያደረገው ትንንቅ ነው።በየካቲት እንቅስቃሴ ውስጥ ገጠር መደቦች በአንድነት በንጉሡ ዙሪያ ሲሰበሰቡ ታይተዋል፣ ወደፊትም ሕዝቡን ለመቋቋም በአንድነት እንደሚሰበሰቡ ጥርጥር የለውም።

ሦስተኛ፣ የኢትዮጵያ ገጠር መደቦች የኢምፔሪያሊዝም ቀገኞች ናቸው።ያለርሱ ድጋፍ የሕዝቡ ትግል እንደሚያጠፋቸው ያውቃሉ፣ ስለዚህም ከርሱ አይላቀቁም።አሁን ሥልጣኑን የያዙት ትንሽ ከበርቴዎችም እስካሁን በተናገሩትና በሠሩት እንደሚታየው ከሆነ፣ ፀረ-ኢምፔሪያሊስትነት ፈጽሞ አይታይባቸውም።

አራተኛ፣ የቢሮ ከበርቴና የባላባት መደቦች ፀረሕዝብና ፀረ ዲሞክራሲ ናቸው። አሁን ሥልጣን የያዙትየትንሽ ከበርቴው መደብ አባላትም ይህንኑ ጎዳና ይከተሉት እንደሁ በቅርቡ ይታያል።ወጣም ወረደም፣ ከዚህ በላይ እንደተባለው ሁሉ፣ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ገና እውነተኛ ነጻነትን አላገኙትም፣ ዋናው ትግል ወደፊት ነው።



(ለ) <u>የትንሽ ከበርቴ መደብ</u>

የዚህ መደብ አባላት እነማን ናቸው ?

እስካሁን በተደረጉት ትንተናዎች መሠረት፣ ይህ መደብ የሚከተሉትን የሕዝብ ክፍሎች ያጠቃልላል:- ዝቅተኛ የፖሊስና የጦር መኮንኖች፣ ተማሪዎች፣ መምህራን፣ ዝቅተኛ የቢሮ ሠራተኞች፣ ዝቅተኛ ነጋዴዎች፣ በጠቅላላም በሕብረተሰቡ ውስጥ መሀልቦታ፣ መሀል የሀብት መጠን፣ የኑሮ ዘዴና አስተሳሰብ ያላቸው ሁሉ የከበርቴ መደብ አባላት ናቸው።ለምሳሌም በየካቲት እንቅስቃሴ የተሳተፉት እንደ ጋዜጠኞችና ሕግ አስከባሪዎች ያሉት — 'ምሁራን' ሊባሉ ይችሉ እንደሆነ እናውቅም እንጂ — ክፍሎች ወደዚሁ የሚቀጠሩ ናቸው።

ትንሽ ከበርቴው በሕብረተሰባዊ ቦታው በከበርቴውና በወዛደሩ መካከል ነው።'ከቀናው' ወደላይኛው መደብ፣ ወደከበርቴው ይሸጋገራል፣ ከከሰረ ደግሞ ወደወዛደሩ መደብ ይወርዳል።እንደሚባለው ሁሉ፣ 'ባንድ ጊዜ ከበርቴም የሕዝብ ሰውም ነው'።ከዚህ አቋሙ የተነሣ ወላዋይ ጠባይን ያሳያል።ምንም እንኳ የየካቲት እንቅስቃሴ መሪ መደብ ቢሆንም፣ ምንም እንኳ ከሌላው ሁሉ መደብ ይበልጥ መሠረታዊ ጥያቄዎችን ያቀረበው የዚህ መደብ አንድ ክንፍ ቢሆንም፣ ጠቅላላ መደቡ ይህንን ወላዋይ ጠባዩን ማሳየቱ አልቀረም።ይህንን ነጥብ ከዚህ በታች እንመለስበታለን፣ ግን አንዲት ምሳሌ ካሁኑ ለመስጠት ያህል፣ የኢትዮጵያ ሠራተኞች አንድነት ማህበር — ኢሠአማ — መሪዎች በየካቲት 11 ቀን ፖሊስ ተማሪና አስተማሪን ደብድቦ ብዙ ሰው በተገደለበት ወቅት የጠቅላላ ሥራ ማቆም ጥሪ አላደረጉም። የወታደሩን ማመጽ መጠበቅ ነበረባቸው።ምናልባት ይህ የወታደር አመጽ በይናር ናር ጠቅላላ የሥራ ማቆሙም ባልተደረገ ነበር።አመራሩ የትንሽ ከበርቴ መደብ በመሆኑ የፊቀነትና ድፍረትን አላሳየም።በሌላ በኩል ግን ወዛደሩ ጥሪውን ተቀብሎ እንደአንድ ሰው ሆኖ በታላቁ ዲሲፕሊን የታዘዘውን ከመፈጸም በላይ በየቦታው የራሱን ነጻ እርምጃዎች በመውሰድ ወገኖችን አሰበርታጓል።በሁለቱ መደቦች አቀራረብ መካከል ልዩነት አለ:- ወዛደሩ በመታገሉ ምንም የሚቀርበት ነገር ስለሌለ በድፍረት ይታገላል፣ ትንሽ ከበርቴው ግን ያችን ያለችውን እንዳያጣ ሲል ያመነታል።

የኢትዮጵያ ትንሽ ከበርቴ በየካቲት እንቅስቃሴ ከዳር እስከዳር ተሳትፎአል።እንኳንስ እዚያ በቦታው ላይ ያለው ተርፎ፣ እዚህ ውጭ ያለውም እንኳን በግብርም ሆነ በአፍ ወይንም በምኞት በትግሉ ተሳትፎአል።አዲስ ዜና ከትግሉ ጋራ በመጣ ቁጥር ልቡ ትር ትር ብሏል።

ሙሉ መደቡ በትግሉ ተሳትፎአል፣ ጥያቄዎችን ደርድሯል፣ በዛሬው ሁኔታ የሠርቶአደሩ ሕዝብ ወገን መሆኑን አሳይቷል።ይሁን እንጂ፣ ይህ ጠቅላላ መደቡን ስንመለከት ነው፣ ዝርዝር ውስጥ በሚገባበት ጊዜ አንዱ ክፍል ከሌላው ይበልጥ የራቀ፣ ወይም ንቁ፣ ወይንም ደግሞ ከሌላው ይበልጥ ወላዋይ፣ አድርባይ፣ ወሬኛ ሆኖ እናገኛለን።የትንሽ ከበርቴው

መደብ በዚህ አኳኋን እንደተሰተደመና የተሸጉረጉረ ቀለሙን አበይቶናል፤ በስተግራ በኩል ቀላ ብሎ ከዚያም ብርቱካን፤ ብጫ... ይሆንና በስተቀኝ በኩል በሰማያዊ ያልቃል::

ቆራጥነትንና ጽናትን ከበዩት ውስጥ አንዱ ክፍል የተማሪው ነው::በለፈት አሥር ዓመታት ሁሉ ተማሪው እንዳችም መሥዋእት ባይፈራ ከሥርዓቱ ጋር ሲጋፈጥ እንደቆየ ከዚህ በላይ በሌላ ቦታ አይተናል::በየካቲት አብዮቱም ያላንዳች ማወላወል ከስተማሪዎችና ከ ታክሲ ነጂዎች ጋር በመሰለፍ ተቀገተ ብዙው ሕይወቱን አሳልፎ እስከመስጠት ደርሷል::በተ ረፈም፤ በየካቲት ዋና መሰለፊያና የድርድር ነጥቦች የሆኑትን እንደነ'መሬት ላራሹ'ን፤ 'ትምህርት ለሁሉ' ወዘተ. መፈክሪያ ያበረከተ ይህው ክፍል መሆኑ መረሳት የለበትም:: ምናልባት አንዳንድ ጊዜ ተወናበደ ሊሆን ይችላል፤ አንዳንዴም እራሱን እንደኢትዮጵያ ሬቮ ሉሽን መሪ የቆጠረበት ወቅት ነበር፤ አንዳንዴም የማያዋጡ እርምጃዎችን ወስዶ ይሆናል፤ አሁንም ወታደሩ ሥልጣኑን በለያዘ ምናልባት ላብዙው ትግሉ ያለቀ ሊመስለው ይችላል::ነገ ርግን ይህ የሕብረተሰብችን ክፍል ከሁሉ ተጋዳይ ከሆኑት ውስጥ መሆኑን አስመስክሯል::

ከዚሁ ጋር ተያይዞ፤ ለየካቲት አብዮቱ አንደኛው ለኳሽ የሆኑት 18 ሺው የኢ ትዮጵያ አስተማሪዎች ፍጹም ታይቶ የማይታወቅ፤ ወደወዛደሩ መደብ የሚጠጋ ዓይነት ዲሲፕሊ ን አሳይተዋል::በቀረቧቸው ጥያቄዎችና አንድ ወር ሙሉ ሥራ በማቆማቸው የዝቀተኛ በሳበቶ ች፤ የተሸው ወታደሮችና ያድሃሪው ሥርዓት ደጋፊዎች ሁሉ የዘለፉ ማረፊያ ሆነው ነበር፤ ነገ ይህ ሁሉ ተቀኒነታቸውን አልቀነሰውም፤ እንዲያውም ያድሃሪዎችን ማስፈራሪያ ሁሉ በ ሚያስደንቅ ታታሪነት ተቋቁመውታል::

ትንሽ ከበርቴው በየካቲት አንቀሳቃሴ ያነሣቸውን ጥያቄዎች ሁሉ እዚህ ላይ እንደ ገና ለመጥቀስ አይቻልም::እነዚህ ወደፊት ተጠቃለው ይቀርባሉ::በጭሩ ግን፤ ሕገአስከባሪ ዎችና የወረዳ ዳኞች፤ ዘፋኞችና የቲአትር ተዋናዮች ሳይቀሩ በሥርዓቱ ላይ በመነሣት፤ ጊዜያዊም ሆኑ ዘላቂ ጥያቄዎችን አቀርበዋል::እዚህ ላይ ግን ለማሳየት የምንፈልገው፤ በ ጠቅላላው መደቡን ዓይነተኛ የሚያደርጉትን አንዳንድ ድርጊቶችን ነው::በዚህም በኩል፤ የ መንግሥቱን ጋዜጠኞች እዚህ ላይ ለማውሳት እንወዳለን::

ከትንሽ ከበርቴው ውስጥ በጣም ወራዳና ሙልጭ ያለ አድርባይነትን ያሳየ ክፍል ይ ህኛው የጋዜጠኞች ክፍል ነው::በየካቲት 11 ዙሪያ በሳማዊ ሰልፍ በማድረግና አውቶቡሶች ን በመውገር ከስተማሪዎችና ከታክሲ ነጂዎች ጋር ተሰልፎ ሥርዓቱን ያረወጠውን ተማሪን 'አንዳንድ ወንበዴዎች' እያሉ እንደተለመደው ያወግዟቸው ነበር::ያኔ የጋዜጠኛው ሰልፍ ከነይልማ ሺበሺ ጋር ነበር ማለት ነው::ወታደሩ አሥመራንና አዲስአበባን ይዞ እነአክሊሉ ከወደቁ በኋላና ጋዜጠኞቻችን 'መተንፈስ' እንደጀመሩ ወዲያው የወታደሩን ጣማ መላስ ያዙ 'ቢተነፍሱም' እነአክሊሉን ከሳወገዙ አይሆንላቸውም ነበር::ወደኋላ ግን የሕዝቡ ትግል ሲፋፋም ክፉኛ ተደናግጠው ፍጹም ፋሺስታዊ የሆኑ እርምጃዎች እንዲወሰዱበት ይጠይቁ ጀመር



'የኢትዮጵያ ሕዝብ ነጻነትን አይፈልግም'፤ 'የኢትዮጵያ ሕዝብ ዲሞክራሲን እንደማይፈልግ አሳይቷል'፤ 'ጥጥር ይደረግበን' ወዘተ. እያሉ፤ ፍጹም ፊደልን ለቆጠ ረ ሁሉ አሳፋሪ የሆኑ አቋሞች ወስደዋል::ትምር እንደነርሱ ከመሆን እንደዘጠና በመቶው የኢትዮጵያ ሕዝብ መሃይም መሆኑ ይሻላል የሚያሰኙ ፍሬከርስኪ ጽፈዋል::በተጨማሪም 'የ ኢትዮጵያ ሕዝብ ሳዊሉ ከቢኔ አዱል አንስጥ ብሏል' እያሉ፤ የረባቸውን እንኳ የሕዝቡ በ ማስመሰል ዓይናወጣ ሀሰት በመንዛት የአንዳልካቸውንም ጣማ ለጥቂት ቀናት ላልሰዋል!!እነ ዚህ ፍጹም አድርባዮች ገራም ነፈሰ ቀኝም ነፈሰ በለጊዜውን እያወደሱ መኖር እንጂ የሕዝ ቡን ወገን መርጦ መታገል እንደማይሆናቸው በሚገባ አሳይተዋል::

በበኩሉ፤ በይወዱ የግድ ሆኖበት የሕዝቡ ቁጣ በሥርዓቱ ላይ እንዲነሣ ተጠማሪ ቀስቃሽ የሆነው ወታደር — ማለት፤ ለወታደሩ አንቀሳቃሴ መሪ የሆኑት ዝቅተኛ መኮንኖች — እርሱም የመደቡን ደንበኛ ወላዋይነት አሳይቷል::የአሥመራ፤ ያዲስአበባ፤ የሐረር መያ ዝና መለቀቅ አንድ ትልቅ ምስክር ይመስለናል::የቀዳሚዎቹ ሚኒስትሮች መጀመሪያ መያዝ፤ ከዚያም መለቀቅ፤ ከዚያም እንደገና መያዝም እንደዚሁ::ወታደር ከመጀመሪያውም ምን እንደ ፈለገ ለራሱ ገልጽ ሆኖለት የነበረ አይመስልም::ከዚህ በላይ፤ በዚህ ምዕራፍ መጀመሪያ ላይ እንደገለጽነው ሁሉ፤ ስለወታደሩ ውስጣዊ ሁኔታ ብዙ ዜና ይጎድሉናል::ስለዚህም እሁ ን ቁርጥ ለመናገር ያዳግታል::

በጥር በቦረና ያመፁት፤ የካቲት 19 ቀን አሥመራን የያዙት፤ የካቲት 21 ቀን አዲስአበባን የያዙት ወታደሮች አርስ በርስ ግንኙነት ነበራቸው ወይ ? አየር ሀይል፤ ባህር ሀይል፤ የሐረር አካዳሚ፤ እነዚህስ ? በየካቲት 30 ቀን 'አገሪቷ ወደጥፋት ስትጓዝ ዝም ብለን አናይም' ያሉትና ቀጥለውም እነቴሌን እነመብራት ሀይልን አስገድደው ያሠሩት የትኞች ወታደሮች ናቸው? 'የጊዜያዊ ፕሮብሌሞች በሳማዊ መፍትሔ አቀናባሪ ኮሚቴ' — የነዓለም ዘወዱ ተሰማ ኮሚቴ — እና የዘረው 'የጦር ሀይሉች አቀናባሪ ኮሚቴ' ምን ግንኙት አላቸው ? መዓት ያልተብራሩ ጥያቄዎች አሉ::ስለዚህም፤ ለጊዜው አንዳንድ የተ ወበጡ ድርጊቶችን በመመርመርና በነርሱ ላይ ተመርኩዘን አንዳንድ መደምደሚያዎችን ብቻ እንድናወጣ ተገደናል:—

ወታደሩ ተሰማምቶ አመጸ አሳመጸ፤ የየካቲት ድርጊቱ፤ ከዚህ በላይ እንደጠቀስነው ሁሉ፤ ወላዋይነትን ቁልጭ አድርጎ ያሳያል::እንደተባለው የሰዎች መያዝና መለቀቅ፤ የዜተ ዎች መያዝና መለቀቅ፤ አንድ ቀን የሕዝብ ወገን ነኝ ብሎ በሚቀጥለው ቀን በሰደፍ እያሰ ፈራሩ ማሠራት፤ ከሁሉም በላይ ደግሞ ሥልጣኑን ለመጨበጥ ማመንታት፤ ወዘተ. እነዚህ ሁሉ ድርጊቶች የዘረዎችን በለሥልጣኖች ወላዋይነትና ደግሞም በፖለቲካ ወደኋላ መቅረት በሚገባ የሚያሳዩ ይመስለናል::

ወታደር የመንግሥትን ሥልጣን እንዲይዝ በመፈለግ ወይንም በመመኘት ሳይሆን፣ ስለየካቲት የወታደሮች እንቅስቃሴ አንድ የማይካድ ሀቅ አለ:— የኢትዮጵያ ወታደሮች ሥልጣንን እንደሚያያትል አብት መጠበቅ ፈርተው መቆየታቸው ነው::ቅድስተ ቅዱሳን ወደሚባለው ወደታቦተ መቀመጫ መግበት እንደሚፈራ መሃይም ነበር ወታደሩ የተንቀጠቀጠው::ልንካ አልንካ ብሎ ቢያመነታ አረት ወረት አበልፏል::አሁን በመጨረሻ አገኘሁ ብሎ ያቀረበውም የሥልጣን እያያዝ ይህንኑ ሚመንታትን ያረጋግጣል::በተረፈም፣ አሁን ወታደሩ በሕልም ዓለም ውስጥ በመዋለል ላይ ያለ ይመስላል::

እንግዲህ ወላዋይነት አለ::በዚያ ላይ ደግሞ፣ ከነዓንዱ ድርጊቶች ለመገመት እንደሚቻለው ሁሉ፣ በውስጡ ክፍፍል አለ::ይህኛው የመጨረሻው ነጥብ የወታደሩን የፖለቲካ ንቃት ዝቅተኛነት ያመለክታል::ከዚህም በላይ ግን ሌሎችን፣ ለዚህ የንቃት ዝቅተኛነት ተጠባቂ ምስክር የሚሆኑ ሁኔታዎችን ለመጥቀስ ይቻላል::ከነዚህ ውስጥ የመጀመሪያው ሠራዊቱ ደጋግሞ ለንጉሡ ታማኝነቱን መግለጹ ነው::የዚህ ትርጉም፣ እንዳንዱ የምእራብ ጋዜጦች እንዳሉትም ሁሉ፣ ንጉሡ ከተነካ ወይንም ዘውዱ ከተነካ ገጠሩ በከተማው ላይ፣ በወታደሩ ላይ ይዘምታል፣ አገር ተከፋፍሎ እርስበርሱ ይፋጃል፣ ወዘተ. የሚል ፍራቻ ነው::ይህ መቼስ ፈጽሞ ከተጨባጩ ሁኔታ የራቀ 'ትንተና' ነው::የኢትዮጵያ ገበሬ፣ የሰሜኑም ሆነ የደቡቡ — በተለይም ደግሞ ይህኛው — በፍጹም ለንጉሠ ነገሥትም ሆነ ለዘውዱ ደንታ የለውም::በተጨማሪም፣የየካቲት እንቅስቃሴ አንዱ ቁልፍ አድርጎ ያሳየው እውነት ቢኖር፣ ከሠራዊቱና ከፖሊስ ውጭ የንጉሡ የራሱ የሥልጣን መሠረት የመነመነ መሆኑን ነው::የገጠሩ ዝቅተኛ ባላባት እንኳን 'ለንጉሥ' ብሎ ይቅርና 'ለሃይማኖትህ' እንኳን ቢል በዘረውዘመን ተከታይ የሚያገኝ አይመስለንም::ስለዚህም የወታደሩ ፍራቻ በርግጥ በዚህ 'ንቃት' ላይ የተመሠረተ ከሆነ፣ በፖለቲካ በኩል ወደኋላ ቀርቷል ማለት ነው::

ለዚህ ወደኋላ መቅረት ሌላ ምስክር ለማምጣት ይቻላል::ይህውም የእንዳልካቸው መኮንን 'በሥልጣን ላይ' መቆየት ነው::እርግጥ ዋናዎቹ ደጋፊዎች እነእምሬተ ካሣ እነአቢይ አበበ ስለተወገዱና በጠቅላላውም ወታደሩ በሲቪሉ 'መንግሥት' ላይ ቁጥጥር ስላለው ይህ የእንዳልካቸው በሥራ ፈጻሚነት መቆየት ምንም ልዩነት አያመጣም ሊባል ይችላል::ግን በሙያው የታወቀ ዘራፊ ከመሆኑም በላይ በቤተመንግሥት ዙሪያ በመደለሉ፣ በሴራ፣ በተንኮል የሰለጠነ ስለሆነ፣ ብዙ ተንኮሎችን ሊተበትብ የሚችል ባይታሰርም የተፈታ ነው::በተረፈም፣ ከመሰሎቹ ጋር ፍርዱን መቀበል የሚገባው ሰው አሁንም እንደዚያ ነፃ መሆኑ ፍጹም የማያደናግር ነገር ነው::

ወታደሩ በሀምሌ ሁለት ባወጣቸው አምፊ በስት ነጥቦች ላይ በሌላ ቦታ እንመለስበታለን::ግን ለፖለቲካ ንቃቱ ደረጃ አንድ የመጨረሻ ምስክር ያመራሩ እስካሁን በይፋ አለመውጣቱ መሆኑን እዚህ ላይ እናስታውስ::



እንግዲህ ጠቅላላውን የትንሹ ከበርቴውን ሚና በሚመለከተው በኩል እንደምድም:: ይህ መደብ በጠቅላላው በየካቲት እንቅስቃሴ ውስጥ ዋናው ተዋናይና መሪ ነበር::ሀይለኛ ፀረፈሳጭ ፕረጭና ዲሞክራሲያዊ ትግል አድርጓል::ከሁሉ የነቃው ክንፉ ፀረኢምፔሪያሊስት ጥያቄዎችን ጭምር አቅርቧል፣ ከሁሉ አድሃሪ የሆነው ክንፉም በሕዝቡ ላይ ፋሺስታዊ እርምጃዎች እንዲወሰዱ እስከመጠየቅ ደርሷል፣ በተረፈም በወታደር ውስጥ ያለው የዚህ መደብ ወኪል ክንፍ በመንግሥት ሥልጣን ውድድር ውስጥ ገብቷል፣ ምናልባትም ሥልጣኑን ይይዛል:: ጠቅላላ መደቡ እስከዛሬ ባሳየው ትግል የሕዝብ ወገን መሆኑን አስመስክሯል::

(ሐ) <u>የገበሬው መደብ</u>::

እንደሚታወቀው፣ በሰሜንና በደቡብ ኢትዮጵያ የዚህ መደብ ሁኔታ ይለያያል::በሰሜኑ አገር የጭሰኛ ቁጥር አነስተኛ ሆኖ ሳለ፣ ገበሬው የራሱ ትሬፍ ማሳ እያለችው፣ ለራሱ በቂ ለማምረት ስለማይችል ለባለ ትልልቅ መሬቶች በኪራይ ወይንም በመጋዝ ለመሥራት ይገደዳል::እንደዚያም ሆኖ በያመቱ ባይሻለው እንዲያውም እየባሰበት ሄዶ በነዚህ ባለፉት አራት አምስት ዓመታት ውስጥ ስንቱ የገበሬ ቤተሰብ በችጋር አልቋል::

በደቡብ፣ ምኒልክ ባለፈው ክፍለዘመን መጨረሻ በያዛቸው አገሮች፣ ይበልጡ ገበሬ ጭሰኛ ነው::ሁኔታውም በጣም አሰቃቂ መሆኑ የታወቀ ነው::እንዲያውም በነዓንዱ ቦታዎች መሬትን ተነጥረሹ ተቀምጦ፣ የጭሰኝነትንም መብት እንዲያጣና መሬቱ ለዘመናዊ እርሻ እንዲውል ስለተደረገ፣ ፈጽሞ መኖሪያ ያጣ ገበሬ ብዙ ሚሊዮን ይሆናል::

በየካቲት አማካኝነት በግልጽ መናገር ተጀምሯል፣ የሲዳሞ ጠቅላይ ግዛት የሕዝብ እንደራሴዎች በፓርላማው ውስጥ የሚቀጥለውን ሁኔታ ገልጸዋል:— በሲዳማ፣ በጀምጀምና በአርፎርኸውራጃዎች ያሉት ጭሰኞች ከምርታቸው ግማሽ ለባለመሬቱ ይሰጣሉ:: ግን ይህ ብቻ አይደለም::ጭሰኛው፣ ሚስቱና ልጆቹ ለባለመሬቱ በየጊዜው ባባሳሽ የጉልበት ሥራ መሥራት አለባቸው::በተጨማሪም፣ በያመቱ በዓሉ ጭሰኛው ለባለመሬቱ በጎችና ፍየሎች መስጠት አለበት: በዚህ ዓመቱ ሩቢካ አንዱ ባለመሬት በዚህ መልክ 280 በጎችን ከሕዝብ እንደዘረፈ አንዱ እንደራሴ ገልጸዋል::

በደቡብ ኢትዮጵያ ያለው የገበሬ መደብ ሁኔታ ይህ ስለሆነ፣ በአንድ በኩል ዛሬ በደቡብ ኢትዮጵያም ረሀብ መግባቱ አያስደንቅም፣ በሌላ በኩል ደግሞ የገበሬው የማያቋርጥ ትግል በዚህ ሁኔታ በቀላሉ ሊገባን ይችላል::በየካቲት እንቅስቃሴ ውስጥ በጠቅላላው የደቡቡ ገበሬ 'መሬት ላራሹ' እራሱ በገዛ እጁ ከሥራ ላይ ለማዋል ሲታገል፣ በሰሜን ኢትዮጵያ ደግሞ አድሓሪ ባለሥልጣኖችን በመቃወም ተነሥቷል::እንደሚታወቀውና ከዚህ በላይ በዚህ ጽሁፍ መጀመሪያ ክፍል እንደተጠቀሰው ሁሉ፣ ረሀብ በገባባቸው በወሎ፣ በትግራይና በሰሜን ሸዋ ገበሬው ሀብታም ባለመሬቶችን እየገደለ ንብረቶቻቸውን ዘርፏል::

በዚህ ባሁኑ እንቅስቃሴ በመላ ኢትዮጵያና በውጭ አገርም ድረስ የታወቀው የገበሬዎች ተጋድሎ ከመጋቢት 4 እስከ 8 ድረስ የቆየው የመቂ ገበሬዎች እንቅስቃሴ ነው። በዚህች በአሩሲ ውስጥ በምትገኝ ከተማ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ገበሬዎች በመጀመሪያ መሬቶቻቸውን ለቀሟቸው ሀብታሞች መሬቱን በሶስት ቀን ውስጥ እንዲለቁ ማስጠንቀቂያ ሰጡ። መሬቱ ባይለቀቁ ቢቀር ገበሬዎች ዘመናዊ እርሻዎችን አጥቅተው ሰብሉን አቃጠሉ። ፖሊስ ለሀብታሞቹ በመቆም ከነርሱ ጋር ተጋጭቶ 11 ሰው ሞተ። ከዚህ በኋላም በሚያዝያ 1 ቀን በአሰላ ከተማ ከተሰለፉት 15 ሺ ሰዎች ውስጥ ብዙዎቹ ገበሬዎች እንደነበሩ ታውቋል። በሰልፉው ተይዘው ከነበሩት ሰሌዳዎች ውስጥ ቀንደኛው 'መሬት ላራሹ' ነበር።

ከዚህ በፊት ተደጋግሞ እንደተነገረው፣ በደቡብ ኢትዮጵያ የመሬትና የብሔረሰብ ጥያቄ በጣም የተያያዙ ነገሮች ናቸው። መሬትን የተቀማው ሕዝብ የነፍጠኞች ጭሰኛ ሆኗል፡ በተለይም በሐረርጌ፣ በባሌ፣ በአሩሲ፣ በሲዳሞ፤ በጋሙ ጎፋ ያሉት ነዋሪዎች — ይበልጦቹ የኦሮሞ ብሔረሰብ አባሎች — በሙሉ ጉደል ጭሰኞች ከመሆናቸውም በላይ፣ በቋንቋና በሃይማኖት ከነፍጠኞች ይለያሉ። ስለዚህም ባለፉት አሥር ዓመታት ውስጥ በነዚህ ክፍሎች የተደረገው ትግል ሁሉ፣ በተለይም የባሌው ትግል፣ የብሔረሰብን መልክ ይዞ መቅረቡ አያስደንቅም።

ከዚህ በላይ የተጠቀሰውም የመቂ ትግል ይህንኑ መልክ ባያሳይ ኖሮ፣ የመንግሥት ፖሊሶች በጋዜጣቸው 'አንዳንድ ሰዎች እንዳሉት የጎሣ ጠባይ የለውም' በማለት ማስተባበል ባላስፈለጋቸው ነበር።

'መሬት ላራሹ' የሚለው መሪ ቃል በኢትዮጵያ ጭሰኞች ዘንድ ከነገሢህ በደንብ ተለምዷል። የየካቲት እንቅስቃሴ እንደጀመረ በአንዳንድ ገጠሮች ሕዝቡ መሬትን መልሶ መውሰድ ስለጀመረ፣ የእንዳልካቸው መንግሥት በሚያዘው ጋዜጣ 'መሬት ላራሹ ማለት አሁኑኑ መሬት ውሰዱ ማለት አይደለም .. ወዘተ.' እያለ ለገበሬው ማስጠንቀቂያ ለማውጣት ተገዶ ነበር በተጨማሪም፣ እንደነሸበሩ ሰይፉ ያሉት ባለመሬቶች በነዚህ በመንግሥት ጋዜጦች ውስጥ ደጋግመው 'ባባት ርስትና በሚስት የለም ቀዝ' እያሉ፣ ያውም ገና ለገና የእንዳልካቸው መንግሥት የመሬት ድልድል ያደርጋል ብለው፣ ገበሬውንና ለርሱ መብት የቆመውን ሁሉ ማስፈራራት ይዘው ነበር። እነዚህ ጉበዞች የሚሉት መሬትን የተነጠቀው ገበሬ የተነጠቀውን መልሶ በመውሰዱ ፈንታ ወደበረሃ፣ ወደ'መንግሥት' መሬት ተልኮ ይተከል ነው። እነርሱ ገን ከሕዝቡ በቀማት መሬት ላይ ዘመናዊ እርሻን ያስፋፉበታል።

በዛሬይቱ ኢትዮጵያ የመሬት ጉዳይ ዋና ጉዳይ እንደሆነ ሁሉ፣ የገበሬውም — ማለት የጭሰኛውና የድሀ ገበሬው — መደብ የመጪው ሕዝባዊ ረቮሉሽን ዋና የጉልበት ምንጭ ነው። ይህ መደብ እውነተኛ የመሬት ድልድልን ሊያገኝ የሚችለው፣ 'መሬት ላራሹ' በርግጥ ከሥራ ላይ ሊውል የሚችለው፣ ሰፊው ገበሬ ከወዛደሩ ጋር ሕብረት ቢፈጥርና በርሱ አመራር ሥር የርሻ ረቮሉሽኑን ቢያከናውን ብቻ ነው። ለዚህም ሥራ የገበሬው መደብ ዝግጁ መሆኑን የየካቲት እንቅስቃሴዎች በመጠኑም ቢሆን ያበቁ ለመሆናቸው ጥርጥር የለውም።



## (መ) ወዛደር መደብ

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር መጽሔቶች ውስጥ ስለዚህ መደብ ሲነገር ብዙውን ጊዜ 'የሠራተኛ መደብ' ሲባል ቆይቷል። ምንም እንኳን በገራችንም የተለመደው አጠራር ይህው ቢሆንም፣ — ለምሳሌ 'የኢት. ሠራተኞች አንድነት ማህበር'፣'የሠራተኛ ድምፅ' ይባላል — ምናልባት ወዛደር ወይንም ላብአደር በሚለው ቃል መጠቀም ቢለመድ ሳይሻል አይቀርም። ያለበለዚያ 'ሠራተኛ' የሚለው ቃል የቢሮ ሠራተኛውንም ስለሚጨምር ሁለት መደቦችን፣ የወዛደሩንና የትንሽ ከበርቴውን፣ የማምታታት አደጋ ሊኖርበት ይችላል። ለማንኛውም፣ ቢያንስ አሁን በያዝነው የጽሁፍ ክፍል ውስጥ፣ ልማዱን በመቋቋም፣ ወዛደር በሚለው መጠሪያ እንጠቀማለን።

ወዛደር የሚባለው ማነው ? ወዛደር ማለት ምንም ዐይነት የግል ሀብት ሳይኖረው ለመተዳደሪያ በቀጥታ የሥራ ጉልበትን ብቻ እየሸጠ የሚኖር ሁሉ ነው። ስለዚህም፣ ባንዱ በኩል በቀለም ትምህርት ከሚጠቀመው የቢሮ ሠራተኛና የራሱ ትንሽ 'መንቀብቀቢ' ገበረት ካላቸው ነጋዴ ሲለይ፣ በሌላ በኩል ደግሞ መሬትን እያረሰ ከሚኖረው ገበሬ ይለያል። የወዛደር መደብ አባሎች ብዙ ሆነው የሚገኙት በከተሞችና በወደቦች ውስጥ፣ በየፋብሪካው፣ በቤትና በመንገድ ሥራ ቦታዎች፣ በትላልቅ ዘመናዊ እርሻዎች ላይ፣ በማእድኖችና በመሳሰሉት የሥራ ጉልበት በሚፈለግባቸው ቦታዎች ናቸው።

የከበርቴ — ካፒታሊስት — ኢኮኖሚ፣ ማለት ገንዘብን በፋብሪካዎች፣ በዘመናዊ እርሻዎች፣ በትላልቅ ንግዶች ወዘተ. አውሎ በዚህ አኳኋን ሀብትን የማካበር ኢኮኖሚ ወዳገራችን የገባው የገባው በቅርቡ ነው። ብዙ ሺ የሚቆጠሩትን ወዛደሮች የሚቀጥሩት ትላልቅ ኩባንያዎች ከተቋቋሙ አሥራ አምስት ወይንም ሀያ ዓመት ገደማ ቢሆናቸው ነው። በያመቱ ከ10 000 ወዛደር በላይ የሚቀጥረው የወንጂ ስኳር፣ 3000 ወዛደሮች ያሉት የድሬዳዋ የጥጥ ኩባንያ፣ 2500 ወዛደሮችን የያዘው ያቲ የጨርቅ ፋብሪካ ወዘተ. የተቋቋሙት ባለፉት ሀያ ዓመታት ውስጥ ነው። ትላልቆች፣ ብዙ ሺ የሚቆጠሩ ወዛደሮችን የሚቀጥሩ እርሻዎች፣ እንደነተንዳሆ፣ እንደነሰቲት ሁመራ ያሉት በቅርብ የተቋቋሙ ናቸው። ባጭሩ፣ ዛሬ በኢትዮጵያ የሚገኘው እንዱስትሪ ሁሉ የረጅም ጊዜ ታሪክ የለውም።

ከጭሰኝነት አለመጥፋትና ከጉልተኛው ሥርዓት አለመለወጥ የተነሣ፣ ባገሪቷ የሚታየው የኢንዱስትሪ እድገት በማንኛውም ሚዛን ቢሆን በጣም ዝቅተኛ ነው። በ1962 በኢትዮጵያ ይገኙ ከነበሩት 479 ፋብሪካዎች፣ ከትላልቆቹ የጨርቃጨርቅ ፋብሪካዎች በስተቀር — እነዚህም አንድ አሥር ናቸው — የቀሩት ሁሉ በአውሮፓ ዓይን የመንደር እንዱስትሪዎች እንጂ እውነተኛ ፋብሪካዎች ሊባሉ አይችሉም። በመንግሥት ስታቲስቲኮች መሠረት፣ በነዚህ ፋብሪካዎች ውስጥ የሚሠሩት ወዛደሮች ቁጥር በ1962፣ 48 ሺ 903 ነበር። ከነዚህ ውስጥ ወደ 22 ሺው በጨርቃጨርቅ ፋብሪካዎች ውስጥ የሚሠሩ ናቸው።

የዛሬ ዓመት ከፍጻሜ የደረሰው 'በስተኛው ያምስት ዓመት ፕላን' ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ የጎማ፣ የወረቀት፣ የመሬት ማልሚያ — ፊርቲላይዘር — የመኪና ባትሪዎች ፋብሪካዎችና በተለይም የጭንቅኪና፣ የትራክተርና የአውቶቡስ መገጣጠሚያ ፋብሪካ በማቋቋም ብዙ የሥራ ቦታዎችን ይፈጥራል ተብሎ ነበር፡፡ከነዚህ ውስጥ ምንም ያህል ከሥራ ላይ ስላልዋሉ፣ በ1959 44ሺ የነበረው የፋብሪካ ወዛደር ቁጥር በፕላኑ መሀል ላይ 49 ሺ ብቻ ነበር፣ ዛሬም ምናልባት ወደ 60–65 ሺ ብቻ ቢሆን ነው፡፡ከዚህ ከፋብሪካ ወዛደር ጋር የቀረውንም ሁሉ ብንደምር ምናልባት ዛሬ የዚህ መደብ አባሎች ከግማሽ ሚሊዮን አይበልጡም፡፡ከጠቅላላ ያገሪቱ ሕዝብ ቁጥር ጋር ሲመሰሰሉ በጣም ጥቂት ናቸው ማለት ነው፡፡

እንግዲህ በኢትዮጵያ የከበርቴ ኢኮኖሚ አዲስ ነው፣ በዚያ ላይ ደግሞ አልተስፋፋም ብለናል፡፡ይሁን እንጂ፣ ይህ ትንሹ የከበርቴ ኢኮኖሚም ቢሆን፣ ከዚህ በላይ በሌላ ቦታ ጠቀስነው እንደነበር ሁሉ፣ ባላባታዊውን ሥርዓት ቦርቡሯታል፡፡በተለይም እዚህ የምናተኩርበት ነጥብ፣ ብዙ መቶ ሺ የሚቆጠሩ የገበሬ ቤተሰቦችን በመበታተኑ ላይ ነው፡፡በነጂማ–አጋሮ ዞሪያ በቡና ለቀማ ላይ የሚገኙት ወዛደሮች ብዙውን ጊዜ ከወሎ ድረስ ለዚህ ሥራ ብዙ ሰዎች ተጉዘው የሚመጡ ናቸው፡፡በነወንጂ፣ ተንዳሆ፣ ሰቲት ሁመራ፣ በነአደላ ማእድን፣ ባዲስ አበባ ዞሪያ፣ በድሬዳዋ፣ ወዘተ.በየፋብሪካው ውስጥ የሚሠሩት ወዛደሮች ከገጠርና ብዙውን ጊዜ ደግሞ ከትውልድ ክፍለአገራቸው ተነቅለው የተሰደዱ ናቸው፡፡ሰነቶ ወዛደር በሚያውቀውና በለመደው አገር በወባና በሌሎች በሽታዎች አልቋል፡፡በሥራ ፍለጋ የተሰደደ ወዛደር በሰሚቀር፣ የዛሬ ሀያ ዓመት ገደማ የወለጋ ልጃገረዶች

አጋሮ ነጩኪን፣ ሂንቲታ
አረበ የቲ፣ ነ ፊታ ።።

(አጋሮ አትውረድ ትቃታለህ፣ መጋዝ አረስ ታገበኛለህ) እያሉ ይዘፍኑ ነበር! የገንዘብ ኢኮኖሚ የገጠሩን ሕብረተሰብ ምን ያህል አምታቶት እንደነበር ያሳያል፡፡

የከበርቴ ኢኮኖሚ በገራችን አዲስ ስለሆነ የወዛደር መደብም በገሪቷ አዲስ ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ ይህኛው የኢኮኖሚ ክፍል ከሁሉ ዘመናዊና ከሁሉ የተራመደ፣ ለማደግና ለመስፋፋት የተፈጠረ ክፍል እንደመሆኑ መጠን ወዛደሩም በሕብረተሰቡ ውስጥ ትልቅ የሆነውን ቦታ ይዟል ማለት ነው፡፡ደግሞም የኢትዮጵያ ወዛደር የከበርቴዎችን — በተለይም የበእድ ዘራፊዎችን — ጭቆናና ዘረፋ በቀርቡ የቀመሰ ስለሆነ፣ ጠቅላላውን ያገሪቷን ሕብረተሰብ እንዳም ለመለወጥ በሚደረገው ትግል ትልቅ ሀላፊነት የሚወድቀው በርሱ ትከሻ ላይ ነው፡፡

ወዛደሩ እስከዛሬ ድረስ ጠቃሚ እንደሆኑ የፃከቲት እንቅስቃሴ አሳይቷል፡፡በዚህ እንቅስቃሴ አማፅነት፣ እንዳንድ ከበርቴዎች ፍጹም ሃፍረትን የማያውቅ ዘረፋን በወዛደሩ ላይ በገሃድ እንደሚፈጽሙ ታውቋል፡፡ከብዙዎች ምሳሌዎች ጥቂቶችን ለመጥቀስ ያህል ብቻ፣



የስሎን ማህተመሥሳቢ አስመጪና ሳኪ ኩባንያ ከቀጠራቸው 1650 ወዛደሮች ውስጥ 1500 ሴቶች ሲሆኑ፣ ለነዚህ የሚከፈለው ሰማንያ ሳንቲም ብቻ ነው፡፡ለቀሩት 150 ወንዶች ገን በቀን ወደአንድ ብር ገደማ ይከፈላቸዋል፡፡የወንዱ ደሞዝ እራሱ የፍጹም ዘረኛ ደሞዝ መሆኑ ሲታወቅ፣ የሴቱ ደግሞ የዘረፋ—ዘረፋ መሆኑ ገልጽ ነው፡፡በዚህ ላይ ደግሞ ወዛደሮች ሁሉ በቀን 13 ሰዓት ይሠራሉ፡፡ ... የእቴጌ መነን የጅ ጥበብ ትምህርት ቤት ወዛደሮች ከመዘረፋቸውም በላይ፣ ለሥራ አርፍደው ከደረሱ በገርፋትና በቅላ ጭምር እንደሚቀጡ ታውቋል፡፡ ... በአደላ የወርቅ ማእድን ውስጥ የሚሠሩት ፣ ጥንት ከየመንገዱ በግድ ታፍነው እዚያ የተወሰዱት ወዛደሮች፣ የሚኖሩበት ሁኔታ ከባሪያ ሁኔታ ምንም የማይሻል መሆኑን የመንግሥት ጋዜጦች ጭምር ለመመስከር ችለዋል፡፡ ... ይህ ሁሉ ሁኔታ ባለፈው ክፍለዘመን መጀመሪያ ላይ በውሮፓ ፋብሪካዎች ውስጥ የነበረውን አሰቃቂ የወዛደሮች ኑሮ የሚያስታውስ በዛሬው ዓለም የትም ቦታ ይገኛል ተብሎ የማይታሰብ ሁኔታ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ወዛደር በማህበር ውስጥ ተመዘገበ አልተመዘገበ፣ ምንም የሥራና የሕይወት ዋስትና የለውም፡፡ይህ የታወቀ ሆኖ ሳለ፣ ይህንን እንኳን የመጀመሪያ ደረጃ መብትን እንዳይጠቀምበት፣ ማህበር እንዳያቋቁም ከበርቴዎችና መንግሥቱ ተሻርከው ይከለክሉት ነበር በነዓንዱ ቦታዎችም የቆሙትን ማህበራት አስከማፍረስ ይደርሱ ነበር፡፡በየካቲት ኢሠአማ ላቀረባቸው ድርድሮች በጻፈው መግቢያ ውስጥ ከዚህ ቀጥሎ የምንጠቅሰው ነበር፡—

> 'በሕግ ከተመዘገቡትም የሠራተኛ ማህበሮች ውስጥ የፈጣን መሰላሽ ድርጅት፣ የሳዘሪዲስ ጥጥ ኩባንያ፣ የኑራ ሄራና የአዋሬ መልካ የርሻ ድርጅት፣ የሸቀ ጥጥ ኩባንያ፣ የፃፕው መኮንን የሕዝብ መሰላሽ፣ የገ.ነ ዞሚሊቶ ሆስፒታል፣ የወሩ አርሻ ሥራ፣ የወደብና ትራንዚት፣ የአስመራ ማተሚያ ቤቶችና እነዚህን የመሰሉት ብዙ የሠራተኛ ማህበሮች በአሠሪዎች ሕገወጥ ድርጊትና በአንዳንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ቸልተኝነት ምክንያት ወድመው፣ በርከት ያሉ ሠራተኞች የማህበር መሪዎችም ከሥራቸው ተፈናቅለው በከንቱ የቀሩ መሆናቸውን በማስታወስ...'

በጥሩ፣ የኢሠአማ ድርድሮችና በተለይም ለድርድሮቹ መግቢያ የሆኑት ነጥቦች እንደሚያሳዩት ሁሉ፣ የኢትዮጵያ ወዛደር ያለርህራሄ የሚበዘበዝና የሚጠቃ መሆኑ ገልጽ ነው፡፡የየካቲት እንቅስቃሴ ደግሞ ይህንን እውነት በይበልጥ አረጋግጧል፡፡በተጨማሪም፣ ለመቀጠር አዲስ ያጋጠመው በዚህ ኢሰብአዊ ሁኔታ ቢኖር፣ በሚሊዮን ሲቀጠር የሚችለው ደግሞ ትላልቅን ከተማ — አዲስአበባን፣ አስመራን፣ ድሬዳዋን፣ ሐረርን፣ ጂማን፣ወዘተ.— በሥራአጥነት ሲያጨበብ ይታያል፡፡

በንደዚህ ዓይነት ሥራ በሌለበትና የወዛደር ጉልበት እለመጠን ርካሽ በሆነበት ሕብረተሰብ ውስጥ ወዛደሩ ከቀጣሪዎች ጋር አይፋጠጥም፣ እንዲያውም ተለማምጦ እጅ እየነሳ ይኖራል እንጂ ተብሎ፣ የከበርቴ ሊቃውንት እንደሚያስተምሩት ሁሉ፣ ሊገመት ይችላል፡፡ነገርገን የኢትዮጵያ ወዛደር ገና ለጋ በሆነው እድሜው ውስጥ ያሳየው የታጋይነትና የቆራጥነት መንፈስ አስደናቂና ስንቱን የቡርዧ ቲዎሪ ያከሸፈ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያው የወዛደር ማህበር የተቋቋመው የዛሬ 26 ወይም 27 ዓመት ሲሆን፣ እርሱም የምድር ባቡር ሠራተኞች ማህበር ነው። የዚህ ኩባንያ ወዛደሮች ከጥንትም ጀምሮ ለቆራጥነታቸውና ለታጋይነታቸው የታወቁ ናቸው። እአአ በ1947 በ1949 እና በ1953 ያደረጋቸውን ትግሎች የኢትዮጵያ መንግሥት 'ሕገወጥ' ብሎ አውግዞ ነበር። ገና መንግሥቱ ስለሠራተኛ ማህበር ሕግ ከማውጣቱ በፊት። በ1947ቱ ትግላቸው የምድር ባቡር ወዛደሮች 'ኑሮ ተወደደ፣ ደሞዛችን አነሰን፣ ልንተዳደርበት አልቻልንም' ብለው ጥያቄ ስለጠየቁ፣ ቀጣሪያቸው

'ሐበሻ ምግቡ ማሽላ

ልብሱ ደንዩ፣ መኝታው ሌጦ

እናንተ የምን ደሞዝ ጭማሪ ያስፈልጋችኋል ?' ብሎ ሰደባቸው ይባላል፡ በዚህን ጊዜ ወዛደሮች ተሰብስበው ደብድበው ልክ ካገቡት በኋላ ለሶስት ወራት ሥራ አቁመው እየተበለ ለምድር ባቡሮች ይወረሳቸዋል።

የኤርትራ ወዛደሮች ማህበር፣ የነአታቲ፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ የነወገኗ፣ የነቻቶል ኮትበ፣ ከመንግሥት መሥሪያ ቤቶችም እንደነአውሬ ጉዳና በለሥልጣን ያሉት ወዛደሮችና ሌሎችም ሠራተኞች፣ ለመታገል የመንግሥትን ሕግ ማውጣት ያልጠበቁ ከመሆናቸውም በላይ፣ በነዚህ ባለፉት አሥር—አሥራአምስት ዓመታት ባደረጋቸው ትግሎች ብዙ ታታሪነትን አሳይተዋል።

የኢትዮጵያ ሠራተኞች አንድነት ማህበር የተቋቋመው ሚያዝያ 1 ቀን 1955 ሲሆን በመሠረት 29 ልዩ ልዩ ማህበሮች ነበሩበት። ይህ ማህበር እንደተቋቋመ ለደሞዝ፣ ለመጠነኛ የሥራ ሰዓት፣ ለተሻሻለ የሥራ ሁኔታ፣ ወዘተ. አቤቱታ ቢያቀርብ ይህ ነው የማይባል ወንጀል በመንግሥትና በአሠሪዎች በመሪዎች ላይ ተፈጸመ። ብዙዎችን ከሥራ አሰወጧቸው። ያን ጊዜ የነበረውን የማህበሩን ፕሬዚዳንት አቶ አብርሃም ገመን ከሥራ አስወጥተው ካጉላሉት በኋላ ሕይወቱ እንዲጠፋ አደረጉ። በሌላ በኩል ግን አንዳንዶችን የማህበር መሪዎች በገንዘብ በመግዛት፣ የወዛደሩ የመብት ትግል እንዲወናገፍ አድርገዋል። ነገርግን ይህ ሁሉ ተንኮል የኢትዮጵያን ወዛደር ታጋይነት አልቀነሰውም፣ እንዲያውም በትግሉ እንዲበረታበት አድርጓል።(ስለወዛደሩ ሁኔታና ትግሎች ትግላችን ቁ. 8፣ሀምሌ 1960 ተመልከት)

የየካቲትን እንቅስቃሴ በሚመለከተው በኩል፣ የወዛደሩን መደብ ከፍተኛ ድርጊቶች በሁለት ክፍሎ ማየት ይቻላል። መጀመሪያ፣ ወዛደሩና ሌላውም በኢትዮጵያ ሠራተኞች አንድነት ማህበር ውስጥ የተደራጀው ሠራተኛ ሁሉ በድርጅቱ አማካይነት የወሰደው እርምጃ ለብቻ መታየት አለበት። ከዚያም፣ ወዛደሩ በራሱ የወሰዳቸው ታሪካዊ ነጻ ድርጊቶችም እንደዚሁ ለብቻ መታየት ያስፈልጋቸዋል ብለን እናምናለን። የኢትዮጵያን ወዛደር ታሪካዊ የ[illegible]ነትና የትግል ችሎታ በበለጠ ሊያስገምቱን የሚችሉት እነዚህኞች ድርጊቶች ናቸው በማለት ነው ይህን አከፋፈል የመረጥነው።



በመጋቢት መጨረሻ የወጣው፣ የዚህ ዓመቱ 'የሠራተኛ ድምፅ' የመጀመሪያ ቁጥር በርእሰአንቀጹ ስለየካቲቱ የጠቅላላ ሥራ ማቆም እርምጃ በደህና መከናወን ሙገሳ ካደረገ በኋላ፣ የሚከተሉትን፣ በሰፊው የምንጠቅሳቸውን እምነቶች ያሠፍራል፡—

'... የሠራተኛው ንቅናቄም የሰፋፊ አዋሪው የኢትዮጵያ ሕዝብ ድምፅ መሆኑ ተረጋገጦለታል። ከዚህ በፊት እንደተደረገው ሁሉ ወደፊትም በሀገሪቱ ውስጥ ሊደረግ የሚገባውን የፖለቲካ፣ የሲቪል እና የኢኮኖሚ እድገም በሰላማዊ መንገድ ለማስገኘት እንደማንኛውም ሕብረተሰብ ኃላፊነት እንዳለብን እናምናለን።'

ከዚያም እንደሚከተለው ርእሰአንቀጹ ይደመድማል፡—

'የሠራተኛው ንቅናቄ በአለው የተለየ እድገና ታሪኩም እንደሚመሰከረው ለአንድ ሕብረተሰብ ለውጥ ለማስገኘት ግንባር ቀደም ነው። በዚሁ አንጻር የኢትዮጵያ ሠራተኞች ንቅናቄም በአለፉት ጊዜያት በተገኙት ስምምነቶች ብቻ ተወስኖ መቅረት የለበትም። ለሃያኛው ክፍለዘመን ኢትዮጵያ የሚያስፈልጋትን ለውጦች ለማምጣት መታገል አለበት። ሆኖም ያለንን ጥሩ ልምድና ባህል በሙሉ ፈንቅሎ መጣል አለበት ማለታችን አይደለም። ከአዲሲቷ ኢትዮጵያ እድገም ጋር ሊስማሙ የሚችሉና አንድነታችንን አጠንክሮ የአገራችንን ታሪክ የሚጠብቅ ልምድና ባህል ሊጠበቅ ይገባዋል።'

ይህንን የሠራተኛ ድምፅን በሰፊው የጠቀስነበትን ምክንያት አንባቢው ቢያየው እንደማይቀር እናምናለን። በተጠቀሱት መስመሮች ላይ በሰፊው ብንተች ደስ ባለን ነበር። ነገርግን በጭሩ ብቻ አንዳንድ ነገሮችን እናንሳ፡— እርግጥ የወዛደሩ ንቅናቄ በግንባር ቀደምትነት ለውጥን በሕብረተሰብ ውስጥ ያመጣል። እርግጥ የወዛደር መደብ የተጠቁት መደቦች ሁሉ ተቆርቋሪና አፈጋባዥ ይሆናል። ነገርግን፣ በሕብረተሰብ ውስጥ 'በሰላማዊ መንገድ' ለውጥን እንዲያመጣ ገዥ መደቦች ይፈቅዱለታል ወይ ? በፍጹም። ታሪክ እንደሚያስየን፣ ገዥ መደቦች ሥልጣንን በሰላም ለሠርቶአደሩ ሕዝብ ለቀቀው አያውቁም፣ ለውጥ ደግሞ ደረቢው እንደሚለው 'መሠረታዊ' እንዲሆን ከተፈለገ ሥልጣን መያዝ አለበት። በዚህ ሁሉ ምክንያት በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ወዛደር ይህንን እውነት እንዲረዳው ማድረግ ያስፈልጋል።

ሁለተኛው ነገር ደግሞ የወዛደሩ እንቅስቃሴ የሠርቶአደሩ ሕዝብ 'ድምፅ' መሆን ጉዳይ ነው። እንደውነቱ ከሆነ ይህም ገና ነው። ራቅ ብለን እንደምናየው ሁሉ፣ ኢሠአማ እራሱ ያቀረባቸው 16 ጥያቄዎች ሙሉ በሙሉ ይህንን አያንጸባርቁም። የወዛደሩ መደብ የራሱ የፖለቲካ ፓርቲ ከሌለው የመንግሥትን ሥልጣን ነገር ሊያነሳ እንደማይችል ግልጽ ነው፣ የሥልጣንን ጉዳይ ካላነሳ ደግሞ ለሠርቶአደሩ ሁሉንም ለጠቅላላ ሕብረተሰቡ፣ በአፈጋባዥነት እንዴት ሊቆም ይችላል?

ሌላው ቁርቁ፣ ያሁኑን የጠቅላላ ሥራ ማቆም እርምጃ የወሰደው ወዛደሩ እራሱ ወስኖ አይደለም። ይህንን የወሰኑለት የኢሠአማ ሀላፊዎች ናቸው። እነዚህ ደግሞ ማንም እንደሚያውቀውና ከዚህ በላይ ያቀረብነው ጥቅስ እራሱ እንደሚመሰክረው፣ በመደብ ሁኔታቸውም ሆነ በርእዮተ ዓለማቸው ወዛደር አይደሉም። ይህም ማለት፣ የኢትዮጵያ ወዛደር ገና የራሱን ፓርቲ ማቆም አለበት፣ ገና የዓለምን ወዛደር እንቅስቃሴ ታሪክና ጊዜያዊ ሁኔታ ማወቅና የኢትዮጵያን ረቮሉሺን ለመምራት መታገል አለበት ማለት ነው። በቅርብ ጊዜ ቢታይ ደግሞ ኢሠአማ እራሱ ገና ከአድሃሪዎች ያሜሪካን ማህበሮች የበላይነት መላቀቅ አለበት።

የየካቲትን የኢሠአማ ድርጊቶች በሚመለከተው በኩል፣ የኢሠአማ ፕሬዚዳንት በየነ በሎምን 'አፍሪካ' ለሚባለው መጽሔት በሰጠው ኢንተርቪው መሠረት፣ የተደረገው ጠቅላላ የሥራ ማቆም ከረጅም ጊዜ ጀምሮ ሲታሰብበት የቆየ ነው::ለምሳሌ. በ1963 እና ከዚያም ወዲህ የዛሬ አራት ዓመት በ1962፣ የጠቅላላ ሥራ ማቆም አድማ ሊወሰድ ተቃርቦ፣ በመጀመሪያው ጊዜ አሠሪዎች ዝም ብለው ብዙ ወዛደርን ከሥራ ሲያስወጡ፣ በሁለተኛው ደግሞ፣ መንግሥት ለብዙዎቹ ጥያቄዎች ቃል ስለገባ፣ አድማው ሳይወሰድ ቀርቷል::በተጨማሪም፣ ከዚህ በላይ የተጠቀሰው የማህበሩ መጽሔት፣ ውሳኔው የተወሰደበትን ሁኔታ ሲያብራራ እንደሚከተለው ይጽፋል:-

'ምክር ቤቱ (ማለት የኢሠአማ ምክር ቤት ) ይህንን ውሳኔ ያሳለፈው እንደሚወራው አጋጣሚ ጊዜ ጠብቆ ሳይሆን፣ ቀደም ሲሉ በነሀሴ ወር 1965 ዓ.ም. እና በጥር ወር 1966 ዓ.ም. ተሰብስቦ በነበረበት ወቅት፣ በኢትዮጵያ ሠራተኞች ላይ የደረሰው ከባድ ችግር ጊዜ የማይሰጥ መሆኑን በመገንዘብ፣ ጠቅላላ የሥራ ማቆም ለማድረግ በዘጋጀው አቋሙ መሠረት ነው::'

ወጪም ወረደም፣ በዚህ እንቅስቃሴ ውስጥ፣ የኢሠአማ መሪዎች ብዙ ቢያመነቱ እንደ ነበረ ግልጽ ይመስለናል::(በነገራችን ላይ፣ 'ጊዜን ጠብቆ' የዚህ ዓይነቱን አድማ መውሰድ ምን ነውር አለበት ?) ከዚህ በላይ በሌላ ቦታ እንደተጠቀሰው፣ የኢሠአማ አመራር የማያመነታ ቢሆን ኖሮ፣ የካቲት 11 ቀን፣ አስተማሪዎች፣ ታክሲ ነጂዎችና ተማሪዎች ሥራና ትምህርት አቁመው ከፖሊስ ጋር ሀይለኛ ግጭት በደረጉበት ወቅትና ብዙ ሰው በቆተበት ተን ጥሪውን ያደርግ ነበር::ማመንታት መቼስ የትንሽ ከበርቴው ዓይነተኛ ጠባይ ነው፣ ደግሞም አስተባባሪም ሆነ ድርጊት ከመደብ ክልል ውጭ ሊታይ አይችሉም::

16 ድርድሮችንና የጠቅላላ ሥራ ማቆምን ጥሪ ያቀረቡት የኢሠአማ መሪዎች ናቸው: ይህንን ያደረጉት ከታች ወደላይ ወዛደሩ ስላገፋፋቸው ይሁን፣ ወይንም የማህበሩ ፕሬዚዳንትና መጽሔት እንደሚሉት ከረጅም ጊዜ ጀምሮ የታሰበበት ይሁን፣ ከዚህ ሆኖ ለመመለስ አስቸጋሪ ነው::የሆነ ሆኖ፣ ወዛደሩ የተደረገለትን ጥሪ በታላቅ ዲሲፕሊን ተቀብሎ በታላቅ ዲሲፕሊን ፈጽሞታል::ሌላው ቀርቶ ማህበሩ 'ሰላማዊ ሰልፍ አታድርጉ፣ መንገድ ላይ አትውጡ' ብሎ ቢያዝዎም፣ በዚያ በነገርገር ሁኔታ፣ የጥንቱን ያገር ልምድ በመከተል ትእዛዙን በሙሉ ልቡ የተቀበለውና ያከበረው ይመስላል::ይህ የዲሲፕሊን ጥበቃ የወዛደሩን ለመደራጀትና በተደራጀ አኳኋን ለመታገልም ዝግጁ መሆን ያሳያል::በተረፈም፣ የወዛደርን መደብ ዓይነተኛ ከሚያደርጉት ባሕርዮች አንዱ የዲሲፕሊን አጠባበቅ ነው::በገራችን ሌኒን ነገ፣ ይህ ገና ለጋ መደብ ከገበሬነት ወደዚህ የተሸጋገረው በቅርቡ በመሆኑና በተጨማሪም የነክዒ ሰአበበ የቀዶ-ወዛደር (ሎምፐን ወዛደር) በከሉት እንደሆነ ፣ ማለት የቁራቆን መገፈስ አጋበቀበት እንደሆነ በማለት ነው እዚህ ላይ የዲሲፕሊን ጥበቃውን የምናቀንሰው::



ከዚህ ሁሉ ይበልጥ ግን የኢትዮጵያን ወዛደር ሊያስመሰግነው የሚገባው በገዛ እራሱ ተደራጅቶ በየቦታው የወሰደው ነጻ አድማ ሁሉ ነው::ይህንን ስላልን የኢሠአማ መሪዎችና ሌሎችም 'አናርኪስቶች' — ፀረ ድርጅት ሰዎች — እንደሚሉን ተስፋ አለን:: ይህንን ያልገበት ምክንያት እንደውነቱ ከሆነ ቀላል ነው::እንደሚነገረው ከሆነ በብዙ የሥራ ቦታዎች የወዛደር ማህበሮች የሚመሩት ወዛደሩ እራሱ ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ በመረጣቸው ሰዎች ሳይሆን በቀጣሪዎች በተመረጡ ሰዎች ነው::ለምሳሌ፣ የዛሬ ሰባት ዓመት በትግላችን በወጣ አንድ ዜና መሠረት፣ ያታዩ የጨርቅ ፋብሪካ ወዛደሮች አዲስ የማህበር ምርጫ እንዲደረግ ቢታገሉ ስድስት ዓመታት አልፈው ነበር:: ( ትግላችን ቁ. 2፣ ህዳር—ጥር 1963::)በዚህ ሁኔታ፣ ከዚህ በላይ እንደተባለው ሁሉ፣ የወዛደሩን ቆራጥነት፣ ለትግል ዝግጁነትና የመደብ ንቃት በይበልጥ ሊያሳይ የሚችለው ወዛደሩ እራሱ የፈጸማቸው ነጻ ድርጊቶች ናቸው::

በዚህ በኩል፣ የኢትዮጵያ ወዛደር የፈጸማቸው ድርጊቶች በጣም ብዙ ከመሆናቸው የተነሣ እዚህ ላይ በዝርዝር ልናቀርባቸው አንችልም::ኢሠአማ የነዚህን ድርጊቶች መዝገብ እንደሚይዝ ተስፋ እናደርግ::በጠቅላላው ግን፣ ማህበርን የማቆም መብት፣ የደሞዝን ጭማሪ የሥራ ሁኔታን መሻሻል፣ የጨቋኝ አስተዳዳሪዎችንና ባለሥልጣኖችን መወገድ፣ ወዘተ. በመጠየቅ ወዛደሩ በብዙ ቦታዎች በገዛ እራሱ ታግሎአል::በአንዳንድ ቦታዎች በጉልበት ጭምር — ለምሳሌ በውሬንጓና ባለሥልጣን — መሥሪያ ቤቱን ወይንም የሥራ ቦታውን በመያዝ ሥርዓቱን ወጥሮ ይዞት ነበር::

እዚህ ውጭ አገር በደረሰን ዜና መሠረት፣ ሚያዝያ 5 ቀን የምድር ባቡርና የአውቶቡስ ሠራተኞች፣ የፊናንስ፣ የኢትዮ—ስዊድሽ የቤት ሥራ፣ የኢትዮጵያ የሱቆች ኮርፖሬሽን የአውጉስታ የሸሚዝ ፋብሪካና ሌሎችም ወዛደሮች ሰላማዊ ሰልፍ አድርገው ነበር::የዩኒቨርሲቲና የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችም አብረዋቸው ተሰልፈዋል::ሰልፈኞች ከያዙአቸው ሰሌዳዎች ውስጥ 'ጥቂቶች ያገሪቷን ሀብት መበዝበዛቸውን ያቁሙ' ፣ 'የታሠሩት መሪዎቻችን ይፈቱ' የሚሉ ነበሩ::በተጨማሪም፣ ሰልፈኞች በራሪ ወረቀቶችን በብዛት እንደበተኑ ታውቋል::ይህንን ሰልፍ ማን እንደጠራ — ኢሠአማ ይሁን ወዛደሮች እራሳቸው — ለማወቅ አልቻልንም:: የሆነ ሆኖ፣ የዚህ ዓይነቱ የትግል ዘዴ ከእንግዲህ የወዛደሩ መሣሪያ ሆኖ ለመለመዱ ይህ ድርጊት ይመሰክራል::የዓለምአቀፍ ወዛደርን እንቅስቃሴ ታሪክና የትግል ልምድ ከራሱ ትግል ጋር በማቀሃድ፣ የኢትዮጵያ ወዛደርም በራሱ ፓርቲ ተመርቶ፣ ምሽጎችን በየከተማው ገንብቶ የሚዋጋበትና 'ሰማያትን የሚያናውጥበት' ቀን የተቃረበ መሆኑን የሚያበስር ድርጊት በመሆኑ ያበረታታል::

የኢትዮጵያ ወዛደር፣ በማህበረቱ በኩልም ሆነ በራሱ በወሰዳቸው የየካቲት ሪቮሉሺናዊ እርምጃዎች ተመናከሮ ወጥቷል::መጀመሪያ የመደራጀትን ነገር ብቻ እንኳን ብንመለከት በውጭ አገር ጋዜጦች እንደተወራው ከሆነ፣ የኢሠአማ አባላት ከየካቲት እንቅስቃሴ በኋላ

ከአቶፍ በላይ ሆነዋል::አሁን ማህበሩ 180 ሺ አባሎች አሉት ይባላል::ከጥር አድገት ይበልጥም ገና ወዛደሩን የሚጠቅመው ያገኘው ትምህርት ነው:- ይኸውም አንድነትን አጠንክሮ ከታገለ፣ በአቤቱታ በብዙ ዓመታት የማያገኘውን በትግል በጥቂት ቀናት እንደሚያገኝ ነው::ይህ መሠረታዊ ነገር ለመላው የኢትዮጵያ ሠርቶአደር ሕዝብ ገልጽ ሳይሆንለት አልቀረም::ነጻነት፣ እኩልነት፣ ፍትህ ከተፈለጉ በተጋድሎ እንጂ በአቤቱታ አይገኙም::

አንዳንድ ሰዎች የወዛደሩ መደብ የየካቲት አንቀሳቃሴ መሪ ነበር በማለት ጽፈዋል::ለምሳሌ፣ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ፌደረሽን መጽሔት የገነበት ጥር ባንድ በተምታታ ርእስ አንቀጽ ውስጥ የሚከተለውን አስፍሯል:-

'የየካቲት ረቮሉሽን በመነሳት ላይ ያለው ላብ አደሩ ሠራተኛ ከራሱ የመደብ ጥቅም አልፎ የመቀሳሰው ሕብረተሰቡን በተለይም ደግሞ የተፈጥሮ የመደብ ጓዱ የሆነውን የደሀውን ገበሬ ዋና ጥያቄ ይዞ የተነሣበትና የታገለበት ነው::የየካቲቱ ረቮሉሽን በጀግናውና ከፍተኛ ዲሞክራቲክ በሆነው የኢትዮጵያ ላብ አደር ሠራተኛ የተጀመረ፣ ገንባር ቀደም መሪነትም በዚህ መደብ የተወሰደ ታላቅ ትግል ነው::'

ይህ መቼስ ፍጹም ከተጨባጩ ሁኔታ የራቀ፣ ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ፣ ያለውን ተጨባጭ የወዛደር መደብና ተጨባጭ ድርጊቶችን፣ በርግጥ የሆነውን ነገር በማጥናት ፈንታ የግልን ምኞት እና የግልን ቅዠት በቦታው መተካት ነው::ይህንን ፍረክርስኪ በመተቸት ጊዜያችንን አናጠፋም::የኢትዮጵያ ወዛደር የየካቲት አንቀሳቃሴ ጀማሪም መሪም አልነበረም::የዚህ አንቀሳቃሴ ጀማሪና መሪ የትንሽ ከበርቴው መደብ መሆኑን ከዚህ በላይ አይተናል::ነገርግን ይህ የወዛደር መደብ መሪ አልነበረም ማለት መሪ መሆን የለበትም ማለት እንዳይደለ ገልጽ ነው

እንዲያውም መጪውን ብሔራዊና ዲሞክራሲያዊ ረቮሉሽን የሚመራው ይህ መደብ እንደሚሆን ተደጋግሞ ተነግሯል::በሕብረተሰቡ ውስጥ ከሁሉ ተራማጅ፣ ከሁሉ ቆራጥና ዘላቂ በመሆኑ የወዛደር መደብ መሪነትን መውሰድ እንዳለበትና መውሰዱም እንደማይቀር የረቮሉሽን ሳይንስ ያስተምረናል::ነገር ግን ከዚህ ደረጃ ከመድረሱ በፊት ወዛደሩ የራሱ ፓርቲ እንዲኖረው ያስፈልገዋል::'የወዛደሩን መደብ ወደአንድነት ነጻ የፖለቲካ ሀይል' የሚለውጥ ፓርቲ መኖር አለበት::ይህ እስከልሆነ ድረስ ወዛደሩ ታሪክ የጣለበትን፣ አዲስ ሕብረተሰብን የመመሥረትን ትግል ሊመራው እንደማይችል ገልጽ ነው::

ሁለተኛ ነገር ደግሞ፣ መሪ ለመሆን ከተፈለገ ተመሪ መኖር አለበት::በኢትዮጵያ ሁኔታ ዋናው ተመሪ መደብ የጪሰኛውና የደሀ ገበሬው ነው::ይህም ማለት እንግዲህ ወዛደሩ እራሱ ነጻ ፓርቲውን ከቆመ በኋላ ገበሬውን መርቶ የገጠር ረቮሉሽኑን ማካሄድ አለበት ማለት ነው::ይህንን ካደረገ ብቻ ነው የወዛደር መደብ የተጨቆኑትን መደቦች ሁሉ መርቶ በጌቶችነትና በኢምፔሪያሊዝም ላይ ድልን ለማስገኘት የሚችለው::ይህንን ካደረገ ብቻ ነው አዲስ ዲሞክራሲያዊ ሕብረተሰብን ሊገነባና ከዚያም ወደሶሻሊዝም ሊጓዝ የሚችለው::ወዛደሩን በሚመለከተው በኩል የየካቲት አንቀሳቃሴ ያሳየው አንድ ዋና ነገር የወዛደሩ ፓርቲን አስፈላጊነት ነው::



### (ሠ) ልዩ ልዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች

ከዚህ በላይ ዋና ዋናዎች የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ መደቦች አሰላለፍ እንዴት እንደነበረ ተመልክተናል::ይህንን ያሰላለፍ ጉዳይ ከመዝጋታችን በፊት በጭሩ ስለልዩ ልዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች እናገባ:-

የየካቲትን አንቀሳቃሴ ዓይነተኛ የሚያደርገው ዋናው ነገር መቼስ የመላ ሕብረተሰቡ መደቦችና ክፍሎች በትግሉ ውስጥ መግባት መሆኑን ከዚህ በላይ ባንድ ቦታ ገልጸናል::በዚህ አንቀሳቃሴ ውስጥ ብሄረሰቦች፣ ሃይማኖቶችና ሴቶች ገብተውበት በሚገባ ተሳትፈዋል: ብሄረሰቦችን በሚመለከተው በኩል፣ ከዚህ በላይ የጠቀስናቸው የአፋሩና የገሙ ጎፋ አንቀሳቃሴዎች፣ ምናልባትም በአዲ ኡግሪ የተደረገው የ10ሺ ሰዎች ሰላማዊ ሰልፍ፣ በማያጠራጥር አኳኋን የሚያሳዩና የአፋር አንቀሳቃሴና ጥያቄዎች በቀጥታም ሆነ በዘወርዋራ መንገድ የብሄርን ጥያቄ የሚያወሱ ነበሩ:: በነገራችን ላይ፣ የእንዳልካቸው መንግሥት ባብሄረሰቦች በኩል ያለውን ትግል ለማቀዛቀዝ በየቦታው የያገሩን ሰው ለመሾም ቆርጦ ነበር::ለምሳሌ የአባ ቢያ አባ ጆቢር በጂማ በምክትል አገረገዢነት መሾም የዚህ ዓይነት እርምጃ ነበር:

የብሄረሰቦች ትግል ገንባር ቀደም የሆነው የኤርትራ ትግል አሥራስምንት ዓመታት ሙሉ ሥርዓቱን ወጥሮ በመያዝ ካከሰረው ሀይሎች አንዱ እንደሆነ ይታወቃል::በየካቲት አንቀሳቃሴ መጀመሪያ ላይ፣ የኤርትራ ገንባር አንድ ክንፍ 'በዚህ ሁኔታ ጥያቄያችንን እናፋፍመዋለን' ብሎ ነበር::ደግሞም በዚህ ፖሊሲ መሠረት፣ ፖሊሲውን ባወጣው ክንፍ ይሁንበሉሳው፣ አንዳንድ እርምጃዎች ተወስደዋል::የደበርዋ ማእድን መዝጋት፣ ያንዳንድ ፈረንጆች ተይዞ ወደገጠር መወሰዱና አሁን በቅርቡም በሀምሌ 6 ቀን ሃሚድ ፈረጅ ሃሚድ መገደል:: ይህንን የሚያረጋ የሚያስመስል ግን በውጭ አገር ጋዜጦች የተነገረው 'ነገሩ ወዴት እንደሚጓዝ ለማየት እንፈልጋለን' የሚለው አቋም በገቢ ክንፍ ተወስዷል::...ለማንኛውም፣ እና እስከምናውቀው ድረስ፣ አዲሱ የወታደሮች ኮሚቴ ያደረገውን፣ ስደተኞች ወደአገር ተመለሱ ይቅርታ ተደርጓል ወዘተ. የሚለውን ጥሪ ገንባሩ እንዴት እንደሚያየው አላስታወቀም: እንደውነቱ ከሆነ፣ የኤርትራ ገንባር ክንፎች ስለጊዜያዊው የኢትዮጵያ ሁኔታ የወሰዱት የተጣራ አቋም የለም::...

በዚህ በየካቲት አንቀሳቃሴ ውስጥ ወደ አሥር የሚጠጉ የኦሮሞ ብሄረሰብ ምሁራን ተይዘው ታሥረው ነበር::መንግሥት ለምን እንደያዛቸውና በኋላም በምን ሁኔታ እንደለቀቃቸው ገልጽ አይደለም::

የኢትዮጵያ አድሃሪ ሥርዓት በትግሬይ ብሄረሰብ ላይ የሌሉትን ጥላቻ ለመቀስቀስ መሞከር ከጀመረ ቆይቷል::በየካቲት አንቀሳቃሴም በጋዜጦች አማካይነት ለመከፋፈል ሲሞከር ታክሲ ነጂዎች ሥራ ያቆሙት በትግሬዎች ተገፋፍተው ነው ለማለት ሞክሯል::በኤርትራው ትግልና በትግሬይ ወዛደሮች ንቃት ምክንያት ሥርዓቱ በነርሱ ላይ ጥላቻን ለማምጣት ሲሞከር

ይህ የመጀመሪያ ጊዜው አይደለም::የኢትዮጵያ ሠርቶአደር ሕዝብ በዚህ ተንኮል ሳይ በመገታት፣ ሌሎችን ተንኮሎች እንዳከሸፈ ሁሉ፣ ይህኛውንም ማክሸፍ አለበት::በተረፈም፣ በየካቲት እንቅስቃሴ የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች በሥርዐቱ ላይ እንጂ አንደኛው በሌላው ላይ ፈጽሞ አልተነሣም::እንዲያውም ሁሉም በምሳጉደል እጅ ለእጅ ተያይዞ ነበር የተነሣው ለማለት ይቻላል::ይህም በአንድ በኩል የገዥ መደቦችንና የባእድ አድሃሪዎችን፣ 'እርስ በርሱ ይፋጃል' የሚለውን ሀሰተኛ የቆየ ፕሮፓጋንዳ ሲያከሽፈው፣ በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያን ሕዝቦች የመደብ ነፃነት መዳበር ያሳያል::እያንዳንዱ የኢትዮጵያ ብሔረሰብ፣ ትልቅም ሆነ ትንሽ፣ የወደፊት እድሉን ለመወሰን መብት አለው::ይህ መብት በትክክል ከሥራ ላይ እንዲውል ከተፈለገ ብሔረሰቦች ተያይዘው ኢምፔሪያሊዝምንና ኋላቀር ሥርዓትን ከአገሪቷ ገጽ ማጥፋት አለባቸው::ይህንን ጉዳይ እንደያዙትም የካቲት ያሳየ ይመስለናል::

ሃይማኖቶችን በሚመለከተው በኩል፣ በሚያዝያ 10 በደሴ ከተማና በሚያዝያ 12 ደግሞ በአዲስ አበባ የተከናወኑት የእስላም ሰላማዊ ሰልፎች፣ እንደብዙው የየካቲት ድርጊቶች ሁሉ፣ በአገሪቷ ታሪክ ውስጥ አምሳያ የሌላቸው ናቸው::እነዚህ ሰልፎች የክርስቲያኑን ቁጣ ወይንም ጥላቻ በማስከተል ፈንታ፣ እንዲያውም ሙሉ ድጋፉንና አብሮ መሰለፉን ማትረፋቸው፣ በሃይማኖትም በኩል ሰፊው ሕዝብ ምን ያህል አርቆ አስተዋይነት እንዳለው ያሳያል:'ሃይማኖት የግል፣ አገር የጋራ' የሚለውን መመሪያ የገዥ መደቦች በአፍ እየተናገሩት በግብር ግን ሰፊውን ሕዝብ ሲከፋፍሉ የኖሩትን ያህል፣ ሰፊው ሕዝብ ግን በተራው በገዛ ራሱ ይህንን መመሪያ ከሥራ ላይ አውሎት መገኘቱ በጣም የሚያኮራ ነው::በዚህም ለብዙ ዘመናት ሲያወናብደን የኖረውን የሃይማኖት ንጭትን ማስፈራሪያ ሰፊው ሕዝብ ሰባብሮ በመጣሉ፣ አድሃሪውን ሥርዓት አንድ መሣሪያ አሳጥቶታል::

በበኩላቸው፣ ከገበሬው አብራክ የወጡት የኢትዮጵያ ቴቦች፣ ጥቅማቸውና ፍላጎታቸው ከማን ጋር እንደሆነ በየካቲት በግልጽ አሳይተዋል::እንደሌሎቹ መሳፍንትና መኳንንት ሁሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን መሳፍንትም — ጳጳሳትና ኤጲስቆጶሳት — ዘራፊዎችና ወንጀኞች፣ በተራው ሕዝብ ደም የወፈሩ መሆናቸውን በመግለጽ አውግዘዋቸዋል::ይህም ትልቅ ሬቮሉሽናዊ ድርጊት ነው::

መንግሥትና ሃይማኖት መለያየት አለባቸው፣ ሃይማኖት ሁሉ እኩል ነው የሚለው አቋም ትክክለኛ ነው::ይህንን አቋም የኢትዮጵያ ሕዝቦች ሁሉ ይደግፉታል::

በመጨረሻም፣ የኢትዮጵያ ሴቶች በበኩላቸው ያሳዩት የትግል መንፈስና የትግል ሰልፍ በአገሪቷ ታሪክም ውስጥ ቢሆን ከፍተኛ ቦታ እንደሚይዝ አይጠረጠርም::የመጋቢት 8 የኢትዮጵያ ሴቶች ሰላማዊ ሰልፍ የመላውን ዓለም አድናቆት አትርፏል::የኢትዮጵያ ሴቶችም



ለታላቅ ታሪካዊ ትግል ዝግጁ መሆናቸውን በሚገባ አሳይተዋል::

እንግዲህ እናጠቃልል::

በየካቲት እንቅስቃሴ ከዘጠና በመቶው የኢትዮጵያ በላይ በአንድ ወገን፣ ትላልቅ ባላባቶች፣ የቢሮ ከበርቴዎችና ደጋፊዎቻቸው በሌላ ወገን ተሰልፈው ታይተዋል::ከገዥ መደቦች በስተቀር የቀሩት የሕብረተሰቡን መደቦችና የሕዝብ ክፍሎች ሁሉ የለውጥ ፈላጊዎች መሆናቸውን አስመስክረዋል::የገዥ መደቦች እንደዛሬ ለብቻ ተነጥለው ወጥተው አያውቁም፣ የተጨቆኑና የተበዘበዙ ሕብረተሰባዊ መደቦችና ክፍሎችም እንደዛሬ በአንድነት ተሰልፈው አያውቁም::

የየካቲት እንቅስቃሴ ዋና መሪ የትንሽ ከበርቴው መደብ ነው::ይሁንና የወዛደሩ መደብ ከትግሉ ጠንክሮ ወጥቷል::ጡንቻውን ቀርጿል::የፖለቲካ ንቃቱን ከፍ አድርጓል፣ ይህ መደብ ለወደፊት ተገቢውን የመሪ ቦታውን እንደሚወስድ አይጠረጠርም::

---

## 2.3. የቀረቡት ጥያቄዎች ይዘትና የእንቅስቃሴው ዋና መልክ::

የየካቲትን እንቅስቃሴ በትግል ታሪክ በኩል በጣም ሀብታም ከሚያደርጉት ነገሮች አንዱ፣ ከየመደቡና ከየሕዝቡ ክፍል፣ ከየመሥሪያ ቤቱና ከየሙያ ድርጅቱ የቀረቡት ጥያቄዎች ብዛት ነው::በየካቲት፣ ጥያቄዎች እንደመስቀል አበባ ችፍ ብለው አብበው ነበር::ይህ የጥያቄዎች መፍለቅለቅ ቢያንስ ሶስት ነገሮችን ያሳያል:— ሀ. ሕዝቡ ብዙ ሥቃይን ቢያይ፣ ብዙ ችግሮችን ችሎ ኖሯል፣ ለ. ጥያቄን አውጥቶ ለመናገር፣ የደረሰበትን በደል በይፋ ለማስታወቅ ጉጉት ነበረው፤ ግን ሥርዓቱ አፍኖ አቆይቶታል፣ ሐ. ጥያቄዎችን እንደዚያ የጥር ማቅረብ ነገርን ማጣራትን፣ ወይንም ለማጣራት ያለውን ፍላጎት ያሳያል::ይህንን የጥያቄዎችን መደርደር አሠራር ሕዝቡ የግሉ ማድረጉ በጣም ጥሩ ነገር ነው::

እንደሚታወሰው፣ ሁለተኛው ክፍለጦር ያስመራን ከተማ ከያዘ በኋላ ያቀረባቸው ድርድሮች 23 ነበሩ::በኋላም፣ የተረሱ እሉ ተብሎ 6 ጨምሮባቸው ነበር::ይሁንናም፣ ይህንኑ ያህል የደረደሩ ሌሎች በኋላ ብቅ ብለዋል::ያዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት፣ የፍርድ ሚኒስቴርና በአገር ግዛት ሚኒስቴር የማዘጋጃ ቤቶች ክፍል ሠራተኞችም ያቀረቧቸው ጥያቄዎች 23—23 ነበሩ::በበኩላቸው የጎንደር ማዘጋጃ ቤትና በማስታወቂያ ሚኒስቴር የማስታወቂያና

የማሠሪያ ክፍል ሠራተኞች 29—29 ጥያቄዎች አቀርበዋል፡፡ ያዲስአበባው አራተኛ ክፍለጦር የቴሌኮሙኒኬሽን አስተማሪዎችና የአቃቢ የእርሻና አንቀሳቃሽ ኩባንያ ሠራተኞች ያቀረቧቸው ድርድሮች 11—31 ነበሩ፡፡ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችና የእስባሳ ሃይማኖት ተከታዮች 13 13፤ የኢትዮጵያ ሠራተኞች አንድነት ማህበርና አንድ ያልታወቀ ያዲስአበባ የገራ ቡድን 17—17፤ የአፋር ሕዝብ 10፤ የቀራስት ድርጅት ሠራተኞች 14፤ የብርሃንና ሰላምና የ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤቶች ሠራተኞች 20 እና 8፤ ያዲስአበባ ሆስፒታሎች ዶሬክተሮች 15፤ ያንበበ ማመሳለሽ ኩባንያ ሠራተኞች 30፤ ... አቀርበዋል፡፡ ከሁሉ ከፍ ያለ ቁጥር ያቀረቡት — እኛ እስከምናውቀው ድረስ — የብሔራዊ ኮ አድገት ሚኒስቴር ሠራተኞች ናቸው፤ 32 ነበር ያቀረቡት.. ምቹስ የቀረቡትን ጥያቄዎች ሁሉ ዘርዝር ለመዘለቅ አይቻልም

ይሁንናም የጥያቄዎች አንደዚያ መበርከት ሊያደናግረን አይገባም፡፡ እነዚህን ጥያቄዎች ሁሉ ሰብስበ በሁለት ዋና ክፍሎች ለመደብ ይቻላል፡፡ የመጀመሪያውን ክፍል ኢኮኖሚያዊና ሕብረተሰባዊ፤ ሁለተኛውን ክፍል የመብትና የፖለቲካ ነጻነቶች ልንላቸው እንችላለን፡ ይህ አከፋፈል ለትንተናና ነገርን አጣርቶ ለማቀረብ እንዲያመች ተብሎ ነው እንጂ፤ ሁለቱ ክፍሎች የተያያዙ ለመሆናቸው፤ አንዱ በሌላው ላይ ተጽእኖ ሀንዳለው፤ ውሎ አድርም ቢሆን ያንደኛው መለወጥ የሌላውን መለወጥም የሚያስከትል ለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ በጠቅላላ አነጋገር ነገ፤ የመጀመሪያው ክፍል የጊዜያዊ ጉዳዮች፤ ያስቸኳይ ጉዳዮች፤ በተወሰነ ቦታ ለሚወሰኑ ጉዳዮች የሚሆን ክፍል ነው፡፡ በተቃርኖ፤ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ የዘላቂ ጉዳዮች፤ የረጅም ጊዜና የአገር—አቀፍ ጥያቄዎች ክፍል ነው፡፡

ሁለቱ ክፍሎች በጥብቅ የተያያዙ ናቸው ብለናል፡፡ አሩቅ ባንሄድ አንድ ለምሳሌ የሚሆነን ጥያቄ እንመልከት፡፡ በየከተት እንቅስቃሴ ተደጋግመው ከቀረቡት ጥያቄዎች ውስጥ አንዱ 'መሬት ላራሹ' ነው፡፡ ይህ ጥያቄ በመጀመሪያ ደረጃ ቢታይ የገበሬውን የኑሮ ጥቅም የሚመለከት ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ገበሬው ኢኮኖሚያዊ ጥቅሙን ያገኝ የሚል ጥያቄ ነው፡፡ ነገ ደግሞ፤ 'ላራሹ' የተባለውን መሬት የያዙት ነገሥታዊ ቤተሰብ፤ መሳፍንትና መኳንንት፤ ነፍጠኞች ስለሆኑና እነዚህም የፖለቲካ ሥልጣኑን የጨበጡ ስለሆኑ፤ ጥያቄው ዘርፈ ዘርፈ (ፍሬ እንዲያውም ምንም ባይዘር በተቀኘ !!)ና የፖለቲካ ጥያቄ፤ እንዲያውም የሙሉ ሕብረተሰቡን መለወጥ የሚጠይቅ ታላቅ የፖለቲካ ጥያቄ ሆኖ እንደሚገኝ ግልጽ ነው፡፡ እንግዲህ፤ 'ኢኮኖሚያዊና ሕብረተሰባዊ' እና 'የመብትና የፖለቲካ ነጻነቶች' ጥያቄዎች ስንል፤ በሁለቱ መካከል የማይደፈር ገደብ ለማቆም መፈለጋችን እንዳይደለ ግልጽ መሆን አለበት፡፡

በተረፈም፤ በሰዚሁ አከፋፈል ትርጉም አንድ ሌላ ነጥብ እንጠቁም፡—

የመጀመሪያው ክፍል ጥያቄዎች — እንደደሞዝ ጭማሪ፤ የሥራ ዋስትናና፤ ጡረታ፤ ነጻ ሕክምና፤ ወዘተ. ያሉት — በመሠረቱ በትርጉሚያቸው በቦታው ላይ ያሉትን ሥልጣናት የሚያውቁ፤ የመንግሥትን ሥልጣን ከጥያቄ ውስጥ የማያገቡ ጥያቄዎች ናቸው፡፡



የሁለተኛው ክፍል ጥያቄዎች ግን — እንደንግግር፤ ጽሑፍ፤ ፓርቲዎችን የማቋቋም መብት ወዘተ. ያሉት — በፍጥረታቸው ለመንግሥት ሥልጣን ተቀናቃኝነትን፤ ለሥልጣን መወዳደርን የሚያመለክቱ፤ ወይንም ወደዚያ የሚያመሩ ናቸው፡፡ በታሪክ ውስጥ እንደታየው ሁሉ፤ አንድ ሥርዓት የመጀመሪያዎቹን ጥያቄዎች በሚገባ መመለስ ቢያቅተው፤ እነዚህን ጥያቄዎች ያቀረቧቸው መደቦችና የሕብረተሰብ ክፍሎች ሙሉ በሙሉ ወደሁለተኛው ዓይነት ጥያቄዎች — ወደዘላቂ፤ የረጅም ጊዜና መሠረታዊ የፖለቲካ ሥልጣን ጥያቄዎች — ይሸጋገሩና ግልጽ የሆነ ውድድር ለመንግሥት ሥልጣን ይደረጋል፡፡ እሰቱ የረቮሉሽን ሆነ ማለት ነው፡፡ ይህ የመጨረሽ ነጥብ እራሱ ይህንን አከፋፈል የመረጥንበትን አንዱ ምክንያት በበቂ ያስረዳል፡፡

ወደጥያቄዎች ወደራሳቸው እንመለስና፤ ኢኮኖሚያዊና ሕብረተሰባዊ ወይንም የጊዜያዊ ችግር ጥያቄዎችን ማን አቀረበ ? የፖለቲካ ወይንም ዘላቂ ጥያቄዎችንስ ?

ኢሠአማ ካቀረባቸው 16 ጥያቄዎች ውስጥ ቢያንስ አሥሩን ከፊተኛው ክፍል ውስጥ ለመደብ ይቻላል፡፡ ሁለተኛው ነጥብ የአነስተኛ ደሞዝ ጥያቄ፤ ሦስተኛው ስለደሞዝና የኑሮ ዋጋ ማስተካከያ፤ አራተኛው የዋጋ ቁጥጥር፤ ሰባተኛውና ስምንተኛው ጡረታን የሚመለከቱት፤ አሥረኛው የሥራን ተቋሚነት የሚመለከተው፤ አሥራሁለተኛው የባእዳን የሥራ ቦታ የሚጠይቀውና አሥራስድስተኛው ሥራአጥን የሚመለከተው ነጥብ፤ እነዚህ ሁሉ ኢኮኖሚያዊና ሕብረተሰባዊ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ ይሁንናም፤ ከዚህ በላይ ስለሁለቱ የጥያቄዎች ክፍሎች የተነገረውን በማስታወስ፤ ስለዋጋ ቁጥጥርና ስለባእዳን የሥራ ቦታ የተሰነዘሩትን ሁለት ጥያቄዎች በንወስ ዴ፤ ፀረኢምፔሪያሊስት፤ ስለዚህም መሠረታዊና ዘላቂ መሆናቸውን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ በተረፈም፤ ኢሠአማ ስለትምህርት፤ ስለራሱ ጋዜጣና ማህበራትን ስለማቋቋም መብት፤ ሥራን ስለማቆም መብት ያቀረባቸው ጥያቄዎች መሠረታዊ አገር—አቀፍ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ ነገ በድርድሮች ውስጥ እነዚህ የያዙት ቦታ የሁለተኛ ደረጃ ቦታ መሆኑን ማስተዋል ያስፈልጋል፡፡

የኢሠአማ ዋና ዋና ጥያቄዎች ጊዜያዊ ጥያቄዎች ነበሩ፡፡ ይሁንናም፤ ከነዚህ 16 ነጥቦች ውጭ፤ በቀጠሉት ቀኖች ውስጥ፤ ሥርዓቱን እንኳን ባይሆን የጊዜውን መንግሥት ከጥያቄ ውስጥ የሚያገቡ አስተሳሰቦችን በበራሪ ወረቀቶች መሰንዘር ለኢሠአማ የግድ ሆኖበት የነበር ይመስላል፡፡ ቀን ያልተጻፈበት ነገ የማህበሩን ማህተም የያዘ፤ 'የኢትዮጵያ ሠራተኞች የስቃይ ድምጽ' የሚል አንድ በራሪ እንዲህ ይላል፡—

'ለመላ ኢትዮጵያውያን ሁሉ በያሉበት፡—

የኢትዮጵያ ሠራተኞች አንድነት ማህበር ስለሠራተኞች መብት አጠባበቅ፤ ማለት ወዛደሩ ሠራተኛ እንደሠራተኛ ይኖር እንጂ እንደእንስሳ አይኖር፤ አይረገጥ፤... አሠሪው በየጊዜው በሠራተኛው ጉልበት በእጥፍና በስድስት እጅ እያተረፈና በፈለገው ም መንገድ ይህንን ትርፍ በአከፋ እንደመዛቅ በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ወደውጭ ከሚልከው ውስጥ በጁ ሠራተኛው ለጉልበቱና ለኑሮው በአወታሳይም ለመረረች ሕይወቱ ትንሽ መሻሻል ያገኝ፤ወዘተ..እያለ ከአሥር ዓመታት በፊት መንግሥትን እየጠየቀ

እና በየጊዜውም ችግሩን በየመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በኩል እያቀረበ በእነዚህ ባለፉት አሥር ዓመታት ውስጥ ምንም ዓይነት መፍትሄ መንግሥቱ ያልሰጠ ስለሆነና የሠራተኞች መብት የተባለው ሁሉ ከአገሪቱ ምድር እየጠፋ ...

መንግሥት 'ምንም ዓይነት መፍትሄ' አልሰጠምና መንግሥት ይለወጥ ወደሚባለው ደረጃ ለመሸጋገር የቀረው ትንሽ ነበር::በተረፈም፣ መቼስ የጠቅላላ ሥራ ማቆምን እርምጃ በሌሎች አገሮች ወዛደሩ በቀዛ አይወስደውም፣ የፖለቲካ ሥልጣን ጥያቄ የሚነሣበት ሁኔታ ይፈጠራልና::በኛ አገር ግን፣ በየካቲት ሁኔታ፣ የወዛደሩን ትግል የሚመራ ፓርቲ በሌለበት ሁኔታ የጠቅላላ ሥራ ማቆም እርምጃ በመሠረቱ የጠቀመው ለኢኮኖሚያዊ ጥያቄዎች ብቻ ነበር::

እንግዲህ ኢሠአማ ያቀረባቸው ጥያቄዎች የፖለቲካ ሥልጣኑን ጉዳይ የሚያስነሱ አልነበሩም::እንደዚሁም በየሥፍራው ወዛደሩ ያደረጋቸውን ትግሎች፣ የደረደራቸውን ጥያቄዎች ብንመለከት፣ ብዙዎቹ ጊዜያዊ የኢኮኖሚ ጥቅምን የሚመለከቱ ሆነው እናገኛለን::ማህበርን የማቋም መብት፣ የአድሎዊ ባለሥልጣኖችን መነሳትና የመሰሰሉትን አንዳንድ አነስተኛ ዲሞክራሲያዊ ጥያቄዎችን ቢያቀርብም፣ ዋናው የጥያቄዎቹ ይዘት ኢኮኖሚያዊና ሕብረተሰባዊ ነው::

ከወዛደሩ መደብ ወደእንቅስቃሴው መሪ ወደትንሽ ከበርቴው ስንሸጋገር ሁኔታው የተለየ ሆኖ እናገኛለን::የዚህ መደብ ንቁ ክፍል፣ ተማሪና ምሁሩ የጠየቀው ከ'ሕዝባዊ መንግሥት' መቋቋም የማያንሰውን ትልቅ የፖለቲካ ጥያቄ ነው::ነገርግን እዚህም ቢሆን መደቡ የራሱም ሆነ የወዛደር መደብ የፓርቲ አመራር ስላልነበረው፣ ያቀረበው ጥያቄ መሉ ሕዝቡን ወዲያውኑ አነሳስቶ ወደድርጊት የሚመራ አልሆነም::የሆነ ሆኖ እዚህ ላይ ዋናው ነገር የጥያቄው መነሳት ነው:: ...

በጠቅላላው ከትንሽ ከበርቴው የቀረቡት ጥያቄዎች መሠረታዊ የዲሞክራሲ ጥያቄዎች ናቸው::የካቲት 25 ቀን፣ ባዲስ አበባ ከተማ ላይ ከሄሊኮፕተር የተበተነው የ 11 ነጥቦች 'የጦር ሀይሎች' በራሪ ወረቀት እነዚህን ጥያቄዎች በቀሳ ጉደል የያዘ ቢሆን፣ ከርሱም ቀደም በየካቲት 21 ባንዱ ካልታወቀ ቡድን ተጽፎ በከተማው የተሠራጨው ወረቀት በ 17 ነጥቦች ሁሉንም አጠቃሎአል ለማለት ይቻላል::የጽሁፍ፣ የንግግር፣ የመሰብሰብና ማህበርን የማቋም ነጻነት፣ መሬት ላራሹ፣ ትምህርት ለሁሉ፣ የብሄረሰቦች፣ የሃይማኖቶች የጾታ እኩልነት፣ የፖለቲካ እሥረኞች ይፈቱ፣ ወዘተ.የሚሉት ጥያቄዎች መሠረታዊ የዲሞክራሲ ጥያቄዎች ነበሩ፣ ናቸውም::

እንግዲህ በጭሩ፣ ኢትዮጵያ ከኋላቀር ሥርዓት ገና ነጻ ያልወጣች አገር ናት::የከበርቴ ኢኮኖሚዋም በውጭ ኢምፔሪያሊስቶች ሥር የተጣመመበት ነው::አገሪቱ እንግዲህ ግማሽ ኋልታዊ፣ ግማሽ የጅክዘር ቀኝ ነች ማለት ነው::በእንደዚህ ዓይነቱ አገር፣ የየካቲት እንቅስቃሴ የመሰለ፣ በገዛ እጁ የተነሣሣ ሰፊ የሕዝቦች እንቅስቃሴ ድርጅትን ቢሆን



ከዲሞክራሲ ጥያቄዎች ሌላ ምን ሊያቀርብ ይችላል ? የንግግር፣ የጽሁፍና የግልጽ ፖለቲካ ትግል ልምድ፣ ነጻ ጋዜጦችና ፓርቲዎች ባልታወቀበት በዚህ አገር የሕብረተሰብ ቅራኔዎች ሲፈነዱ፣ ከዲሞክራሲያዊ የፖለቲካ ነጻነቶች ሌላ በምን ላይ ሊያተኩሩ ይችላሉ ? የወዛደሩ መደብ ባልተደራጀበትና የራሱን ፓርቲ ባልፈጠረበት፣ ኢምፔሪያሊዝም ብሄራዊ የከበርቴ መደብ እንዳይፈጠርና እንዳያድግ በደረገበት በገራችን ሁኔታ የዚህ እንቅስቃሴ መሪ ከትንሽ ከበርቴው ሌላ ማን ሊሆን ይችላል ?

በዚህ ሁሉ ገልጽ ሁኔታ ምክንያት፣ የየካቲት እንቅስቃሴ ዲሞክራሲያዊ ጥያቄዎችን በጉልህና በጣዓፊ አኳኋን ያቀረበ የሰፊው ሕዝብ ሬቮሉሽናዊ እንቅስቃሴ ነው እንላለን:: ዋና መልኩም የከበርቴ ዲሞክራሲያዊ ሬቮሉሽን መልክ ነው::

ይህ እንቅስቃሴ ያገኛቸው ድሎች ፍጹም የሚናቁ አይደሉም::የነአክሊሉን የቢሮ ከበርቴዎች ሥልጣን ገለበጧል፣ የንጉሡ ነገሥቱን ሥልጣን ፈጽሞ ባያጠፋውም እጅግ በጣም አመንምኖታል፣ የበሳበሱትን መደብ ዋና ዋና መሪዎች ለጊዜው ገለል አድርጓል::በተበሩ ያሉት ወጤቶች፣ እንደነንግግር፣ ጽሁፍና መሰብሰብ ነጻነቶች ያሉት ከሥራ ላይ የመዋል እድል ባያገኙዋቸው አይቀርም::የሚሸሸለው ሕገመንግሥት የሕዝብን መብቶች ያጸድቃል ተብሎ ይጠበቃል::እነዚህ ሁሉ መብቶች ከሥራ ላይ ከዋሉ፣ ለኢትዮጵያ ሕዝቦች የወደፊት ትግሎች አዲስ ጎዳናዎችን ይከፍታሉ::

የሆነ ሆኖ፣ የኢትዮጵያ ጊዜያዊ ሁኔታ ገና አልተደላደለም::እንቅስቃሴው ገና አላከተመም::በተለይም የመንግሥት ሥልጣን ጉዳይ ገና ፍጻሜውን አላገኘም::በዚህ ምክንያት፣ ስለተገኙት ድሎች ዘላቂነት በዛሬው እለት ከዚህ ሆኖ አፍ ሞልቶ ለመናገር ያስቸግራል::የመጣ ቢመጣ ግን፣ የየካቲት እንቅስቃሴ ያስገኘው ሊፋቅ ሊደመሰስ የማይችል ድል አለ::ይኸውም፣ ሕዝቡ እራሱ ከትግሎቹ የተማረው ትምህርት ነው::ይህ ትምህርት የወደፊቱን ትግል መንገዱ በበቂ አሳይቶአል::የወደፊቱ ትግል የሚደረገው ዘጠና በመቶው የኢትዮጵያ ሕዝብ ባንድነት ተሰልፎ ኋላቀር ሥርዓትንና ኢምፔሪያሊዝምን ከገሪቱ ገጽ እንዲያጠፋቸውና አዲስ ሕዝባዊ ሥርዓትን እንዲመሠርት ነው::ጊዜውም እየተቃረበ ሄዷል::

## 2.4. የመንግሥት ሥልጣን ጉዳይ

ዛሬ፣ ሀምሌ 6 ቀን 1966፣ የየካቲት እንቅስቃሴ ከተጀመረ ከአምስት ወሮች በኋላ፣ እነዚህ መስመሮች በሚጻፉበት በዛሬው እለት፣ የኢትዮጵያ ንጉሡ ነገሥት መንግሥት ሥልጣን በማን እጅ እንደሆነ፣ ከዚህ ሆነን በርግጠኝነት ለመናገር አስቸጋሪ ሆኖብናል::ከዚህ በላይ ከሰፈሩት ትንተናዎች ለመገንዘብ እንደሚቻለው ሁሉ፣ ሥልጣኑ በርግጥ በንጉሡ

ነገሥቱ እጅ አይደለም፡፡በእንግዳልካቸው እጅም አይደለም፡፡በፓርላማው ወይም በሌላ የሕዝብ ድርጅት ዘንድም አይደለም፡፡ዛሬ የመንግሥት ሥልጣን አለ ቢባል፣ ምናልባት ከሰኔ 21 እና22 ወዲህ በወታደሩ እጅ ብቻ ይሆን አይቀርም፡፡ግን ከየትኛው ወታደር እጅ ? ወታደር ሙች ሙሳ ያስተዳደሩን መኪና ያዘ ? እንዲያውስ የተደቆሰውን መንግሥት የጸጥታ ድርጅት እንዴን የት አል ያፈረሰው ? ደግሞም የመንግሥት ሥልጣን በወታደሩ እጅ ከሆነ፣ እነእንግዳልካቸው ለዚያ ሰፈር ምን ይሠራሉ ?

እነዚህ ጥያቄዎች ዛሬ ቁርጥ ያለ መልስ ባያገኙም በቅርብ ጊዜ ውስጥ ሳይበረፉ እንደማይቀሩ የታወቀ ነገር ነው፡፡በተለይም የተባለው የተሸሸለ ሕገመንግሥት ሲጸድቅና — ለመጸደቁስ ምን ማረጋገጫ አለን ? — ማን በሥልጣኑ እንደሚሰተፍ ሲታይ ለተጠቀሱት ጥያቄዎች አጥጋቢ መልስ ለመስጠት ይቻላል፡፡በዛሬው እለት ግን ይህንን የመንግሥት ሥልጣን የሚወስደውን መደብና ክፍል በመገመት ብቻ እንድንወስን ተገደናል፡፡ይሁንናም፣ ይህንን ግምት ከማቀረባችንም በፊት፣ መለስ ብለን ባለፉት አምስት ወራት ሥልጣን እንዴት እንደነበር ከዚህ በታች በጭሩ እንመልከት፡—

እንደሚታወሰው የነአክሊሉ—አካለወርቅ—ማሞ ታደሰ የቢሮ ከበርቴዎች መንግሥት በየካቲት 20 ቀን ወደቀ፡፡ከዚህ በኋላ ለሁለት—ሶስት ቀኖች የመንግሥት ሥልጣን በማን እጅ እንደነበረ ለማወቅ አስቸጋሪ ሆኖ ነበር፡፡በዚህ ሁኔታ፣ በቤተመንግሥቱ አካባቢ ሰፊ ውረውጥ ነበር፡፡ብዙ ከተደለተ በኋላ የነእንግዳልካቸው—አበቤ ካቢኔ በንጉሡ መሾሙ ተነገረ፡፡ግን እንግዳልካቸው በጠቅላይ ሚኒስትርነት ይሾም እንጂ፣ እርሱም ቢሆን የካቢኔውን ሙሉ አባላት ከዘመድ አዝማዶቹ አንኳ መርጦ ማቀረቡ ጊዜ ወሰደበት ነበር፡፡

የእንግዳልካቸውን መሾም ሕዝቡ ወዲያውኑ በሰፊው ተቃወሞ ነበር፡፡ተማሪዎችና አስተማሪዎች በሰላማዊ ሰልፍ በማድረግ የእንግዳልካቸውን መወገድና የነአክሊሉን መስቀል ጠየቁ፡፡ሕዝቡም 'አር በቀዘን ተተካ' በማለት በእንግዳልካቸው ላይ ያለውን ተቃውሞ ገለጸ፡፡በአዲስ አበባ የተሰራጨ አንድ ወረቀትም 'ትሸልን ትቼ ትበስን አገባሁ' በሚል ርእስ ስር እነእንግዳልካቸው ከነአክሊሉ የማይለዩ መሆናቸውን አስረዳ፡፡የሰፊው ሕዝብ ረቮሉሽናዊ እንቅስቃሴ በጥልቅቀትም በስፋትም እያደገ በመሄዱ፣ ከቀን እቀን በሚያቀርባቸው ጥያቄዎች 'አዲሱ'ን ባለሥልጣን ወጥሮ ያዘው፡፡ይሁንናም፣ እስከየካቲት ወር መጠረሻ፣ ምንም እንኳ የሥራ ማቆምና ሰላማዊ ሰልፎችን ማድረግ፣ ጥያቄዎችን መደርደር በሕዝቡ በኩል ቢቀጥልም፣ ያዲስ መንግሥት ሀሳፊዎች የተማሩ መሳፍንት ወገን ቀስ በቀስ ገፍቶ የመጣና ያየለ ይመስል ነበር፡፡ከመጋቢት መጀመሪያ እስከ ሰኔ ወር አጋማሽ ድረስ የነበረውን ጊዜ ብናጠቃልል፣ ከመንግሥቱ ዘንድ ባንድ በኩል ሕዝቡን ለመደለልና ለውጥ እንደሆነ ለማስመሰል ያልተጉነጉነ ፕሮፓጋንዳ እንዳልነበር እናስታውሳለን፡፡በሌላ በኩል ደግሞ ገልጽ የሆኑ ማስፈራሪያዎችና የጭቆና እርምጃዎች ይወሰዱ ነበር፡፡ይህ ጊዜ የመሳፍንት መደብ ሥልጣኑን ለማደላደል



ከፍተኛ ጥረት ያደረገበት ወቅት ነበር፡፡ለዚህ ጥረት ከተወሰዱት እርምጃዎች አንዳንዶችን ለመጥቀስ ይቻላል፡—

የወታደሩ ደሞዝ በ 50 በመቶ ገደማ መጠመር እራሱ አንድ ጸጥ ማስኚያ እርምጃ ተብሎ የታሰበ ነበር፡፡ከዚህ እርምጃ በኋላ የመጣው የ'ከፍተኛ ሕገመንግሥት ጉባዔ' መፈጠር ነው፡፡ጥቂት ቆይቶም፣ በመጋቢት 12 የቀደሞ ባለሥልጣኖችን 'በሥልጣን መባለግ' የሚመረምር ኮሚሲዮንእንዲቋቋም ታዘዘ፡፡በመጠረሻም፣ ንጉሡም እርጅታል፣ አልጋ ወራሹም ከልጋ ተቆረጧል የሚለውን ወረና ፍርሃት ለማጥፋት ሲባል ሚያዝያ 6 ቀን፣ መሳፍንት ለጊዜው መሣሪያ ይሆናል ያሉትን ዘርአ ያእቆብን 'በተጠባባቂ' አልጋወራሽነት ሸሙት፡፡ እንግዳልካቸውም እንደዚሁ—ሕዝብ የመጣበትን ተቃውሞ በመፍራት፣ መጋቢት 2 ቀን 'ጊዜያዊ ነኝ' የሚል መግለጫ ካወጣ በኋላ፣ ከሥር ቀናት በኋላ ግን የቀጠበ በጀት፣ ከዚያም መጋቢት 30 ቀን ያገን የረጅም ጊዜ መሸሸያ ፕሮግራም የተባለውን ማታለያ አወጣ፡፡የመንግሥቱ ጋዜጦች በበኩላቸው 'ጊዜ እንስጠው'፣ 'አሁንስ አበዛነው'፣ ወዘተ እያሉ ጊዜ ሲለምኑለትና ሕዝቡን ሲያወናብቡ ቆዩ፡፡

በዚሁ ጊዜና ያ ሁሉ'መሸሸያ' በሚዘነበበት ወቅት፣ በተንቀሳቀሰው ሕዝብ ላይ ከፍተኛ ጭቆና ይወርድ ነበር፡፣እዚህ ውጭ አገር የደረሱትን ዜናዎች ብቻ እንኳን ብንወስድ፣ የሚከተሉትን ጥቂቶች ለመጥቀስ ይቻላል፡፡

— መ ጋቢት 4 ቀን ስምንት አብተማሪዎችና ወደአሥር የሚጠጉ የኦሮሞ ብሄረሰብ ምሁራን ተይዘው ታሠሩ፡፡

— መጋቢት 19 በጂማ ከተማ 5000 ሰው ሰላማዊ ሰልፍ ሲያደርግ ፖሊስ ተኩስ ከፍቶበት ብዙ ሰው ገደለ፣ ብዙ አቆሰሉ፡፡

— መጋቢት 20 በአርባ ምንጭ ከተማም እንደዚሁ ፖሊስ በሰላማዊ ሰልፍ ላይ ተኩስ ብዙ ሰው ገደለ፣ ብዙ አቆሰለ፡፡

— መጋቢት 23 ያዲስ አበባ ተማሪዎች እንግዳልካቸው እንዲነሣ ተሰልፈው ሲጠይቁ ፖሊስ በዱላና በሚያስለቅስ ጢስ በታተናቸው፡፡

— መጋቢት 24 በጉባ ከተማ ከፍተኛ ተኩስ ተካሄደ ነበር፡፡

— መጋቢት 26 በጎንደር ከተማ በፍርድ ቤት ሠራተኞችና በፖሊስ መካከል በተደረገው ግጭት 6 ሠራተኞች ተገደሉ፡፡

— መጋቢት 27 ባዲስ አበባ ፖሊስ የገንዱ ትምህርት ቤት ተማሪዎችን ደበደበ፡፡

እነዚህ ጥቂት ምሳሌዎች እንደሚያሳዩት፣ የእንግዳልካቸው አዲስ መንግሥት ባንድ በኩል በመደለያ የመሸሸያ እርምጃዎች ሲጠቀም፣ በሌላ በኩል ደግሞ በግሃድ በጭቆናም ይጠቀም ነበር፡፡ከመጋቢት ወር መጠረሻ አንስቶ የልብ ልብ ይሰማውና አንዳንድ እርምጃዎችን እንደሚከተለው ይወስዳል፡— ሚያዝያ 7 ቀን በቴሌቪዥንና በሬዲዮ ሀይለኛ ማስፈራሪያ ይናገራል

ሚያዝያ 10 ቀን ለሁለት ሺ የጦር ሠራዊት አባሎች ንግግር ያደርጋል።በማግሥቱም የቀድ
ሞ ባለሥልጣኖች 'እንዲገለሉ' ሠራዊቱ የጠየቀውን ይፈቅዳል።ሚያዝያ 15 ቀን መንግሥቱ
ሥራ ማቆምንና ሰላማዊ ሰልፍን የሚከለክል አዋጅ ያወጣል።ሚያዝያ 19 ቀን፣ ወታደሩ
'አዲሱን ካቢኔ' እንደሚደግፍ፣ ያዲስአበባን ጸጥታ ሠራዊቱ እንደሚጠብቅ፣ ከንግዲህ ማን
ም ሌላ ሰው እንደማይያዝ፣ ወዘተ. ተገለጸ።ሚያዝያ 27 ቀን የነጻነት በዓል በሚከበር
በት ወቅት ንጉሠ ነገሥቱ 'የውጭ እጅ ያስገቡ አሉና እንደምስሰቸው' ቢል፣ የእንዳልካቸ
ው—አቢይ አበበ መንግሥት የተደላደለ መስሎ ታይቶ ነበር።ቢያንስ ለነርሱ።

ከየካቲት መጨረሻ ጀምሮ በጉልበትም ሆነ በሽንገላ በመጠቀም ለመደላደል እንደዚ
ያ ሲፍጨረጨር የቆየው የእንዳልካቸው መንግሥት በተራው በሰኔ 21—22 ላይ በሙሉ ጉደል
ከሥልጣን ተወገደ።የመደብ ወንድሞቹና ቀኝአዞች እሥራ ተከሣና አቢይ አበበ አሁን በእስር
ላይ ይገኛሉ።እንዳልካቸው ግን እንደገና ከእስር አምልጧል።ለማንኛውም ግን የኢትዮጵያ
ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ሥልጣን ባሁኑ ጊዜ በሠራዊቱ እጅ ነው ማለት ነው።ይህም እንግ
ዲህ በአምስት ወሮች ውስጥ በሥልጣኑ ሶስት መደቦች ተፈራርቀውበታል ማለት ነው።ከቢሮ
ከበርቴ ወደ መሳፍንት፣ ከመሳፍንት ወደ ትንሽ ከበርቴው።

ሥልጣኑን የያዘው ሠራዊት በሀምሌ 2 ቀን የ13 ነጥቦች ፕሮግራም አውጥቶ ለሕዝ
ብ አስታውቋል።እነዚህ ነጥቦች በዲስ ዘመን ጋዜጣ በሀምሌ 3 ቀን ታትመው ወጥተዋል።
በነዚህ 13 ነጥቦችና በዚሁ ጋዜጣ ውስጥ ለ'ኢትዮጵያውያን የፖለቲካ ስደተኞች' በተደረ
ገው ጥሪ ላይ ሰፊ ትንተና ብናደርግ ደስ ባለን ነበር።ግን እነዚህ ሁለት ጽሁፎች ብዙ
ጥያቄዎችን የሚያስነሱ በመሆናቸው ራሱን የቻለ ጥናት ያስፈልጋቸዋል።ለጊዜው በጥር በጥ
ሩ አንዳንድ ጥያቄዎችን በማቅረብ እንወስናለን።

የአሥራበስቱ ነጥቦች የመጀመሪያው ቁጥር 'የኮሚቴው አደ ተባብሮ ፍልስፍና' 'ኢት
ዮጵያ ትቅደም' የሚል መሆኑን ይጠቀብል።ይህ መሪ ቃል — ስሉገን — በስድስተኛዉና ሰበ
ተኛው ቁጥሮችም እንደገና የሚደገም ቢሆን፣ የመንግሥቱ ጋዜጦች ከሀምሌ 2 ወዲህ በሚያቀ
ርቧቸው ጽሁፎች ውስጥ ስለደርጉ ቢናገሩ፣ ይህንኑ መሪ ቃል እንደደርጉ መጠሪያ ስም አድ
ርገው ያቀርቡታል።እንደውነቱ ከሆነ፣ ይህ የ'አስተባባሪ ፍልስፍና' ምን ትርጉም ሊሰጠ
ው እንደሚችል ፈጽሞ ገልጸ አይደለም።የነጥቦች የመጨረሻ ቁጥር ደርጉ ወደፊት 'ዓላማው
ን በየጊዜው' ያስታውቃል ስለሚል፣ ምናልባት መሪ ቃሉን እራሱን ያብራራልን ይሆናል።በኛ
አስተባባሪ ግን 'ኢትዮጵያ ትቅደም' የሚለው መሪ ቃል እውነተኛና ትክክለኛ ትርጉም የሚኖ
ረው ለዘጠና በመቶው የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ ለገበሬውና ለወዛደሩ፣ ለተጨቋው የከተማ ነዋሪ
ደህንነትና ጥቅም በጃ መቆም ያመለከተ እንደሆነ ነው።



የያዝነውን የመንግሥት ሥልጣን ጉዳይ በሚመለከተው በኩል፣ ከአሥራበስቱ ነጥቦች
ቀነኛው ሰበተኛው ነው።ይህንን ነጥብ በሙሉ ከዚህ በታች እንጠቅሰዋለን፦

'7. ቀደም ቢል በነቀናቴው ዓላማ ውስጥ እንደተገለጠው ሁሉ፣ ይህ ደርግ 'ኢት
ዮጵያ ትቅደም' በሚለው መመሪያው መሠረት ወደፊት ለሚያቀርባቸውና ለሚያስፈጽማች
ው ማናቸውም ብሄራዊ ጉዳዮች ከካቢኔው ጋር የቀርብ ግንኙነት ማድረጉ ትክክለኛና
አስፈላጊም ነገር ሆኖ ያገኘውና ያመነበትም ስለሆነና የሚፈለገው ግንኙነት ቀደም
ብሉ በመጀመሩ የተከፈተዉ የግንኙነት መስመር በዚሁ ሁኔታ የሚቀጥል ነው።'

ይህ አንቀጽ ሠራዊቱ ሥልጣኑን መያዙን ያስታወቀበት አንቀጽ ነው ለማለት ይቻላል።ሁለት
ነጥቦችን በተለይ ማስተዋል ያስፈልጋል።የመጀመሪያው 'ለሚያቀርባቸውና ለሚያስፈጽማቸው'
የሚለው ሐረግ ነው።ይህ አዘሽ ማን እንደሆነ በግልጽ ያስያል።ሁለተኛው ነጥብ ደግሞ
በመጨረሻው ሐረግ ውስጥ ይገኛል።ይኸውም 'በዚሁ ሁኔታ የሚቀጥል ነው' የሚለው ነው።
ሠራዊቱ እንደ ገዲህከሲቪሉ መንግሥት በስተጀርባ ሆኖ ያሠራዋል፣ ይህም አሠራር ላልታወቀ ጊ
ዜ የሚቀጥል ነው ማለት ነው።ለማንኛውም በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ የትን
ሽ ከበርቴው መደብ ሥልጣኑን መያዙ ነው።

ይሁንናም፣ ከዚህ በላይ በገዱ በታ እንዳመለከትነው ሁሉ የመንግሥት ሥልጣን ጉዳ
ይ አሁንም ቢሆን አልተፈጸመም።በሚመጡት ወራት ውስጥ ያሁኑ ሁኔታ ሊለዋወጥ ይችላል።
የተባለው ሕገመንግሥት ገና አልወጣም።እርሱ ቢወጣ ሁኔታው የበለጠ ባይብራራ አይቀርም።

ያሁኑ የኢትዮጵያ ሁኔታ ያልተብራራ ነው ማለት ግን ካሁኑ ተገበረችንን ለመቀየስ
አንችልም ማለት አይደለም።የሚመጡት ዓመታት የታላቅ የመደብ ትግል ዓመታት እንደሚሆኑ
ካሁኑ ለመናገር ይቻላል።የኢትዮጵያ ሕዝቦች ገና ተደራጅተው መራራ ትግል ማድረግና የመ
ንግሥትን ሥልጣን በገዛ እጃቸው መጨበጥ አለባቸው።ይህም ጉዳይ በኛ ላይ ትልቅ ሀላፊነ
ትን እንደሚጥል ገልጽ ነው።ምን ብናደርግ ነው የሕዝቡ ትግል ወደዱል በተፈጠነ እርምጃ
እንዲጓዝ የምናደርገው ?

የየካቲት የኢትዮጵያ ሕዝቦች ረፖሉሽናዊ እንቅስቃሴ የመጣው በዙረይቱ ዓለም ላይ
ትልልቅ ለውጦችና ከፍተኛ ረፖሉሽናዊ አዝማሚያዎች በሚታዩበት ወቅት ነው::ኢምፔሪያሊዝም
በተለይም ያገራችን የጅአዙር ገዥ የሆነው ያሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም በውስጥና በውጭ ችግር
ች ውስጥ እየወደቀ ሄደአል::የምእራብ አገሮችም በኢኮኖሚና በፖለቲካ ችግሮች በየጊዜው
እየተወጠሩ ተይዘዋል::በኢኮኖሚ በኩል የቀጋዎች መምጠቅ — ኢንፍሌሽን — ኢምፔሪያሊስት
ዓለምን ከአደገኛ ሁኔታ ላይ ሲያደርሰው፣ ወዛደሩ ሕዝብ ደግሞ ለመብቱ የሚያደርገው ትግ
ል ለካፒታሊዝም እንደዚሁ አስፈሪ ሆኗል::በንግሊዝ፣ በፈረንሣይና በተለይም በጣሊያን
የተደረጉትና የሚደረጉት የወዛደር ትግሎች፣ የኢኮኖሚዎች መዓከም፣ የጠቅላላ ሕዝቡ በሥር
ዓቶቹ ላይ እምነት ማጣትና ይህም ያስከተላቸው የመንግሥት መለዋወጦች የከበርቴውን ሥርዓ
ት ክፉ ቀናት አጽፍጠው እንደሚጠብቁት ያሳያሉ::

በሌላ በኩል ደግሞ፣ የኢንዶቻይና ሕዝቦች የነጻነት ትግል፣ በአህጉራችን ደግሞ
የፖርቱጋል ቀኝ ገዥዎች ሕዝቦች፣ የአንጎላ፣ የሞዛምቢክ፣ ጊኒ ቢሳው የነጻነት ተዋጊዎች
ድል በድል እየተቀዳጁ በመጓዝ ላይ ናቸው::በቅርባችን፣ የአረብ አገሮች ፀረኢምፔሪያሊስ
ትና ፀረጽዮኒስት ትግል ብዙ ከፍታና ዝቅታ ቢደርስበትም፣ ጠቅላላ አዝማሚያው ወደትግሉ
መቀጠልና መረሩም ነው::የፓለስቲና ተዋጊዎች በበኩላቸው ትግላቸውን እንዳጠነከሩት ቢሆኑ
አሁን በጄኔቫ ይደረጋል የተባለው የሰላም ድርድር ሁሉ ዘላቂነት የሌለው፣ የጊዜው ሁኔታ
መጠገኛ እንጂ እውነተኛ መፍትሄ ስላልሆነ፣ የፓለስቲና ሕዝብ የተቀማውን አገሩን እስኪያ
ስመልስ ድረስ ትግሉን መቀጠሉ ፈጽሞ የማይቀር ነው::በኤደን የባሕር ሰላጤ አካባቢ
የሚደረጉት የነዶፋር ሕዝባዊ ትግሎች እየበረቱ የሚሄዱ ናቸው::

በጠቅላላው በዓለም ላይ በመካሄድ ያሉት ለውጦችና ትግሎች ለሠርቶአደሩ ሕዝብ
የሚያመች፣ ለኢምፔሪያሊስቶችና ለአድሃሪ ሀይሎች ሁሉ ግን መጥፎ ዘመንን የሚያበስሩ ና
ቸው::የኢትዮጵያ ሕዝቦች ረፖሉሽናዊ እንቅስቃሴ የተደረገው በዚህ ዓይነቱ ዓለም—አቀፍ
ሁናቴ ውስጥ ነው::ይህ እንቅስቃሴ በበኩሉ ሌሎች ትግሎችን እንደሚያስከትልና የኢትዮጵ
ያ ሕዝቦች ሕዝባዊ ሥርዓትን በገራቸው የሚያቋቁሙበት ጊዜ የግድ እንደሚመጣ ደጋግመን ገለ
ጸናል::እንግዲህ ከፍ ብለን በተመለከትነው ያገራችን ሁኔታና በዚህ በዛረው ዓለም—አቀፍ
አካባቢ የኛ ተግባር ምን መሆን አለበት ?



ይህንን ጥያቄ ከመመለሳችን በፊት፣ 'እኛ' ስንል ማንን ማለታችን እንደሆነ መግ
ለጽ ያስፈልግ ይመስለናል::ይህንን ጽሁፍ የሚያነቡትን የኢትዮጵያ ወጣቶች፣ እነዚያን
አንዳችም መሥዋእት ሳይፈሩ ሲታገሉ የቆዩትን የዩኒቨርሲቲና የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች፣
በውጭ አገር የሚገኙትን ወንድሞችና ማህበሮቻቸውን፣ በጠቅላላውም ባገርም ሆነ በውጭአገር
የሚገኙትን ኢትዮጵያውያን ምሁራን ማለታችን ነው::በጭሩ፣ የሕዝብ ወገንን የመረጡትንና
ለመምረጥ የተዘጋጁትን፣ ሳሚስ፣ የነጻነት፣ የእኩልነትና የወደፊት አርምዓ ኢትዮጵያ የሚ
ታገሉትንና ለመታገል የሚፈልጉትን ሁሉ ያጠቃልላል::

እንግዲህ የኛ ሁሉ ተግባር ምንድነው ? ይህንን ጥያቄ በሁለት ደረጃ ለመመለስ
እንሞክራለን::አንደኛ፣ በግለሰብ ደረጃ ያለብን ግዴታ ምንድነው ? ሁለተኛ፣ የተማሪና
የምሁር ድርጅቶቻችን ምን ዓይነት አገልግሎት መስጠት አለባቸው ?

1ኛ::<u>በግለሰብ ደረጃ</u>፣ ከሁሉ አስቀድሞ መገንዘብ ያለብን ነገር የመደብ ምንጮች
ንንና የመደብ አቋማችንን ነው::የመደብ አመጣጣችን ብዙውን ጊዜ የቱንሽ ከበርቴው ስለሆ
ነ፣ የመጣንበት ሕብረተሰብም በሁኑ የታሪክ ደረጃው የዚህን መደብ መስፋፋትና የአስተሳሰ
ቡን መስረጸት የሚያበረታታ ስለሆነ፣ በመጨረሻም የተማርነው ትምህርት ሁሉ የከበርቴውን
ርእዮተዓለም ያጎናጸፈን ስለሆነ፣ የመደብ አቋማችን ወላዋይነትን፣ አለሁ—አለሁ በይነትን
አንዳንዴ ታላቅ ደስታን — በሜሪካኑ ማህበራችን አበባል "moment of joy and thrill" —
በማግሥቱ ደግሞ ታላቅ ሀዘንን፣ አንዳንዴ ቆራጥነትን አንዳንዴ ማመንታትን ... በጭሩ፣
የማያቋርጥ ተለዋዋጭነትን ያሳያል::ከዚህ በላይ እንደተነገረው ሁሉ፣ ይህ መቼስ ከወዛደ
ሩ ቆራጥነት፣ እርሱ ለሕይወት ካለው ፍቅርና ደስታ፣ ከወዛደሩ ትእግሥትና የማያቋርጥ
ሥራ—ወዳድነት የማያቋርጥ ትጋት የራቀ ለመሆኑ እንድነትና ሁለት የለውም::ግን ደግሞ፣
በገራችን ረፖሉሺን ተደርጉ ሕዝባዊ ሥርዓት እንዲቋቋም ከፈለግን፣ በዚህም ሀላፊነታችንን
ለመፈጸም ከፈለግን፣ የቱንሽ ከበርቴ ሸክማችንን አራግፈን የወዛደሩን ርእዮተዓለምና ዲሲ
ፕሊን ለመጎናጸፍ መቻል አለብን::ይህም ቀላል ነገር አይደለም::

ስለነዚህ "የትንሽ ከበርቴ ጠባዮች ሲነገር፣ ላብዙ ጓደኞች፣ ብዙውን ጊዜ 'የቲዎሪ
ጉዳይ' ፣ በየእለት ኑሮ ውስጥ የማይታይ፣ ስለዚህም ባንዱ ጆሮ ተሰምቶ በሌላው ቢወጣ
ምንም ጉዳት የማያስከትል ነገር ይመስላቸዋል::ይህ 'መምሰል' እራሱ የግለሰብነት፣
የትንሽ ከበርቴ ርእዮተዓለም ምልክት ነው::ይሁንናም፣ ጥያቄው የእለት—በእለት ነገር መ
ሆኑን በተለይ በማህበሮቻችን አመራር ወይንም በመጽሄቶች ሥራ ውስጥ የተሳተፉት ጓደኞች
ያውቁታል ብለን እንገምታለን::የተሰጠውን ሀላፊነት ከግብ አለማድረስ፣ ቀጠሮ አለማክበር
ቸልተኝነት፣ ስንፍና፣ ስብሰባ ላይ እየተነሡ መጮህና ጥሩ ጥሩ ረፖሉሽናዊ ቋንቋ ማሰማ
ትና ከዚያ ውጭ ግን በሥራ ላይ አለመገኘት፣ ወዘተ. ይህ ሁሉ የትንሽ ከበርቴ ሥራ ነው

በሁኑ ጊዜ በውጭአገር ባሉት የኢትዮጵያ ተማሪዎች መካከል 'ሀይለኛ' የጥራዝ—ነጠቅነት አዝማሚያ አለ። ይህንን አዝማሚያ የያዙት ጓዶች 'ረቮሉሺናውያን ወዛደሮች ነን' ይላሉ። ይህ ጒረኝነት አራሱ ጥራዝ—ነጠቅነታቸውን ያሳያል። በነዚህ ጓዶች አስተሳሰብ ውስጥ በዙ ውዥንብ ስላለ፣ ከረቮሉሺናዊ መጻህፍት የነጠቋቸውን አባባሎች እንደጥንቆላ ድግምት ወዲያና ወዲህ በመወርወር ይጠረቃሉ። የኢትዮጵያን ተጨባጭ ሁኔታም ሆነ ረቮሉሺናዊ ቲዎሪን በማጥናት ፈንታ፣ በዚህም ላይ በመመሥረት ሳይንሳዊ ትንተናን በመቀከር ፈንታ፣ በጥራዝ ነጠቅነት ይሸመጥጣሉ። በተረፈም፣ የገራን ወይንም የገራ—ቀደምነትን ለምድ የደረቡ የቀኝ አድሃሪዎች መሆናቸውን በሥራቸው አስመስከረዋል።

ይህ በውጭአገሩ የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ውስጥ ገነኖ የሚታየው አዝማሚያ ጥናትንና ሳይንሳዊ ትንተናን አይወዱም። ስለዚህም ሰፊው ተማሪም እንዲያጠናና እንዲያሰላስል፣ አዙሮ እንዲያስብ፣ ረቮሉሺናዊ ሳይንስ ን እንዲማር አይፈልጉም። ይህንን አዝማሚያ በቶሉ ማወቅና ማክሸፍ የሰፊው ማህበርተኛ አንድ ጊዜያዊ ተግባር ነው።

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር ለመጀመሪያ ጊዜ የዛሬ ስድስት ዓመት በ 1960 'ተማሪና ምሁር ከሠራተኛውና ከገበሬው ጋር ተቀሃዱ፣ ከነርሱ ተማር፣ መልስህም አስተምራቸው' የሚለውን መሪያል አሰረጠ። ይህ ጥሪ ዛሬ በተፈጠረው አዲስ የኢትዮጵያ ሁኔታ ይበልጥ አስፈላጊና ይበልጥ ተገቢ መሆኑ ግልጽ ይመስለናል። ነገርግን፣ ረቮሉሺናዊ ቲዎሪን የገሉ ያላደረገ፣ የከበርቴ ርእዮተዓለምንና የትንሽ ከበርቴን ፀረረቮሉሺናዊ ወበዎች ፈጽሞ በያራገፍም እንኳን በመጠኑ ያላሸነፈ፣ የወዛደሩን ወበዎች በመጠኑም ቢሆን ያልተቀዳጀ ተማሪ ወይም ምሁር ከሠርቶአደሩ ሕዝብ ጋር እንዴት ሊቀሃድ ይችላል ? ከመቀሃዳችን በፊት የመደብ ወበያችንን ማሸነፍ የመጀመሪያው ተግባራችን ነው።

ሁለተኛው በግለሰብ ደረጃ ያሳበነ ግዴታ መስሉችን ፈልጎ ረቮሉሺናዊ ድርጅት እንደፈጠር መታገል ነው። በረቮሉሺናዊ እንቅስቃሴዎች ጉዳይ 'እንደዚህ ቢሆን ኖሮ' ተብሎ ክርክር የለምና ነው እንጂ፣ የየካቲት እንቅስቃሴ በገድ ረቮሉሺናዊ ድርጅት ቢመራ ኖሮ ሌላ ውጤትን ያስከትል እንደነበር ግልጽ ነው። ከሕገመንግሥቱ በኋላ የሚመጣው የኢትዮጵያ መንግሥት 'ፈቀደ—አልፈቀደ'፣ የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ሁኔታ የፖለቲካ ፓርቲዎችን መፈጠር ይጠይቃል። ረቮሉሺናውያን ነን የምንል ረቮሉሺናዊ ፓርቲ እንዲቋቋም መታገል አለብን።

2ኛ። በማህበራት ደረጃ። ማህበሮቻችን በፕሮፓጋንዳና በቅስቀሳ በኩል እስከሁን ያደረጉት አስተዋጽኦ የሚናቅ አይደለም። በገድ በኩል ያገሪቷን ሁኔታና የመደቦችን ትግል አብራርቶ በማስረዳትና የገዥ መደቦችን ጭቆናና ብዝበዛ በማጋለጥ፣ በሌላ በኩል ደግሞ፣ ለወደፊቱ የሚያዋጣውን ረቮሉሺናዊ መንገድ በመጠቆም፣ ያውሮፓ ማህበር መጽሄቶች ትግላችን እና ታጠቅ በዙ እንዳበረከቱ ምንም አይጠረጠርም። ከየካቲት እንቅስቃሴ ወዲህ በኢትዮጵያ



መንግሥ' ጋዜጦች ላይ የሚሰፍሩትንና ለምሳሌም እንዳንዱ የፓርላማ አባሎች የሚጠቀሙበትን ቋንቋ በንመለከት — 'ባላባታዊ ሥርዓት'፣ 'ሕብረሰባዊ ቅራኔ'፣ 'አድሃሪ'፣ ወዘተ — ሌላው ቢቀር፣ በአስተሳሰብ ደረጃ እነዚህ መጽሄቶች ምን ያህል እንዳበረከቱ ለመገመት ይቻላል። በፍጹም ሊናቅ የማይቻል አስተዋጽኦ ነው።

ያውሮፓው ማህበር መጽሄቶች በይዘትም ሆነ በቅርጽ ሁልጊዜ ለመሻሻል መጣጣር አለባቸው። እስከዛሬ የሰፊው ሕዝብ ድምጽ እንደነበሩ ሁሉ አሁንም በረቮሉሺናዊ ሳይንስ እየተመሩ ወደፊት መገስገስ አለባቸው። በተለይም አሁን የተነሣሣው ጥራዝ—ነጠቅነት ወደኋላ እንዳይመልሳቸው ትልቅ ትግል መደረግ አለበት። በፕሮፓጋንዳና በቅስቀሳ በኩል የሚደረገው ትግላችን ከፍ እንዲል ማድረግ የመጀመሪያው ተግባር ነው።

ይህ ተግባር በሚገባ ከሥራ ላይ ከዋለ፣ ሁለተኛውን ግዴታ፣ ሰፊውን ተማሪ ወደትግሉ ማስገባትና ማሰተፍን፣ እያንዳንዱ ማህበርተኛ ያለውን የመንፈስ፣ የጉልበት ወይንም የገንዘብ አስተዋጽኦ በትጋት እንዲያበረክት ማድረግን ለማከናወን ይቻላል። ማህበሮች መሥራት አለባቸው። ለዚህም የማህበሮችም አመራሮች ሆኑ የማህበር ነቃ አባሎች በርትተው መሥራት ይኖርባቸዋል።

ሶስተኛው የማህበሮች ተግባር የኢትዮጵያን ሕዝቦች ትግል ለውጭው ዓለም ማስታወቅ እና የዓለም ሕዝቦችን ድጋፍ ማስገኘት ነው። ከተራማጅና ዲሞክራሲያዊ ድርጅቶች ጋር ያለውን ግንኙነት ማጠንከር ያስፈልጋል።

በግለሰብና በድርጅት ደረጃ ብለን ከዚህ በላይ ያቀረብናቸው ተግባሮች የተያያዙ መሆናቸው ግልጽ ነው። እንደውነቱ ከሆነ፣ ግለሰቡ የሚሻሻለውና ተጋዳይ የሚሆነው በድርጅት ውስጥ ነው። ድርጅትም ጠንካራና ጠቃሚ የሚሆነው አባሎቹ ንቁና ተጋዳይ ረቮሉሺናውያን ሲሆኑ ነው። ከዚህ በላይ ስለግለሰቡ የሰጠናቸው ተግባሮች በዚህ ካልሆነ በሌላ እንዳይተረጐሙ እናስጠነቅቃለን። ረቮሉሺናዊ ለመሆን ግለሰቡ እቤቱ ቁጭ ብሎ ቲዎሪን ማጥናት አይበቃውም። ያጠናውን በሥራ በሕብረተሰቡ ውስጥ፣ በድርጅቶች ውስጥ፣ በትግል አባት መፈተን አለበት። ያለበለዚያ በአገራችን እንደሚባለው ሁሉ 'የጋን ውስጥ መብራት' ይሆናል። ለሕብረተሰቡ ምንም አይጠቅምም።

አንድ የመጨረሻ ቃል። ይህንን ምእራፍ በሰፊው በንገልጸው ደስ ባለን ነበር። ነገ በጊዜ እጥረትና እንደዚሁም ጽሁፉ የተራዘመ ስለሆነ፣ ባጭሩ አቀርበነዋል። እንግባቢው የኢትዮጵያን ሕዝቦች ለማገልገል ቆርጦ የተነሣ ከሆነ፣ በገዛ አራሱ ተፍጨርጭሮ፣ መዓት ሊሠሩ የሚችሉና ሊሠሩ የሚገባቸው ጉዳዮች እንዳሉ ሊገነዘብ ይችላል።

ተጨማሪ፡፡

## የ 1905 የሩሲያ ዴሞክራሲያዊ ረቮሉሽን፡፡

(በዚህ ጽሁፍ ውስጥ የዓመት አቆጣጠር በሙሉ እኤአ ነው፡፡)

ከ1917 ታላቁ የኦክቶበር ረቮሉሽን በፊት የነበረችው ሩሲያ የምኒልክን ኢትዮጵያ፣ የሀይለሥላሴንም ኢትዮጵያ ትመስል ነበር፡፡ምርጫቷ እስተኛ ሆኖ፣ ከአውሮፓ አገሮች ሁሉ ወደኋላ የቀረች ነበረች፡፡በአንድ በኩል ገዥው እስታዊ መደብ ሥር በመበስበስ፣ ዓለም በደነቀው የቀጋዐና የቀነፀት ኦርቶዶክሶች ቤናኒ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ዘወናኪምስት በሞቶ ያገሬቷ ሕዝብ በረሀብ፣ በመሃይምነትና በበሽታ ተቆራርቦ ኢሰብአዊ በሆነ አኗኗ ይኖር ነበር፡፡ጨሰኛው እንደኛው አገር ለባለመሬቱ በነሱን ከማስረከቡም በላይ፣ በየሳምንቱ በባላሽ ሶስት ቀናት ቢያንስ ለባለመሬቱ እንዲሠራ ይገደድ ነበር፡፡ከዚህ ሁሉ የተነሣ ሀብለኛው የሩሲያ ክረምት በመጣ ቁጥር በያመቱ በብዙ መቶ ሺህ እየተቆጠሩ ጨሰኞችና ቤተሰቦቻቸው በረሀብና በተላላፊ በሽታ ይረግፉ ነበር፡፡

እንደኢትዮጵያ የነገሥ ነገሥት መንግሥት ገዘት ሁሉ፣ 'ቅድስት ሩሲያም' 'የብሄሮች ወህኒ ቤት' ነበረች፡፡እውነተኛ 'ሩሲያኖች' ከምር እጅ በቁጥር የሚበልጧቸውን ሕዝቦች በመሣሪያ ሀይል አስገብረው ይዘው ይዘርፉና ይወቀሱ ነበር፡፡

የሩሲያ ነገሥ መንግሥት በክራይሚያ ጦርነት ከተሸነፈ በኋላ በጣም ተዳከም ስለነበርና በተጨማሪም ጨሰኛው በየቦታው እየተነሣ ባለመሬቶችን እየገደለና እየዘረፈ ስላስቸገረ፣ በ 1861 መንግሥቱ ጨሰኝነትን በሕግ ከለከለ፡፡ይሁን እንጂ፣ ገበሬው ከችግሩ አልላቀቀም፡፡ይህም የሆነበት ዋናው ምክንያት፣ ጨሰኝነት በሕግ ቢከለከልም፣ ገበሬው የራሱ መሬት ስላልነበረውና ዘር ዘር ለባለመሬቱ በኪራይም ሆነ በመጋዝ መሥራት የግድ ስለነበረበት ነው፡፡የጨሰኝነት መከልከል የጠቀመው ነገር ቢኖር ገበሬው እንደበፊቱ ከባለመሬቱ ጋር የተሳሰረ ባይሆን፣ ከራሱ መሬቱን ትቶ የመሄድ መብት ማግኘቱ ብቻ ነበር፡፡ሆኖም፣ ይበልጥ ገበሬ ከትውልድ ወደትውልድ የኖረበትን መሬት ትቶ ወደከተማ መሰደድ ስለማይሆንለት፣ እዚያው ለባለርስቶች ባበኋቂ ሁኔታ እየሠራ መኖር የግድ ነበረበት፡፡

ሩሲያዊ ባልሆኑ ብሔረሰቦች ውስጥ ዋናው፣ ፖሊሱ፣ ወታደሩ፣ ጠቅላላው የመንግሥት ሠራተኛ ሩሲያዊ ነበር፡፡ብሔረሰቦች ምንም መብት አልነበራቸውም፡፡ቋንቋቸውን ለመናገርና ለመጻፍ፣ ባህላቸውን ለመጠበቅና ለማስፋፋት፣ የገዛ አስተዳደራቸውን ለመምረጥ ምንም መብት አልነበራቸውም፡፡በተጨማሪም የነገሥ መንግሥት ብሔረሰቦችን ከሩሲያ በመግዛት፣ በየህዝብ እንዱን በሌላው እያጋጨ አንድነት እንዳይፈጥሩ ያደርግ ነበር፡፡በተለይ አይሁዶችን ደጋግሞ አስመርሯል፡፡

ይሁንናም፣ የምርዓቱ ዘፈፈነትና ጨቋኝነት እንዳለ ሆኖ፣ ጨሰኝነት ከተወገደ በኋላ፣ የከበርቴ ኢኮኖሚ በሩሲያ በአጭር ጊዜ ውስጥ በጣም ተስፋፋ፡፡በ 25 ዓመታት ውስጥ፣



ከ 1865 እስከ 1890፣ በፋብሪካዎችና በምድር ባቡር የሚሠሩት ወዛደሮች ቁጥር እጥፍ ሆነ፡፡ከ 706 ሺህ ወደ አንድ ሚሊዮን 433 ሺህ ከፍ አለ፡፡ከዚያም እስከ 1900 ባሉት አሥር ዓመታት ውስጥ ደግሞ ከባድ ኢንዱስትሪ በጣም ስለተስፋፋ፣ በመላ ሩሲያ የወዛደሩ ቁጥር እንደገና እጥፍ ሆኖ 2 ሚሊዮን 792 ሺህ ደረሰ፡፡ይህንን ብዛት ያስከተለው በተለይ የምድር ባቡር ሥራ መስፋፋት ነበር፡፡

አዲሱ የሩሲያ ወዛደር መደብ በጣም የተጠቀነና የተበዘበዘ ነበር፡፡ስለዚህም ደጋግሞ ሥራ እያቆመ ይታገል ነበር፡፡ በ 1875 በኦዴሳ ከተማ 'የደቡብ ሩሲያ ሠራተኞች አንድነት'፣ በ 1878 በፔትሮግራድ — የዛሬይቱ ሌኒንግራድ — 'የሰሜን ሩሲያ ሠራተኞች አንድነት' የሚባሉ፣ በነቁ ወዛደሮች የሚመሩ ማህበሮች ተፈጠሩ፡፡በነዚህ ድርጅቶች አማካይነት የሩሲያ ወዛደር እንቅስቃሴ እየተስፋፋ ሄደ፡፡ ከ 1881 እስከ 1886 ባሉት አምስት ዓመታት ውስጥ 48 የሥራ ማቆም አድማዎች ሲወሰዱ፣ 80 ሺህ ወዛደሮች ተሳትፈውባቸዋል፡፡

ከ 1900 እስከ 1903፣ በሩሲያ ትልቅ የኢኮኖሚ ውድቀት ደርሶ ነበረ፡፡በገጠሩና በከተማው ሁሉ ለሕዝቡ ችግር ተፈጠረ፡፡በዚህ ላይ ደግሞ በ 1904 ጃፓን ሩሲያን በድንገት ወጋታ አሸነፈለች፡፡ሁለቱ የተጣሉት ምሥራቅ እስያን ለመከፋፈል በሚያደርጉት ውድድር ነበር፡፡የሩሲያ ወታደር ምግብም፣ መሣሪያም፣ የሚጠነቀለት አዛዥም ስላልነበሩት በቀላሉ ተሸነፈ፡፡ጃፓኖች በዘመናዊ መሣሪያ ወታደሩን ሲመቱት፣ የሩሲያ መንግሥት ገና የቅዱሳንን ምስሎች ለወታደሩ ጥና ይልክ ነበር፡፡ባቡሮች ምግብና መጠቀ ወደጦር ግንባሩ በማምጣትና ሲመለሱም ቁስለኞችን ይዘው በመሄድ ፈንታ፣ ሲሄዱ ምስሎችን ሲመለሱ ደግሞ ጄኔራሎች ከእስያ ሕዝብ የዘረፏቸውን እቃዎች ይዘው ይመለሱ ነበር፡፡በከተማውና በገጠሩ የገባው ችጋር፣ የወታደሩ መሸነፍና የነገሥ ወረዳ የሰላም ድርድር መፈረም፣ ይህ ሁሉ በአንድነት ተደምሮ የሩሲያን ሕዝብ ክፉኛ አናደደው፡፡በየትላልቅ ከተማው ወዛደሩ ሥራ እያቆመ፣ በየገጠሩ ገበሬዎች እየተነሱ የባለመሬቶችንና የሀብታሞችን ንብረት እየዘረፉ፣ ወታደሩም በያለበት እያጉረመረመ ሁሉም ተቃውሞውን ይገልጽ ጀመር፡፡

ቀደም ብሎ በ 1883 ተቋቁሞ የነበረው የሩሲያ ረቮሉሽናውያን 'ወዛደርን ነጻ ለማውጣት' የተባለው ቡድን ረቮሉሽናዊ ጽሁፎችን በመተርጎምና በመደረስ የሩሲያን ወዛደር ማስተማር ጀምሮ ነበር፡፡እንደዚሁም በ 1898 በሚንስክ የተቋቋመው የሩሲያ ሶሻል ዴሞክራቲክ ፓርቲ ይህንኑ ሥራ ጀምሮ ነበር፡፡በ 1900 ሌኒን ወደውጭ አገር ከወጣ በኋላ ከነዚህ ረቮሉሽናውያን ጋር ተገናኝቶ ተስማምቶ በዓመቱ መጨረሻ ኢስክራ የተባለው ጋዜጣ የመጀመሪያ ቁጥር በውጭ አገር ታትሞ እንዲወጣ ተደረገ፡፡የሩሲያን ወዛደር በሌኒን አስተባባሪ ያስተማረና ያደራጀ ጋዜጣ ይህኛው ነበር፡፡ ... እንግዲህ፣ በጠቅላላው ከ 1905 የሩሲያ ረቮሉሽን በፊት የነበረው ሁኔታ ይህ ነበር፡፡በአንድ በኩል ታላቁ የኢኮኖሚ ውድቀት፣ ችጋር፣ የወታደር ማጉረምረም፣ በሌላ በኩል ደግሞ ወዛደሩን በማስተማርና

በማደሪያቸው ላይ የነበሩ ፓርቲዎች ነበሩ:: ...

በ 22 ጃንዋሪ 1905፣ በፔትሮግራድ ከተማ ትልቅ ሰላማዊ ሰልፍ ተደረገ:: ይህ ሰልፍ እንዲደረግ ያነሣሣው ጋፖን የሚባል ቄስ ነበር:: ይህም ቄስ ይህንን ሰልፍ እንዲያዘጋጅ የተደረገው በመንግሥት የጸጥታ ፖሊስ ተገፋፍቶ እንደሆነ በኋላ ተደርሶበታል የሆነ ሆኖ፣ በዚህ ቀን ወደ 140 ሺ የሚጠጉ የፔትሮግራድ ነዋሪዎች፣ ወዛደሮች ከነሚስቶቻቸውና ከነልጆቻቸው ሆነው፣ የቀሳውስትን ምስሎች፣ የንጉሡንም፣ መስቀሎችንና ሌሎችንም የቤተክርስቲያን እቃዎች ይዘው ተሰልፈው ወደቤተመንግሥት አመሩ:: ለንጉሡ ለማቅረብ የወሰዱት አቤቱታ እንዲህ የሚል ነበር:-

'እኛ የፔትሮግራድ ከተማ ወዛደሮች፣ ሚስቶቻችን፣ ልጆቻችን፣ ረዳት የሌላቸው ወላጆቻችን፣ ካንተ ከገዢያችን እውነትንና መከታን ለመፈለግ መጥተናል:: በጣም ደኸየን፣ እንደተጨቆን ነን፣ ሊነገር የማይችል የሥራ ጫንት ይጭኑብናል፣ ያዋርዱናል፣ ሰዎች አንመስላቸውም... ሁሉንም በትዕግሥት ችለነው ነበር፣ ግን ሁልጊዜ ይበልጡን እየደኸየን፣ ይበልጡን ፍርድ እየጎደለብንና ይበልጡን ወደድንቁርና እየሰመጥን ሄደናል፣ ፈላጭቆራጭነትና አምባገነንነት አስጠምቀውናል፣... ትዕግሥታችን ከወሰኑ ደርሷል:: ከእንግዲህ ለኛ ከዚህ ከማይቻል ሥቃይ ሞት የሚሻልበት ያቺ አስፈሪ ደቂቃ ደርሰናል:: ...'

የሩሲያ ንጉሥ ህሳስ ግን እንኳንስ ይህንን አቤቱታ ሊያዳምጥ፣ እንዲያውም በዚህ መዓት ሕዝብ ላይ ተኩስ እንዲከፈት አዘዘ:: አንድ ሺህ ወዛደሮች እዚያው ተገደሉ፣ ከሁለት ሺህ በላይ ቆሰሉ:: ፔትሮግራድ በወዛደሩ ደም ተጥለቀለቀች:: ይህ ጭካኔ ግን የሠርቶአደሩን ሕዝብ ዓይን ከፈተለት:: በልመናና በጸሎት ምንም እንደማይገኝ፣ በትግልና በጉልበት ብቻ መብትና ነጻነት እንደሚመጣ እዚያው በቦታው ላይ የነበሩት በልሼቪኮችም በድጋሚ አስረድተዋል:: የፔትሮግራድ ፍጅት በሩሲያ ታሪክ ውስጥ 'የደም እሁድ' ተብሎ ይታወቃል::

ይህ ፍጅት የሠርቶአደሩን ሕዝብ ትግል ያስቀረዋል ብሎ የተመኘው የገዢው መደብ ተሳስቷል:: እንዲያውም ትግሉ ተፋፋመ:: ወዛደሮች ሥራ ማቆምን ገበሬዎችም ማመጽን ቀጠሉ: ከዚያም በጁን — ሰኔ — 1905፣ ፖትዮምኪን በተባለው የጦር መርከብ ላይ መርከበኞች አመጹ:: አለቆቻቸውን ይዘው አሰሩ:: ነገርግን ያመጸኞች የፖለቲካ ብስለት ዝቅተኛ ስለነበረና ያመጹም አመራር በቦልሼቪኮች እጅ ስላልነበረ፣ አንዳንዶቹ መርከበኞች ወደኋላ ማፈገፈግ አመሩ:: በመጨረሻም፣ አመጸኞች እጃቸውን የግድ መስጠት ሆነባቸው፣ አንዳንዱ መሪዎች ቢረሸኑ አንዳንዶች ደግሞ በስደት እንዲኖሩ ተደረገ::

በሕዝቡ ትግል ተወጥሮ የተያዘው የሩሲያ መንግሥት በጉልበት ብቻ መጨቆን እንደማያዋጣው ስለተረዳ፣ ሌሎችን መንገዶች ይፈልግ ጀመር:: በዚህም መሠረት፣ በአንድ በኩል በአይሁዶች፣ በአርመኖችና በታታሮች ላይ ፍጅትን ሲያዘጋጅና ሲያደርስ፣ በሌላ በኩል ደግሞ፣ ሕዝቡ የሚወከልበትን 'አማካሪ' ፓርላማ እንደሚጠራ አስታወቀ:: ግን ይህም ተንኮል አልያ ዘለቀም ነበር::



በኦክቶበር — ጥቅምት — 1905፣ በሞስኮ በሚገኝ በአንድ ትልቅ ማተሚያ ቤት ሠራተኞች ሥራ አቆሙ:: ወዛደሮችን በመደገፍ የቢሮ ጸሀፊዎች፣ ተማሪዎች፣ ምሁራን — ጠበቆች፣ መሀንዲሶች፣ ሀኪሞች፣ ወዘተ. — ሥራ አቆሙ:: በዚህ ሁኔታ በ 17 ኦክቶበር ንጉሡ አዋጅ አወጀ:: በአዋጁም መሠረት፣ የማሰብ፣ የመናገር፣ የመጻፍ፣ የመሰብሰብና ማህበራትን የማቋም ነጻነቶች ይፈቀዳሉ የሚል ተስፋ ተሰጠ:: ግን ይህም ማታለያ ነበር:: በአንድ በኩል እነዚህን ነጻነቶች በተስፋ ሲሰጥ፣ በሌላ በኩል ግን ልዩ ልዩ አድሃሪ የምስጢር ድርጅቶችን አቋቁሞ፣ እነዚህ፣ የወዛደር መሪዎችን፣ ምሁራንንና ሌሎችንም ሥርዓቱን በመቃወም የታወቁትን ሰዎች በምስጢር ማስገደል ጀመረ:: ይሁን እንጂ፣ ይህም ወንጀል የሕዝቡን ትግል ወደኋላ አልመለሰውም:: እንዲያውም የሩሲያ ወዛደር ሶቪየቶችን — እነዚህን ፍጹም አዲስ የሆኑትንና በኋላም የመንግሥት ሥልጣን ዋና መሠረት የሆኑትን የመማክርት ድርጅቶች — እንዲፈጥር ሁኔታው ፈቀደለት::

በኖቬምበር — ህዳር — 1905፣ የወዛደሮች ሥራ ማቆምና የገበሬዎች በመላ ገጠሩ መሸፈት፣ የወታደሮችም አመጽ በገሪቷ በሙሉ ተስፋፋ:: በጥቁር ባሕር ላይ የነበረውም የመንግሥት የባሕር ሀይል እንደዚሁ አልፎ አልፎ አመጸ:: በጠቅላላ ሩሲያ ትልቅ ነገር ያለበት ሁኔታ ተፈጠረ::

በ 18 ዲሴምበር — ታህሣሥ — 1905 በሞስኮ ከተማ ጠቅላላ የሥራ ማቆም አድማ ተጀመረ:: ሁለት ሺ የወዛደር ፈቃደኞች የመንግሥትን ፖሊስ ለመቋቋም መሣሪያ ይዘው ተዘጋጁ:: በ 22 ዲሴምበር በከተማው ውስጥ ምሽጎች በየመንገዱ ላይ በወዛደሩ ተገነቡ:: በወዛደሩና በፖሊስ በወታደር መካከል ተኩስ ተጀመረ:: ወዛደሮችን የሞስኮ የቦልሼቪኮች ኮሚቴ ይመራቸው ነበር:: ይሁንናም፣ ይህ ትግልና የሌሎች ወዛደሮች ትግል ሳይቀናበር ስለቀረ፣ መንግሥት ተጨማሪ ወታደሮችን በምድር ባቡር ከሌላ ቦታ አምጥቶ በሕዝቡ ላይ አሰለፈ:: ጀግኖች የሞስኮ ወዛደሮች በብዙ እጅ የሚበልጧቸውን የንጉሡን ወታደር ዘጠኝ ቀን ሙሉ በቆራጥነት ተቋቋሙት:: እስከመጨረሻው ሰው ድረስ ደማቸውን አፈሰሱ:: በዚህ አኳኋን ትግላቸው ተደመሰሰ::

የሩሲያ መንግሥት የሁለት ስለት ሰይፍ ፖለቲካውን ቀጠለ:: በአንድ በኩል ጭቆናውን ከማንኛውም ጊዜ ይበልጥ አጠነከረ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ጉልበት ብቻ ረብሻዎችን ለመደምሰስ የማይችል መሆኑን በመረዳት፣ አንዳንድ የፖለቲካ መብቶችን ሰጠ:: በጭቆናው በኩል፣ እላይ እንደተባለው ወዛደሩን በወታደሮች አስደበደበ፣ በገጠር የተነሡትን የገበሬ አመጾች በታላቅ ጭካኔ ደመሰሰ:: የጆርጂያን፣ የፊንላንድን፣ የፖላንድን፣ ወዘተ. ብሄረሰቦች ትግሎች የሚደመስሱ ወታደሮች በመላክ ሰላማዊውን ሕዝብ አስጨፈጨፈ:: በፖለቲካ መብት በኩል፣ በዲሴምበር 1905፣ ሕግ የሚያወጣ፣ ሥራው እንደበፊቱ መንግሥትን ማማከር ብቻ ያልሆነ

ፓርላማ እንዲቋቋም የንጉሡ መንግሥት ፈቀደ:: ይሁን እንጂ አሁንም ቢሆን በርግጥ ነጻና ዲሞክራሲያዊ፣ የተሟላና በምስጢር የሚፈጸም አመራረጥ ለሕዝቡ አልተፈቀደለትም::እንዲያውም አራት የሕዝብ ክፍሎች ወኪሎቻቸውን የሚመርጡላቸውን ሰዎች እንዲመርጡ ተደርጎ ነበር:: እነዚህም የባለመሬቶች፣ የከተማው ከበርቴ፣ የገበሬዎችና የወዛደር መደቦች ነበሩ::

የሩሲያ ፈላጭ ቆራጭ ሥርዓት በነዚህ ጣምራ እርምጃዎች ቢጠቀምም የሕዝቡን ትግል ሊያቆመው አልቻለም::በ 1905 ሬቮሉሺኑ ከተሸነፈ በኋላ፣ የሬቮሉሺኑ ሀይሎች፣ በተለይም የቦልሼቪኮች ፓርቲ በርጋታና በሥርዓት ወደኋላ አፈገፈገ::ለመጪው የሕዝቦች ትግልና ለሬቮሉሺኑ በተሻለ አቋን ለመሰናዳት ይመች ዘንድ::

የ 1905 ሬቮሉሺን እንደዚያ በወዛደሩ ደም መፍሰስ ቢያልቅም፣ በ 1906 ከአንድ ሚሊዮን በላይ የሩሲያ ወዛደሮች ሥራ ቢያቆሙ፣ በ 1907 ደግሞ ከ 740 ሺ በላይ እንደዚሁሥራ አቁመው ታገለዋል:: ...እንደሚታወቀውም፣ ይህ ዲሞክራሲያዊ ሬቮሉሺን በተከናወነ በአሥራሁለት ዓመት ታላቁ የኦክቶበር ሬቮሉሺን ተደርጎ፣ የሩሲያ ሠርቶአደር ሕዝብ በዓለም ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያውን የወዛደር ሥልጣን የሰፈነበት አገር አቋቋመ::

ሌኒን ስለ 1905 የሩሲያ ዲሞክራሲያዊ ሬቮሉሺን ሲናገር፣ 'ልምምድ ማረጊያ' ነበር ብሏል::በአገራችን የተደረገውና አሁንም የቀጠለው እንቅስቃሴም በአገራችን የታሪክ ደረጃና በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ በርግጥ 'ልምምድ ማረጊያ' ነው ልንል እንችላለን::ያገራችን ሁኔታ የተወሳሰበ ነው፣ የዘረጋው ዓለም ሁኔታም እንደዚሁ::መንገዱ ጠመዝማዛና ወጣገብ የቆሰበት ሊሆን ይችላል፣ የሆነው ቢሆን ገን የኢትዮጵያ ሕዝቦችም ሬቮሉሺናቸውን ማደረጋቸውና የራሳቸውን አዲስ የሕዝብ ሥርዓት ማቆማቸው ፈጽሞ የማይቀር ነው::